
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3572 | ቅዳሜ ግንቦት 1 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባካሄደው ጉባኤ፡-

- በአሁኑ ወቅት በተለያዩ አማራጮች 165 ሺህ 903 ቤቶች በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፤ በወቅቱ እንዲጠናቀቁም የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑ ተጠቁሟል፤
- ምክር ቤቱ ለ2018 ዓ.ም በጀት አመት ተጨማሪ 9 ነጥብ 94 ቢሊዮን ብር በጀት አጽድቋል፤


6

ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ በሰጡበት ወቅት

## ከጥሻ ወደ መናፈሻ


8

ፎቶ- በገነት ወንድሙ
በራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ የሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ልማት በከፊል

## የመዲናዋ አረንጓዴ ጋሻ


16

ፎቶ- ከገፀ ድር
ከተማዋን አረንጓዴ የማልበስ ጥረት ውጤት እያሳየ ነው

## የመዲናዋ የጥበብ ዳናዎች


11

ፎቶ- ከፋይል
አዲስ አበባን ያስዋቡት አዳዲስ የሥነ ጥበብ አሻራዎች


# የዜጎቿን አቅም ወደ ውጤት የለወጠች ከተማ

- ከ2010 እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ ለ2 ሚሊዮን 432 ሺህ 353 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል

በመለሰ ተሰጋ

በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ዕድገት የሚለካው በተፈጥሮ ሀብቶች፣ በመሠረተ ልማት ወይም በካፒታል ኢንቨስትመንት ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ጥንካሬ እና ምርታማነትም ጭምር ነው። እናም የአንድ ሀገር ከፍታ የሚወሰነው የሚሰራውን ኃይል በተለይም ወጣቱን በሁለንተናዊ መልኩ በመደገፍ ጠንክሮ እንዲሰራ ማድረግ ሲቻል ነው ይላሉ የልማታዊ ኢኮኖሚክስ ምሁሩ ፕሮፌሰር ቴዎዶር ደብሊው ሹልትዝ "Investing

ወደ ገጽ 4 ዞሯል



በአዲስ አበባ ከተማ ከ2013 እስከ 2018 ዓ.ም የተፈጠረ የስራ ዕድል

# ለወላጅ እፎይታ ለህፃናት ደስታ

- አዲስ አበባ የመጀመሪያውን "አዲስ አፍሪካ ቀዳማይ ልጅነት ጉባኤ" ከግንቦት 3 ጀምሮ ለሦስት ቀናት እንድታስተናግድ ተመርጣለች


በሳህሉ ብርሃኑ

የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ሀገር ማለት በህጻናት ሳቅ ውስጥ የሚቀረጽ ተስፋ፣ በአዳጊዎች ትከሻ ላይ የሚሰቀል ራዕይ ነው ይላሉ። ዛሬ የምናቅፋቸው ህጻናት ነገ ሀገርን የሚያቅፉ ግዙፍ ክንዶች ይሆናሉ። በመሆኑም ለእነሱ የሚደረገው እንክብካቤ የበን

ወደ ገጽ 5 ዞሯል



# ርዕሰ አንቀፅ



## ድህነትን በትጋት ድል ለመንሳት እድሎችን በአግባቡ መጠቀም ይገባል!

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ፀጋዎቿ የታደለች፣ በከርሰ-ምድርና በገፀ-ምድር ሀብቷ የምትታወቅ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ድህነትን በትጋት መርታት የሚችል ወጣት የሰው ኃይል ያላት ሀገር ናት። ሆኖም ይህ እምቅ አቅም ለዘመናት ከድህነትና ከተመፅዋችነት አዙሪት ሊያወጣን ሳይችል ረጅም ዘመናትን አስቆጥሯል። የድህነት የታሪክ ጠባሳችንን ለመፋቅና እንደ ሀገር አዲስ ምዕራፍ ለመጀመር አማራጭ የሌለው መፍትሔ ጠንካራ የሥራ ባህልን መገንባትና በየደረጃው የሚፈጠሩ የልማት ዕድሎችን በአግባቡ መጠቀም መሆኑ አያከራክርም። ዛሬ ላይ የምንመለከታቸው ግዙፍ የልማት እንቅስቃሴዎችና የመንግሥት ጥረቶች የሚያሳዩትም ይህንኑ እውነት ነው፤ ችግሮችን በማውራት ብቻ ሳይሆን፣ ዕድሎችን ወደ ውጤት በመቀየር ድህነትን ታሪክ ማድረግ ይቻላል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የነዋሪዎችን ሕይወት ለማሻሻልና ከተማዋን የኢኮኖሚ ሞተር ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ዘርፎች አንዱ የሥራ ዕድል ፈጠራና የመሥሪያ ቦታዎችን ማቅረብ ነው። ከንቲባ አዳነች አቤቤ በቅርቡ ያስተላለፉት መልዕክት እንደሚያሳየው፣ የድህነታችን ቋጠሮ የሚፈታው ሁላችንም በርትተን ስንሠራ ብቻ ነው። ዕድሎች ሲመቻቹ በትጋት የማይጠቀም ትውልድ ካለ ለውጥ ማምጣት አይቻልም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በመንግሥትና በግል ጥረቶች በርካታ ዜጎች ወደ ሥራ ገብተው ሕይወታቸውን መለወጥ መጀመራቸው፣ ትጋትና ዕድል ሲገናኙ ተአምር መፍጠር እንደሚችሉ ትልቅ ማሳያ ነው።

ከትናንት በስቲያ ለ1 ሺህ 278 ኢንተርፕራይዞች የመሥሪያ ቦታዎችና ሼዶች ተለልፈዋል። በዚህም 3 ሺህ 889 አንቀሳቃሾች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ሆነዋል። የሚገርመው ግን የሼዶቹ ብዛት ብቻ ሳይሆን የተገነቡበት ፍጥነትና ጥራት ነው። በዚህ ዓመት ብቻ 10 ሺህ የሚደርሱ የመሥሪያ ቦታዎችና ሼዶች ተገንብተው የተላለፉ ሲሆን፣ ከትናንት በስቲያ የተላለፉት አብዛኛዎቹ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቀው ለአገልግሎት የበቁ ናቸው። ይህ የሚያሳየው መንግሥት ለሥራ ፈላጊው ያለውን ቁርጠኝነትና የልማት ሥራዎችን በምን ያህል ፍጥነትና ጥራት ማከናወን እንደሚቻል ትልቅ ትምህርት የሰጠ ክስተት ነው።

ድህነትን ለመርታት መንግሥት የመሥሪያ ቦታና ሥልጠና ማመቻቸቱ አንድ እርምጃ ቢሆንም፣ ዋናውና ወሳኙ ጉዳይ ግን የተጠቃሚዎች ወኔና ጥረት ነው። ከድህነት መላቀቅ የሚቻለው በተገኘው ዕድል እልህ ውስጥ ገብቶ ሌት ተቀን በመሥራት ብቻ ነው። ድህነትን የመቅበር ኃላፊነት በመንግሥት ትከሻ ላይ ብቻ የሚወድቅ ሳይሆን፣ የሁላችንንም የተቀናጀ ጥረትና የሥራ ባህል ለውጥን ይጠይቃል። ተደራጅተውና ሰልጥነው ወደ ሥራ የገቡ ዜጎች፣ መንግሥት የሰጣቸውን ይህን ወርቃማ ዕድል ተጠቅመው ራሳቸውንና ሀገራቸውን የመለወጥ አደራ አለባቸው።

ከትናንት በስቲያ የመሥሪያ ቦታ ያገኛችሁ ወጣቶችና ኢንተርፕራይዞች፣ ግባችሁ በልቶ ማደር ብቻ ሊሆን አይገባም። ከመንግሥት ያገኛችሁትን ድጋፍ እንደ መነሻ ተጠቅማችሁ፣ በትጋትና በታማኝነት በመሥራት የነገዎቹ ትላልቅ ኩባንያዎችና የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ለመሆን መቆም አለባችሁ። የተረከባችሁት ሼድ ነገ ወደ ግዙፍ ፋብሪካ፣ ዛሬ የፈጠራችሁት ጥቂት የሥራ ዕድል ነገ ወደ ሺዎች እንዲያድግ የሚጠበቀው ከእናንተ እልህና ጥረት ነው። ድህነት በትጋትና በእልህ ድል ይነሳል! የመስሪያ ቦታዎችና ሼዶች የተረከባችሁ ኢንተርፕራይዞች የተሰጣችሁን ዕድል ተጠቀሙ፣ ለሀገራችሁ ተስፋ ሁኑ። ምክንያቱም ነገ የሚገነባው ዛሬ በተሰጡ ዕድሎች ላይ በትጋት በሚፈስ ላብና ጥረት ነውና።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## የሀሳብ መስጫ ሳጥኖች ተከፍተው ይታዩ ይሆን?

**ሳሮን ከጊዮርጊስ**

የሀሳብ መስጫ ሳጥኖች በተለያዩ ተቋማት ተዘጋጅተው ይገኛሉ፡፡ ዋና ዓላማቸውም ተገልጋዩ ስላገኘው አገልግሎት በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ በነፃነት ሀሳቡን የሚሰጥበት ነው፡፡ እንደ እኔ አስተያየት፤ በሃሳብ መስጫ ሳጥኖች አማካኝነት የምንሰጠው ሀሳብ (አስተያየት) ገደብ የለሽ በመሆኑ፣ በአካል ተገኝቶ ሀሳብ (አስተያየት) ከመግለፅ አንፃር ነፃነቱ የሰፋ ነው፡፡

የሀሳብ መስጫ ሳጥኑን ተቋማት ሲያስቀምጡት አንድ ተገልጋይ ከቅጥር ግቢ ጀምሮ ተገልግሎ እስኪወጣ የሚሰማውን እና ያጋጠመውን መግለፅ እንዲችል ነው፡፡ እንዲህ ያለው አስተያየት ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግብረ መልስ ሆኖ ጠንካራውን እንዲያስቀጥልበት ድክመቱን ደግሞ እንዲያሻሽል እንደሚረዳው አምናለሁ፡፡

በነገራችን ላይ የሀሳብ መስጫ ሳጥንንን በአግባቡ በመጠቀም ረገድ እኛ ተገልጋዮች ላይም የሚስተዋል ችግር እንዳለ አይካድም፡፡ በሄድንበት ተቋም ጥሩ ያገለገለንን በግል ከማመስገን አለፍ ስንል እጃችንን ስናረዝም፣ በእኛም ችግር ይሁን በአገልጋዩ የአቅም ወይም የባህርይ ችግር ሲገጥም አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ እሰጥ አገባ መግባት ተገቢ አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም የሐሳብ መስጫ ሳጥንን በሁነኛ አማራጭነት ተጠቅመን በአግባቡ ሀሳባችንን መግለፅ ላይ ያለንን ልምድ ማጤን ይገባናል፡፡በአንፃሩ ተቋማት የተገልጋዩን አስተያየት በየጊዜው ሳጥኑን በመክፈት ግብረ መልስ ይሆን ዘንድ ጠቀሜታውን ታሳቢ በማድረግ ከፍቶ የመጠቀም ልምዱ ምን ያህል ነው?

የዛሬውን አስተያየት ለመፃፍ ያነሳሳኝ ዋና ምክንያት፤ ከተገልጋዩ የመጻፍ ልምድ ማነስ እና ፍላጎት አለመኖር በተለይም "ተከፍቶ አይነበብም" በሚል አስተሳሰብ የመነጨ እንደሆነ በተለያየ አጋጣሚ በጉዳዩ ዙሪያ ያወጋኋቸው ሰዎች ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡ በእርግጥ አብዛኛው ተቋማት የሀሳብ መስጫ ሳጥኑ የተሰራበት ቁስ እና የሀሳብ መስጫ ሳጥኖቹ ቶሎ የሚከፈቱ ባለመሆናቸው በፀሐይና በአቧራ መልካቸውን ለቀው መቀመጣቸው፣ በአንዳንድ ቦታ "ባይኖርስ" ያሰኛል፡፡

"በሀሳብ መስጫ ሳጥኑ ችግሮች ሲገጥሙ በግልፅ የሚመለከተውን በግልጸኝነት መንገር እየተቻለ ማንነታችንን በመሸፈን ሀሳብ እንሰጣለን፡፡ ይህን ተግባር የምናደርገው ድብቅነትን ስለምንሻ ነው በመሆኑም ተገቢ አይደለም" ሲል አንዱ ሀሳቡን አጋራን፡፡

ሌላው ሀሳብ ሰጪ ደግሞ፤ "ሀሳቡ ግልጸኝነት ይጎለዋል" በሚል ሳጥኑ ተከፍቶ የሚያውቅ አይመስለኝም። ሲል ሀሳቡን አንፀባርቋል፡፡ ነገር ግን ባለቤትስ አለው ወይ? የሚለው አብዛኛውን የሚያስማማ ይመስለኛል። እንደ እኔ ሀሳብ መስጫ ሳጥን ጠቀሜታው ቀላል አይመስለኝም። የተፃፈው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተያየት ተቋማት ትኩረት ቢሰጡት እላለሁ፡፡ ከሀሳቡም በመነሳት ራሳቸውን ቢመለከቱ ተገቢነት አለው፡፡ ተገልጋዩም "ወረቀቶቹን የሚያነባቸው የለም።" በሚል ድምዳሜ ሀሳብ ካለመስጠት ከመታቀብ ወይም በአገልግሎት መስጫ ቦታ ክርክር በመግጠም የአገልጋይን እና የተገልጋይን ጊዜ ከማጥፋት ተገቢ የሆነውን ሀሳብ፤ በሀሳብ መስጫ ሳጥን ብናስቀምጥ ጥቀሙ ለጋራ ነው እላለሁ፡፡


ADDIS MEDIA NETWORK
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ለፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ የተዘጋጀ

## ከአቧራ ወደ ዐሻራ፤ ከቆሻሻ ወደ ውብ መዳረሻ፤ ከቅርስ ወደ ቁርስ

- **የቱሪዝም ዘርፍ ልማት አቋማችን፣ ስኬቶችና ትልሞች**




### በቱሪዝም ዘርፍ ላይ የብልጽግና ፓርቲ ዕሳቤና አቋም

ብልጽግና ፓርቲ ቱሪዝምን እንደ ተራ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሳይሆን፣ የሀገር ግንባታ፣ የሰላም ማስፋፊያ፣ የብዝኃነትና የኅብረ ብሔራዊ አንድነት መገንቢያ መሣሪያ እንደሆነ ያያል። ኢትዮጵያ በታሪክ፣ ባሕል እና ተፈጥሮ ያላትን ባለጠግነት በተገቢው ሁኔታ ተጠቅመን እንዲያገለግል ቱሪዝምን ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች አንዱ አድርጎ ይቆጥረዋል።

ቱሪዝም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት፣ ሀገራዊ ገቢን ለማሳደግ እና ለዜጎች ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ዋና መሠረት እንደሆነ ብልጽግና ይገነዘባል። ብልጽግና የቱሪዝም ልማት በመንግሥትና በግል ዘርፍ ቅንጅትና ትብብር እንዲካሄድ መሀከለኛና ሚዛናዊ አቋምን ይከተላል።

በመደመር ዕሳቤ መሠረት፣ ቱሪዝም የጋራ ታሪካችንን የሚያሳይ፣ ዜጎችንና ሕዝብን የሚያቀራርብ ብሔራዊ ማንነትን የሚያጠናክር መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል አድርገናል።

### ባለፉት ዓመታት የሠራናቸው ሥራዎች

በባለፉት ዓመታት ቱሪዝምን ለማሳደግ በርካታ ተቋማዊና ዘላቂ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ በዚህም መሠረት፡-

- ለ16 ዓመታት ያልተሻሻለው የቱሪዝም ፖሊሲ በመሻሻሉ እና ተቋሙ በሚኒስቴር ደረጃ እንደገና እንዲደራጅ እና የቱሪዝም ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆን አድርገነዋል።
- የስብሰባ፣ የጉዞ፣ የኮንፍረንስ እና ኤግዚቢሽን ስትራቴጂ እና የመዳረሻ ልማት ስትራቴጂዎች ዘርፉን በአዲስ መልክ ለማደራጀት በሚያስችል አግባብ እንዲተገበሩ አድርገናል።
- የኢ-ቪዛ፣ ዲጂታል አገልግሎቶች እና የጉምሩክ ሂደቶችን በማሻሻል የቱሪስቶች ተደራሽነትን ማዘመን እና ማቀላጠፍ ተችሏል።
- እንደ "ገበታ ለሀገር"፣ "ገበታ ለሸገር"፤ "ገበታ ለትውልድ" እና "ኮሪደር ልማት" ያሉ ፕሮጀክቶች ውብ እና ድንቅ ሀብቶችን አስተሳስረው ለልማትና ለሀገር ገጽታ ግንባታ አገልግለዋል።
- እንደ እንጦጦ፣ ወንጪ፣ ሃላላ ኬላ፣ ኮይሻ እና ሌሎች መዳረሻዎች ተገንብተው ወደ ሥራ ገብተዋል።
- ሸገር፣ እንጦጦ፣ አንድነት እና በወዳጅነት ፓርኮች የኮሪደር ልማቶች እና የአዲስ አበባ ወንዝ ዳርቻ ልማቶች የከተማ ውበትን፣ ለሀገር ክብርን አበርክተዋል።

### የተከናወኑ ሥራዎች ያመጡት ተጨባጭ ውጤት

እነዚህ የተከናወኑ ሥራዎች በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ ሕይወት እና በሀገራዊ ምስል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

- ቱሪዝም የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ ኢትዮጵያዊነትን የምንገነባበት፣ የጋራ ቤታችንን የምናስውብበትና ዜጎችን በወንድማማችነትና በእህትማማችነት የምናስተሳስርበት ትልቅ የፖለቲካና ማኅበራዊ ፕሮጀክት ሆኖ እንዲያገለግል አድርገናል።
- ኢትዮጵያ በዓለም ቱሪዝም ድርጅት እንድትሸለም ከማስቻላችንም በላይ፣ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ሦስት ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስመዝገብ የታሪክ ክብረ-ወሰን እንድታስመዘግብ አድርጓታል።
- ቱሪዝም እንደ ብዝኃ-ዘርፍ የብልጽግና መሠረት መሆኑን በተግባር ያረጋገጠ ውጤት አስገኝቷል።
- በብሔር ብሔረሰቦች መካከል መተማመንና መቻቻል ተጠናክሯል።
- ከአቧራ ወደ ዐሻራ፣ ከቅርስ ወደ ቁርስ የተቀየረ የቱሪዝም ዕድገት ተመዝግቧል።
- እንደ ኮይሻ፣ ጎርጎራና ወንጪ ያሉ የሀገር ገጽታ ቀያሪ፣ የቱሪዝም ዕድገት ዘዋሪ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተተግብረዋል።
- ዓመታዊ የውጭ ቱሪስቶች ቁጥር ከ781 ሺህ ወደ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን በመስፈንጠር ከፍተኛ ዕድገት ተመዝግቧል።
- የቱሪዝም ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በከፍተኛ መጠን ጨምሯል።
- በሆቴል፣ በመጓጓዣ፣ በአስጎብኚ እና በንግድ ዘርፎች በሺዎች የሚቆጠሩ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል።
- በቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ተዳክሞ የነበረው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በግልጽ ተነቃቅቷል።
- ባሕላዊ እና ታሪካዊ ቅርሶቻችን በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) አማካይነት ዓለም አቀፍ እውቅና አግኝተዋል፤ በአንድ ዓመት ውስጥ 3 አዳዲስ ቅርሶችን በዩኔስኮ ማስመዝገብ ተችሏል።

### በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የምንሠራቸው ሥራዎችና የምናመጣው ውጤት

ብልጽግና ፓርቲ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ቱሪዝምን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ተዘጋጅቷል። የአምስት ዓመቱ ትልማችንም፡-

- ኢትዮጵያን የአፍሪካ ዋና የቱሪዝም መዳረሻ፤ በዓለም የተወደደችና የተመረጠች የቱሪዝም መዳረሻ እናደርጋለን።
- የውጭ ቱሪስት ብዛትን እስከ 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን እናደርሳለን።
- አዳዲስ የኢኮ ቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስፋፋት እናለማለን።
- ታሪካዊና ባሕላዊ ቅርሶችን በማደስ፣ በመጠበቅና በማዘመን ከፍ ባለ ደረጃ በማስተዋወቅ፣ የገቢ ምንጮችን እናሳድጋለን፤ እናስፋፋለንም።
- የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን እናበረታታለን።
- የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ፣ የውኃ እና የቴሌኮም መሠረተ ልማቶችን በማሻሻል እናስፋፋለን።
- ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የቱሪዝም ዘርፉን አገልግሎት እናዘምናለን።
- ዓለም አቀፍ የማስተዋወቂያ፣ የግንኙነትና ትሥሥር ሥራዎችን እናጠናክራለን።
- በሚሊዮኖች የሚቆጠር የሥራ ዕድል እንፈጥራለን።
- ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለተሻለ የኑሮ ደረጃ መሻሻል አስተዋጽዖ እናደርጋለን።
- ሀገራዊና ኅብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲጠናከር የሚያስችሉ ተግባራትን እናከናውናለን።

በአጠቃላይ፣ ብልጽግና ፓርቲ ቱሪዝምን ከኢኮኖሚ በላይ የሀገር ግንባታ እና የኅብረ ብሔራዊ አንድነት መገንቢያ መሣሪያ አድርጎ በማየት፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚታይ ለውጥ አምጥቷል። ወደፊትም ይህንን ዕድገት አጠናክሮ በማስቀጠል ኢትዮጵያን በዓለም የቱሪዝም ካርታ ላይ ከፍ ያለ ቦታ እንድትቆም እንሠራለን።

ፓርቲያችን ብልጽግና የጀመረውን ዕድገት አልቀን በማስቀጠል ኢትዮጵያን በዓለም ቱሪዝም ከፍ ያለ ቦታ ላይ እንድትቆም ለማድረግ እንሠራለን፤ ይህንንም በስኬት እንፈጽማለን። ምክንያቱም እኛ ሀገር የማበልጸግ ትልም ያለን፥ የጀመርነውን የምንጨርስ፣ ቃል የገባነውን በጥራትና በከፍታ የምንፈጽም ብልጽግናዎች ነን።

- **ብልጽግናን ይምረጡ!!!**
- **ብልጽግናን መምረጥ.... የኢትዮጵያን መታያ ሀብት መምረጥ ነው።**
- **ምልክታችን የስንዴ ነዶ ነው።**
- **የስንዴ ነዶ የመደመር፣ የትብብር እና የአንድነት ምልክት ነው።**
- **ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር!!!**

**ይህ ቦታ ለአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ እና ለአዲስ ትውልድ ፓርቲ ምርጫ ቅስቀሳ የተሰጠ ቢሆንም ፓርቲዎቹ የቅስቀሳ ጽሑፍ ባለማምጣታቸው ጋዜጣው ከዚህ በታች ያለውን የራሱን ጽሑፍ አስተናግዶበታል።**

## የመራጮች የግንዛቤ ትምህርት ለምን ያስፈልጋል?

### በስንታየሁ ምትኩ

በየትኛውም ምርጫ መሰራት ካለባቸው ጉዳዮች መካከል የመራጮችና የስነ ዜጋ ትምህርት መስጠት አንዱ ነው፡፡ መራጮች መብቶቻቸውን መጠቀም እንዲችሉ፣ የፖለቲካ ስርዓቱን እንዲረዱ፣ እንዴትና የት መምረጥ እንዳለባቸው እንዲረዱ ለማድረግ የመራጮች እና የዜጎች ትምህርት አስፈላጊ ናቸው። አንድ ምርጫ ስኬታማና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን መራጮች መብቶቻቸውንና ግዴታዎቻቸውን መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

የመራጮች ትምህርት ሲባል በአንድ ሀገር በሚካሄድ ምርጫ መራጮች በምርጫ አሰራርና ሂደት ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚሰራጩ መረጃዎችን፣ ቁሳቁሶችና ፕሮግራሞችን ያካትታል፡፡ የመምረጥ ህጋዊ መብት ያለው ማን እንደሆነ፣ የት መምረጥና ለመራጭነት መመዝገብ እንደሚቻል፣ ምን ዓይነት ምርጫዎች እየተካሄዱ እንደሆነ፤ የት፣ መቼ እና እንዴት ድምፅ መስጠት እንደሚቻል፣ ዕጩዎቹ እነማን እንደሆኑ እና ቅሬታዎችን እንዴት ማቅረብ ይቻላል የሚሉትን ይይዛል።

የመራጮች ትምህርት ዓላማ መረጃን ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ እና ዝግጁ ማድረግ ነው። የመራጮች ትምህርት ዘመቻዎች መላውን መራጭ ሕዝብ ለማዳረስ መጣር ይኖርባቸዋል። ይህንን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ደግሞ ከተለመዱት መራጮች በተጨማሪ የተገለሉና በችግር ውስጥ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማግኘት ያስፈልጋል።

በምርጫ ዙሪያ መረጃ በማቅረብ የሚታወቀው Mailitinneveda.com ገፀ ድር "The importance of voter education in a democracy" በሚል ርዕስ በፈረንጆች አቆጣጠር በ2025 ያወጣው ጽሑፍ እንደሚያመላክተው፣ የመራጮች ትምህርት ዜጎች በምርጫ ወቅት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መስጠት እንዲችሉ ያስችላል። የተማሩ መራጮች መብታቸውን፣ የምርጫ ሂደቱን፣ ምርጫቸው የሚያስከትለውን ተፅዕኖና ተጠያቂነት መረዳት ይችላሉ፡፡ የአሜሪካ ሴንሰስ ቢሮ ሪፖርት እንደሚያመላክተው በሀገሪቱ በፈረንጆች አቆጣጠር በ2020 በተካሄደው ምርጫ ሰፊ የመራጭ ትምህርት በሰጡ ክልሎች የመራጮች ተሳትፎ በ10 በመቶ አድጓል፡፡

የምርጫ ትምህርት መራጮች ስለ ምርጫው ሂደት፣ ስለ እጩዎች እና የተለያዩ ጉዳዮች ትክክለኛ መረጃ እንዲታጠቁ በማድረግ በምርጫ ወቅት የሚያጋጥመውን ሀሰተኛ መረጃ ለመከላከል ያስችላል፡፡ መራጮች በቂ መረጃ ሲኖራቸው በሀሰተኛ ትርክቶች፣ አሳሳች መረጃዎች፣ ያልተገቡ ጥያቄዎች የመታለል እድላቸው ዝቅተኛ ይሆናል።

በኢትዮጵያ የምርጫ ህግና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ባወጣው የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 4/2012 መሰረት፣ የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡ ቦርዱ መራጮች በቂ ምርጫ ነክ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስልት በመቀየስና የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም የመራጮች ትምህርት መስጠት እንዲችሉ ህጋዊ ሰውነት ላላቸው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የትምህርት ተቋማት፤ የማስተማር ፈቃድ ይሰጣል። ማንኛውም ሰው ያለቦርዱ ፈቃድ የመራጮች ትምህርትና መረጃ መስጠት አይችልም። ለ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ በመራጮች ትምህርት ላይ ለሚሠማሩ 169 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዕውቅና መስጠቱን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከሳምንት በፊት በይፋዊ የማህበራዊ ትስስር ገፁ (ፌስቡክ) አሳውቋል፡፡ እውቅና ያገኙ የሲቪክ ማህበራትም መራጮች በዕውቀት ላይ ተመስርተው ድምፅ እንዲሰጡ የሚያስችላቸውን ትምህርት መስጠት እንደሚገባቸው ቦርዱ አስታውቋል፡፡

የመረጃ ምንጭ፡- www.un.org/womenwatch/osagi/wps/publication/Chapter5.htm፣mailitinnevada.com እና የምርጫ ቦርድ መረጃ

# የዜጎቿን ... ከገጽ 1 የዞረ

in People, The Economics of Population Quality" በተሰኘ መጽሐፋቸው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ባሳለፍነው ሳምንት (ረቡዕ ሚያዝያ 28 ቀን 2018 ዓ.ም) ለ1 ሺህ 278 ኢንተርፕራይዞች መስሪያ ቦታዎችና ሼዶችን ባስተላለፉበት ወቅት ያነሷቸውም ነጥቦች ከፕሮፌሰሩ ጥልቅ ሀሳብ ጋር የሚስማሙ ናቸው፡፡ እነዚህ መስሪያ ቦታዎች እና ሼዶች 3 ሺህ 889 አንቀሳቃሾችን ተጠቃሚ ያደረጉ ናቸው፡፡

እንደ ከንቲባዋ ገለፃ፣ የድህነታችን ቋጠሮ የሚፈታው ሁላችንም በርትተን ስንሰራ ነው፡፡ በከተማዋ የሥራ ባህል እንዲቀየር ለሥራ የሚተጋ ትውልድ ለመፍጠር፣ በግል ጥረት ራስን መቻል እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የማያቋርጥ ሥራ እየተሰራ ነው፡፡ ለአብነትም በዚህ ዓመት 10 ሺህ የሚደርሱ መስሪያ ቦታዎችና ሼዶች በፍጥነትና በጥራት ተገንብተው ተላልፈዋል፤ አሁን የተላለፉትም አብዛኛዎቹ ከ3 ወር ባልበለጠ ጊዜ የተገነቡ ናቸው፡፡

ችግሮችን ብቻ በማውራት ከድህነት መላቀቅ እንደማይቻል የገለፁት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ ከድህነት መላቀቅ የሚቻለው በተገኘው እድል እልህ ውስጥ ገብተን ስንሰራ ብቻ ነው። ድህነት የሚፈታው በመንግሥት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም የሁላችንንም ጥረት እንደሚጠይቅም ተናግረዋል፡፡ የመስሪያ ቦታ ያገኙ ወጣቶችም በልቶ ከማደር ባሻገር፣ ከመንግሥት የተደረገላቸውን ድጋፍ ተጠቅመው እልህ ውስጥ ገብቶ በመስራት የትልልቅ ኩባንያ ባለቤት በመሆን ለሀገር እድገትም የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማበርከት እንዳለባቸውም መክረዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ እና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪት አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ሰብሀዲን ሱልጣን ለአዲስ ልሳን ጋዜጣ እንደተናገሩት የቢሮው ዓላማ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ መስኮች የዳበሩና ጠንካራ ዜጎችን ማፍራት ነው፡፡

ይህንንም መሰረት በማድረግ ከሀገራዊ ለውጡ ወይም ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ ለ2 ሚሊዮን 432 ሺህ 353 ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ እነዚህ የሥራ ዕድሎች በዋናነት የኢንዱስትሪ፣ የግብርና እና የአገልግሎት ዘርፎች ስብጥርን ጠብቆ የተከናወኑ ናቸው፡፡ ከዚህ ቁጥር ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ (1ሚሊዮን 986 ሺህ 355) የሚሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡

በዚህ ዓመትም የሥራ ፈጠራ ተግባሩ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፣ እስከ 10ኛው ወር ባሉት ጊዜያት ውስጥ ብቻ 350 ሺህ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ከተያዘው ዕቅድ 359 ሺህ 310 ወይም የዕቅዱን 110 በመቶ ያህል ማሳካት ተችሏል፡፡

ይህም በከተማ ግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች የተፈጠረ ዕድል ነው፡፡ የሴቶችም ተጠቃሚነት ወደ 53 ነጥብ 1 በመቶ ነው፡፡ ከተፈጠረው የሥራ ዕድልም 49 ነጥብ 7 በመቶው በቅጥር እንዲሁም 50 ነጥብ 3 በመቶው በመደበኛ በመደራጀት የተፈጠረ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የመስሪያ ቦታዎችን ለከተማዋ ነዋሪዎች ባስተላለፉበት ወቅት

በተለይም የሥራ ባህል እንዲለወጥ እና ምርታማነት እንዲጨምር ከማድረግ አንፃር ከብሎክ አደረጃጀት ጀምሮ በየአስራ አምስት ቀኑ ማህበረሰብ አቀፍ ውይይት እንዲካሄድ እየተደረገ ነው። ይህም ከአዳራሽ ውይይት በመውጣት ማህበረሰቡን በራሱ ችግር ላይ ውይይት እንዲያደርግ ተሰርቷል፡፡ በዚህ የወጣቱን አመለካከትና የአስተሳሰብ ብሎም ሥራ ማመረጥ ላይ ለውጥ ማምጣት ተችሏል። ለዚህም በዓመት የያዝነውን ዕቅድ በእነዚህ አስር ወራት ማከናወን መቻላችን በዘርፉ እየተሰራ ያለውን ተጨባጭ ለውጥ የሚጠቁም ነው ብለዋል፡፡

በበጀት አመቱ 400 ሺህ ሥራ ፈላጊዎች እንደተመዘገቡ የጠቆሙት አቶ ሰብሃዲን፣ እስካሁን ከ359 ሺህ በላይ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ ይህንን ዕድል መፍጠር የተቻለውም ከከፍተኛ አመራሩ ጀምሮ የሥራ ዕድል ፈጠራን ለዜጎች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ዋና አጀንዳ አድርጎ በመንቀሳቀሱ ነው፡፡ በተለይም የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራውን አስመልክቶ በየሳምንቱ ጠንካራ ድጋፍ፣ ግምገማና ክትትል በማድረጋቸው የመጣ ውጤት ስለመሆኑም ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ሰብሀዲን ገለፃ፣ በተጨማሪም የስራ ዕድል አማራጮችን ለማስፋት የተለያዩ መርሃ ግብሮች ተከናውነዋል። ለአብነትም በአንድ ጀምበር 30 ሺህ የሥራ ዕድል የመፍጠር መርሃ ግብር አንዱ ነው። በዚህ ተነሳሽነትም ባለድርሻ አካላቶችን በማዋቀር እና በመደራጀት ብቻ በተለይም በከተማዋ ውስጥ እየተሰሩ ባሉ ልማቶች ወጣቶች ከተማቸውን ንፁህ እና ውብ እያደረጉ በሥራ ዕድሉም እንዲጠቀሙ የማድረግ ሥራ ተከናውኗል፡፡

በኮንስትራክሽን ዘርፍም አሁን በከተማዋ የምናያቸው መንገዶች፣ ቤቶች እና መሰል ታላላቅ ልማቶች በመዲናዋ ወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ጭምር የተገነቡ ናቸው፡፡ በየክፍለ ከተማውም አሰሪና ሠራተኞችን በማገናኘት እና የሥራ አውደ ርዕይ በማድረግ በቀን ሁለት ሁለት ሺህ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በማዕከል ደረጃም እራሱን የቻለ በየቀኑ ከ2 ሺህ በላይ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ በመደረጉ እቅዶችን ስኬታማ እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡

በሥራ ዕድል ፈጠራው የሚከናወኑ ተግባራትን ተአማኒ ለማድረግም የሥራ አጦች ምዝገባ በድጅታል መንገድ ተደርጓል፡፡ ለተመዝጋቢዎቹ የሥራ ዕድል ሲፈጠርላቸውም ለማን? የትና እንዴት? የሚሉ ዝርዝር መረጃዎች በድጅታል መንገድ በግልፅ ይያዛሉ፡፡ ይህም በሁለት ቦታ መጠቀምን እንዲሁም ሥራ እድሉ ሳይፈጠርለት ተፈጠረ የሚሉ የተሳሳቱ ሪፖርቶችን ከማስቀረት ጋር በተያያዘ 'ጆብ ማኔጅመንት ሲስተም' Job management system (JMS) በተሰኘ የዲጅታል አሠራር አማካኝነት በትኩረት እየተሰራበት ነው፡፡

እንደ ከተማ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልምት ሥራዎች ለወጣቱ ትልቅ የሥራ ዕድልን እየፈጠሩ ነው፡፡ ለአብነትም ከኮሪደር ልማቱ ጋር ተያያዞ ፓርኪንግም ሆነ ተራ የማስከበር ሥራዎች ዘምነዋል። ይህም በየአካባቢው ላሉ ወጣቶች በአቅራቢያቸው የሥራ ዕድልን መፍጠር አስችሏል፡፡

በሲኤምሲ አካባቢ በፓርኪንግ አገልግሎት ዘርፍ ተሰማርቶ ያገኘነው ወጣት አስፋው ይስማው በኮሪደር ልማቱ መንገዶቹ ምቹ በመሆናቸውና ለፓርኪንግ አገልግሎት የለሙ ስፍራዎችም በብዛት በመኖራቸው እሱና ጓደኞቹ በአቅራቢያቸው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ መሆናቸውን አጫውቶናል፡፡

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በ2024 ይፋ ያደረገውን ጥናት በዋቢነት የጠቀሱት አቶ ሰብሀዲን በዚህ መረጃ መሰረት የከተማዋ የሥራ አጥ ምጣኔ 22 ነጥብ 8 በመቶ ያህል ነው፡፡ በመሆኑም እንደ ከተማ በ2030 ዓ.ም የሥራ አጥ ቁጥሩን ወደ አንድ አሀዝ ለማውረድ እየተሰራ ነው፡፡ ለዚህም በየዓመቱ በትንሹ 300 ሺህ ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር አለብን፡፡ እየተመዘገበ ያለውም ተጨባጭ ውጤት ይህ እውን እንደሚሆን አመላካች ነው፡፡

በተለምዶ የለቡ ቀለበት መንገድ ድልድይ ስር ያለውን ቦታ በማልማት እና በማስዋብ የሥራ እድል ከተፈጠረላቸው መካከል ወጣት ሀና አድማሴ አንዷ ናት። ወጣቷ እንደምትለው በኮሪደር ልማቱ ምክንያት በርካታ ስፍራዎች ወደ ውብ መናፈሻና መዝናኛዎች ተለውጠው እሷን ጨምሮ ለብዙ ወጣቶች የሥራ ዕድልን መፍጠር ችለዋል፡፡

እንደ ቢሮው መረጃ፣ በ5 ዓመቱ ስትራቴጂክ እቅድ ክንውን መሠረት በ2013 ዓ.ም ለ345 ሺህ 62፣ በ2014 ዓ.ም ለ421 ሺህ 850፣ በ2015 ዓ.ም ለ416 ሺህ 999፣ በ2016 ዓ.ም ለ291 ሺህ 577 እንዲሁም በ2017 ዓ.ም ለ366 ሺህ 44 ዜጎች የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡

ከዚህ ውስጥ እስከ 2015 ዓ.ም ያለው ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ሲሆን፤ የቀሩት ሁለት ዓመታት ደግሞ ቋሚ የሥራ ዕድሎች ናቸው፡፡ በእነዚህ አምስት ዓመታትም በጥቅሉ 1 ሚሊዮን 841 ሺህ 532 የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል፡፡ በሥራ ዕድል ፈጠራው ከሀገራዊ ለውጡ ጀምሮ ማለትም ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ ለ2 ሚሊዮን 432 ሺህ 353 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት በአዲስ አበባ ከተማ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከናወኑ ያሉ ልማቶች የከተማዋን ውበትና ዘመናዊነት ከፍ ከማድረጋቸው ባሻገር በትውልዱ ዘንድ አዲስ የሥራ ባህልን እያስተዋወቁ እና ሰፋፊ የስራ ዕድል አማራጮችን እየፈጠሩ ነው፡፡

በየዓመቱም እየተፈጠሩ ያሉ የሥራ ዕድሎች በእርግጥም ከተማዋ በአዲስ የሥራ ባህል የተሻለ ለውጥ እያመጣች እና ለበርካቶችም ኢኮኖሚያዊ አቅምን እየፈጠረችና አስተማማኝ ዕድገትን እየገነባች መሆኑን የሚጠቁም እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

ይህም ለውጥ ያሉንን ፀጋዎች በሚገባ መለየትና መጠቀም ከቻልን ለበርካቶች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደምንችል የሚያመላክትና ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ውጤት የሚያመጣ ነው፡፡ ወጣቱ የሥራ ዕድል አገኘ ማለት ኑሮውን ከማሻሻሉ ባሻገር በምርትና ምርታማነት ላይ ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል፡፡ የሀገርንም ዕድገት በፅኑ መሠረት ላይ ለመገንባት ያግዛል ብለዋል ተባባሪ ፕሮፌሰር ይንገስ አለሙ (ዶ/ር)፡፡

# ለወላጅ ... ከገጽ 1 የዞረ

አድራጎት ስራ ሳይሆን፣ የሀገርን ህልውና የማረጋገጥ ስትራቴጂያዊ ኢንቨስትመንት ነው ማለት ይቻላል። ሳይንሳዊ ግኝቶች እንደሚነግሩን፣ የአንድ ሰው አዕምሮ እድገት 90 በመቶው የሚጠናቀቀው ገና በለጋነት ዕድሜ ነው። ይህ ማለት የነገው ሳይንቲስት፣ መሐንዲስና መሪ ጥራት የሚወሰነው ዛሬ ላይ ለህጻናቱ በምናቀርበው ምግብ፣ ፍቅርና ጥበቃ ልክ ነው ማለት ነው።


የኖቤል ተሸላሚው ኢኮኖሚስት ጄምስ ሄክማን እንደሚሉት፣ በቅድመ መደበኛ የህጻናት እንክብካቤ ላይ የሚወጣ እያንዳንዱ 1 ዶላር፣ ለሀገር እስከ 13 ዶላር የሚደርስ ትርፍ ያስገኛል። ይህ ትርፍ የሚመጣው የወደፊት የወንጀል ተሳትፎን በመቀነስ፣ የጤና ወጪን በመቆጠብና ከፍተኛ ምርታማነትን በመፍጠር ነው። በአንጻሩ በለጋነት ዕድሜያቸው ተገቢውን ክትትልና የተመጣጠነ ምግብ የማያገኙ ህጻናት፣ በጎልማሳነት ዘመናቸው በበሽታ የመያዝ እድላቸው ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ፣ በስራ ዓለም ያላቸው ተወዳዳሪነት በ25 በመቶ ዝቅ ይላል። ስለዚህ የልጆች እንክብካቤ የሰብዓዊነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሀገርን የኢኮኖሚ አቅጣጫ የሚወስን የሂሳብ ስሌት ነው።

የስነ-ልቦና ምሁራን እንደሚሞግቱት፣ የሰው ልጅ ስብዕና መሰረት የሚጣለው በአዳጊነት ወቅት ነው። አንድ ህፃን በቤተሰቡና በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያገኘው ደህንነት፣ ነገ ለሀገሩ የሚታመንና ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ እንዲሆን ያደርገዋል። ምሁራኑም "ቁስን ለመጠገን ቀላል ነው፣ የተሰበረ ስብዕናን መጠገን ግን ትውልድን ይፈጃል" የሚሉትም ለዚሁ ነው። የትምህርት ባለሙያዎችም ቢሆኑ፣ ትምህርት ቤት መሄድ ብቻውን በቂ እንዳልሆነና ጥራት ያለው የቅድመ መደበኛ ክብካቤ ለፈጠራና ለችግር ፈቺነት ቁልፍ መሆኑን ያስረዳሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ9 ወራት የስራ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያሳየው ከተማዋ ለህጻናት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች መሆኑን ነው። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ሪፖርቱን ለከተማዋ ምክር ቤት ባቀረቡበት ወቅት እንደገለፁት፣ በቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ህጻናት ቦርቀው የሚጫወቱባቸው ከ5 ሺህ በላይ የልጆች መጫወቻ፣ እንክብካቤ የሚያገኙበት ከ1 ሺህ በላይ የህጻናት ማቆያዎች ተገንብተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ህጻናት ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፊት ተገቢው የህይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው፣ ከፅንስ ጀምሮ እስከ 6 ዓመት እድገታቸው የተስተካከለ እንዲሆን በቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ ሆነዋል። ወላጆችና አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን የሚያውሉበት ቦታ እንዳይቸገሩ፣ ልጆቻቸው እንክብካቤ የሚያገኙበት ዴይ ኬሮች (የህፃናት መቆያ ማዕከላት) ተገንብተው በርካታ ወላጆችና ህጻናት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤት መረጃ እንደሚያሳየው ቤት ለቤት በመሄድ ለህፃናት እና ለወላጆች


ፎቶ- ከገፀ ድር
በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ተገንብተው ወደ አገልግሎት ከገቡ የህጻናት መዋያ ማዕከላት አንዱ

የቅርብ ምክርና ድጋፍ የሚሰጡ 5 ሺህ ባለሙያዎች ተሰማርተዋል፡፡

ለብዙ ዓመታት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የአዲስ አበባ እናቶች ትልቁ ጭንቀት "ወደ ስራ ስወጣ ልጄን የት አስቀምጣለሁ?" የሚል ነበር። ዛሬ ግን ይህ ስጋት በከተማዋ ሰፈሮች ውስጥ በታነጹት ከ1 ሺህ በላይ ዘመናዊ የህፃናት መዋያ ማዕከላት ተቀይሯል። እነዚህ ማዕከላት ቀደም ሲል ለግል ትምህርት ቤቶች ብቻ ተከልሎ የነበረውን ጥራት ያለው የቅድመ መደበኛ እንክብካቤ ወደ ሁሉም ህዝብ ደጃፍ አምጥተውታል። ማዕከላቱ እናቶች በሙሉ ልብ ወደ ስራቸው እንዲሰማሩና የኢኮኖሚ አቅማቸውን እንዲገነቡ የፈጠሩላቸው ዕድል፣ በቤት ውስጥ ታፍነው የነበሩ ህልሞችን ዳግም እንዲያብቡ አድርጓል።

ህፃናቱ በእነዚህ ማዕከላት ውስጥ የሚያገኟቸው የጨዋታ ቁሳቁሶች፣ ንጹህ የመኝታ ክፍሎችና የተመጣጠነ ምግብ የአዕምሯቸውን እድገት በከፍተኛ ሁኔታ እያነቃቃው ይገኛል። "በለጋነት የተዘራ በሽምግልና ይታጨዳል" እንደሚባለው፣ አዳጊዎቹ በእነዚህ ማዕከላት ውስጥ የሚያሳልፉት እያንዳንዱ ሰዓት ለወደፊት የትምህርት ህይወታቸውና ለማህበራዊ ግንኙነታቸው ጥንካሬ መሰረት እየጣለ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የዘርፉ አስተባባሪ አቶ ጥላዬ ዘውዴ የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም መዲናዋ ህጻናትን ለማሳደግ ምቹ አፍሪካዊት ከተማ እንድትሆን በከንቲባ አዳነች አቤቤ የተቀመጠውን ሌጋሲ ስኬታማ ለማድረግ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ፕሮግራም መሆኑን ይጠቁማሉ። በትምህርት ሴክተሩ ፕሮግራሙ በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆን የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በከፍተኛ በጀት ግብዓት ከማቅረብ ጀምሮ በጫወታ የማስተማር ስነ ዘዴ ተግባራዊ አድርገው ሞዴል እንዲሆኑ እየተሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የእነዚህ ማዕከላት ግንባታ በከተማዋ ነዋሪዎች መካከል የነበረውን የማህበራዊ ልዩነት ድልድይ እየናደው ይገኛል። አንድ አነስተኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ የተገኘ ህፃን፣ በላቀ ደረጃ በታነጸና በግብዓት በተሟላ ማዕከል ውስጥ የመማርና የመጫወት ዕድል ማግኘቱ፣ ኢትዮጵያን በእኩልነት መሰረት ላይ ለመገንባት የሚደረግ ትልቅ ጉዞ ነው። ማዕከላቱ የህፃናቱን የጤና ክትትልና የስነ-ልቦና ደህንነት ጭምር ታሳቢ ያደረጉ በመሆናቸው፣ ከተማዋን "ለህፃናት የምትመች ከተማ" ለማድረግ ለተያዘው ግብ እንደ ትልቅ ሞተር እያገለገሉ ነው። በየሰፈሩ የሚሰሙት የህፃናት የደስታ ድምጾች፣ አዲስ አበባ ለትውልድ ግንባታ የከፈለችው መስዋዕትነት ፍሬ እያፈራ መሆኑን በየቀኑ ይመሰክራሉ።

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆች እንደሚያስረዱት ልጆቻቸውን የሚተውበት አስተማማኝ ስፍራ በማጣታቸው፣ አቅማቸው እየፈቀደ ወደ ስራ ከመሰማራት ታቅበው ወይንም ልጆቻቸውን ለከፋ አደጋ በሚያጋልጥ መልኩ ዘግተውባቸው ለመውጣት ይገደዱ ነበር። ዛሬ ግን እነዚህ ከ1 ሺህ በላይ ማዕከላት የወላጆችን የልብ ስጋት አስወግደዋል። አንዲት እናት ልጇን በባለሙያዎች እጅ፣ በተሟላ ምግብና በንጹህ ስፍራ መተው መቻሏ፣ በሙሉ ትኩረትና አቅም ወደ ስራ ዓለም እንድትሰማራ መንገዱን ከፍቶላታል።

"ቀኑ እስኪመሽ ድረስ ልቤ እቤት ነበር፤ ዛሬ ግን ልቤም ስራዬም አንድ ሆኗል" የሚለው የበርካታ እናቶች ምስክርነት የማዕከላቱን ፋይዳ በግልጽ ያሳያል። በጉለሌ ክፍል ከተማ በሚገኘው ማዕከል የመርሃ ግብሩ ተጠቃሚ የሆኑት ወይዘሮ አልማዝ አያሌው እንደሚናገሩት፣ ቀደም ሲል ለግል መዋያ የሚከፈል አቅም የማይፈቅደው ክፍያ ወይንም ልጆችን በሰው እጅ ጥሎ የመሄድ ስጋት የሁልጊዜ ስቃያቸው ነበር። ዛሬ ግን በማዕከሉ የሚሰጠው እንክብካቤ ከቤትም በላይ እንደሆነ ይመሰክራሉ። "ልጄ እዚህ ማዕከል መግባት ከጀመረች በኋላ ንግግሯ ተስተካክሏል፣ ስርዓት ተምራለች፤ እኔም ልጄ ተርባ ይሆን? ተጎድታ ይሆን? የሚል ስጋት ስለሌለኝ በሙሉ አቅሜ ስራዬን እሰራለሁ" የሚሉት ወይዘሮ አልማዝ ማዕከሉ ለቤተሰባቸው የፈጠረውን ሰላም ይገልጻሉ።

ይህ ለውጥ በቤተሰብ ገቢ ላይ የሚያመጣው ጭማሪ ብቻ ሳይሆን፣ እናቶች በራሳቸው እንዲተማመኑ እና በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደረገ ትልቅ ማህበራዊ ስኬት ነው። በወላጆች ፊት ላይ የሚታየው እፎይታ እና ለነገ የሚሰንቁት ተስፋ፣ የማዕከላቱ ትልቁና የማይታየው ትርፍ ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያገኙት ነፃ የጤና ክትትልና የተመጣጠነ ምግብ፣ በኢኮኖሚያቸው ላይ ያመጣውን እፎይታ እንደ ትልቅ በረከት ይቆጥሩታል። እነዚህ ምስክርነቶች እንደሚያረጋግጡት፣ ማዕከላቱ ህንፃዎች ብቻ ሳይሆኑ የሺዎችን ኑሮ የቀየሩ የደህንነት መጠለያዎች መሆናቸውን ነው።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ "ለህፃናት የምናደርገው እንክብካቤ የከተማዋን የወደፊት እጣ ፈንታ ይወስናል" የሚል ጥልቅ እምነት አላቸው። ይህንን ራዕይ በተግባር ለመተርጎም፣ አስተዳደራቸው የልጅነት ልማት ስትራቴጂ በይፋ ሲያስጀምር፣ ከንቲባዋ "ህፃናት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የሚያገኙት ፍቅር፣ ምግብና ትምህርት የነገ ማንነታቸውን ይቀርጻል፤ ስለዚህ ለልጆች ኢንቨስት ማድረግ ለነገዋ ጠንካራ ኢትዮጵያ መሰረት መጣል ነው" በማለት ተናግረዋል። ይህ ንግግራቸው ከተማዋን ለህፃናት ምቹ የማድረግ ስራ በፖለቲካዊ ቁርጠኝነት የታጀበ መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ የሚታዩት የህፃናት መጫወቻ ፓርኮች፣ የጤና ክትትል ማዕከላትና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦቶች የዚሁ ታሪካዊ ንግግር ፍሬዎች ናቸው።

ይህንንም ተከትሎ አዲስ አበባ "አዲስ አፍሪካ ቀዳማይ ልጅነት ጉባኤ" የተሰኘውን የመጀመሪያውን አህጉራዊ መድረክ ከግንቦት 3 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ ለሦስት ቀናት እንድታስተናግድ ተምርጣለች። ጉባኤው "አፍሪካ በቀዳማይ ልጅነት ሥርዓት ለውጥ የግንባር ቀደምትነት ሚና" በሚል መሪ ቃል የሚካሄድ ሲሆን፣ 19 ሀገራትና ከ350 በላይ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ይሳተፉበታል ተብሏል።

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ማዕከል ዋና ስራ አስፈፃሚ ከበደ ወርቁ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በዚህ በየሁለት ዓመቱ በሚካሄድ መድረኩ ላይ አዲስ አበባ ባለፉት ዓመታት በዘርፉ ያከናወነቻቸውን ስኬታማ ተግባራት ለዓለም የምታሳይበት ይሆናል። በተለይም የእናቶችና ሕፃናት ጤና ጥበቃ፣ የቅድመ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት፣ የሕፃናት ማቆያ አገልግሎት ጥራት እና ለሕፃናት ምቹ የመጫወቻ ስፍራዎች ግንባታ በዋናነት በተሞክሮነት ይቀርባሉ ተብሏል፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባካሄደው ጉባኤ፡-

- **በአሁኑ ወቅት በተለያዩ አማራጮች 165 ሺህ 903 ቤቶች በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ፤ በወቅቱ እንዲጠናቀቁም የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑ ተጠቁሟል፤**
- **ምክር ቤቱ ለ2018 ዓ.ም በጀት አመት ተጨማሪ 9 ነጥብ 94 ቢሊዮን ብር በጀት አጽድቋል፤**

**በጊዜው አማረና ስንታየሁ ምትኩ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ በሰጡበት ወቅት

በትናንትናው እለት በተካሄደው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የስራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ ከምክር ቤቱ አባላት የተለያዩ አስተያየት እና ጥያቄዎች ተነስተዋል፡፡ የምክር ቤት አባላት ከህዝብ ጋር በነበራቸው መድረክ ከቀረቡና በምክር ቤቱ ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል የትራንስፖርት፣ የመኖሪ ቤት አቅርቦት፣ የኑሮ ውድነት፣ ጤና፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎች፣ የመብራት አገልግሎት አሰጣጥ፣ የሙስናና ተጠያቂነት እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ይገኙበታል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም ለተነሱ ለጥያቄዎችና አስተያየቶች የተሰጡ ምላሾችን እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## የመኖሪያ ቤት አቅርቦት

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በሰጡት ምላሽ በከተማዋ የመኖሪያ ቤት ፍላጎቱ ሰፊ እንደሆነና አቅርቦቱ ከፍላጎቱ አኳያ የሚመጣጠን እንዳልሆነ አንስተው፣ የቤት ፍላጎትን ለማቃለል ስትራቴጂካዊ በሆነ መንገድ አቅርቦትን ለመጨመር እየተሰራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት 480 ሺህ ቤቶችን መገንባት የተቻለ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 139 ሺህ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው ለነዋሪዎች ተላልፈዋል። 46 ሺህ ቤቶችን በመገንባት የተለያየ ማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ፣ በተጎሳቆሉ ቤቶች ለሚኖሩ ዜጎችና ለልማት ተነሺዎች ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ ሌሎችንም ቤቶች በመገንባት በኪራይ መስጠት እንደተቻለ ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም በከተማዋ በመንግስት በጀት 50 ሺህ፤ በመንግስትና የግል አጋርነት 55 ሺህ በድምሩ 105 ሺህ ቤቶች ግንባታቸው ተጀምሮ እየተከናወኑ እንደሚገኙ ያነሱት ከንቲባዋ፣ የግንባታ አፈጻጸማቸውም ከ40 በመቶ እስከ 90 በመቶ የደረሱ መሆናቸውን ገልጸዋል። እነዚህ ቤቶችም ቅድሚያ የሚሰጡት ቁጠባቸውን ላሟሉ ሲሆን፤ ቆጣቢዎች ቤቱን ሲረከቡ አሁን ያለውን የቤት ዋጋ ታሳቢ በማድረግ መቆጠብ እንደሚጠበቅባቸው አመላክተዋል፡፡

በተጨማሪም በማህበር ቤት በ2018 ዓ.ም በ119 ማህበራት 13 ሺህ 630 ቤቶች ግንባታ ተጀምሯል፡፡ ለእነዚህ ቤቶች መንግስት መሬትና መሰረተ ልማት በነጻ አቅርቧል፡፡ የመምህራን ቤቶች ጋር በተያያዘም ከ630 በላይ ቤቶች ወደ ግንባታ የገቡ ሲሆን የተቀሩትም ግንባታ ለመጀመር በዝግጅት ላይ እንደሚገኙ ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡

በሪል እስቴት፣ አፓርትመንትና መሰል ደግሞ 32 ሺህ 73 ቤቶች እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ በግለሰብ ደረጃ 20 ሺህ ቤቶች በመገንባት ላይ ናቸው፡፡ በጥቅሉ በአሁኑ ወቅት 165 ሺህ 903 ቤቶች በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በወቅቱ እንዲጠናቀቁም በከተማ አስተዳደሩ የቅርብ ክትትል እየተደረገ ነው፡፡ በበጎ አድራጎት እና ለኪራይ ቤት ከሚሰሩት ውጪ ያሉት ቤቶች ለቆጣቢዎች በቅድሚያ እንደሚተላለፉ ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡

በሚቀጥሉት የምርጫ ዘመን መንግስት ድምፅ አግኝቶ የሚቀጥል ከሆነ በየዓመቱ 100 ሺህ ቤቶችን እየገነባ እንደሚሄድ ጠቅሰዋል፡፡ እስከ አሁን በተሰራው ስራ የሪል እስቴት ቤቶች ሽያጭ ገበያ ላይ መረጋጋት እንደሚታይም አያይዘው አንስተዋል፡፡

## የኑሮ ውድነት

ከኑሮ ውድነት ጋር በተያያዘ ለተነሳው ጥያቄም ከንቲባ አዳነች አቤቤ በሰጡት ምላሽ፤ በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ምክንያት ያጋጠመው የኑሮ ውድነት እንዳይባባስ መንግስት እየሰራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡ የምርት አቅርቦትን በመጨመርና ተኪ ምርቶችን በማሳደግ እየተሰራ ነው፡፡ ምርቶች በቀላሉ ሸማቹ ጋር እንዲደርሱ የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር ረገድ የተሳካ ስራ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት በከተማዋ በአምስቱ የመግቢያ በሮች ስድስት የገበያ ማዕከላትን በመገንባት በተለይ በግብርና ምርቶች ላይ አምራችና ሸማቹ በቀጥታ እንዲገናኝ በማድረግ የደላላ ሰንሰለቱን መበጣጠስ ተችሏል። የህብረት ስራ ማህበራትም ምርት በመግዛትና በማቅረብ ለማህበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቶችን ማቅረብ እንዲችሉ ተሰርቷል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም 250 የእሁድና ቅዳሜ ገበያዎችን በማቋቋም ህብረተሰቡ በየአካባቢው የግብርና ምርቶችን በየደጁ ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የዋጋ ንረትን ለመከላከል ለምሳሌ የዳቦ አቅርቦት ዋጋ እንዳይጨምር የከተማ አስተዳደሩ ከ779 ሚሊዮን ብር በላይ ድጎማ በማድረግ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲቀርብ አድርጓል። ከ300 በላይ ባዛሮች በማካሄድ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረብ እንዲችሉ ተሰርቷል፡፡ በጤና መድህን፣ ምገባ፣ በትራንስፖርት ድጎማ በማድረግ የህብረተሰቡን የኑሮ ጫና ለማቃለል እየተሰራ እንደሚገኝም ከንቲባዋ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ በማድረግና ምርት በመሸሸግ ገበያውን ለማዛባት ሲሰሩ የተገኙ ከ18 ሺህ በላይ ነጋዴዎች በተያዘው ዓመት እንዲቀጡ መደረጉን ከንቲባ አዳነች አቤቤ አንስተዋል፡፡

## ጤና

ከጤና አኳያም ከተማዋን የጤና ቱሪዝም ማዕከል በማድረግ ረገድ ውጤታማ ስራ መሰራቱን ከንቲባ አዳነች አቤቤ አንስተዋል፡፡ በከተማዋ በሽታን አስቀድሞ ለመከላከል የብክለት ምንጭ የነበሩትን ወንዞች በማከም፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓቱን በማዘመን፣ ፅዳትን በማስጠበቅ፣ ከተማዋን አረንጓዴ በማድረግና ምቹ የእግረኛ መንገዶችን በመገንባትም ስኬታማ ስራ ተከናውኗል።

የጤና መሰረተ ልማትን በማስፋፋት ረገድም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የተሰሩት በመቶ ዓመታት ከተሰሩት በሁለት እጥፍ ከፍ ያሉ እንደሆኑ ከንቲባ አዳነች አቤቤ አብራርተዋል፡፡ 500 አልጋዎች ያሉት የቤቴል መንዲዳ አጠቃላይ ሆስፒታል በግንቦት ወር ወደ ስራ ይገባል፡፡ ሌላው 500 የመኝታ አልጋዎች ያሉት የላፍቶ ሆስፒታልም ግንባታው ተጠናቅቆ ዘመናዊ መሳሪያዎችና የሰው ሀይል በማደራጀት በቅርቡ ስራ ይጀምራል፡፡ ወደ 577 አልጋዎች ያሉት የገላን ድንገተኛ ህክምና ሆስፒታልም ግንባታውን በማጠናቀቅ በሚቀጥለው አዲስ ዓመት ወደ ስራ ለማስገባት እየተሰራ ይገኛል፡፡

ነባር ሆስፒታሎችም ዘመኑን የዋጁ እንዲሆኑ ደረጃቸውን በማሳደግና አዳዲስ ግንባታዎችን በማካሄድ የሚሰጡትን አገልግሎት ከፍ ለማድረግ ሰፋፊ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኝ ከንቲባዋ አንስተዋል፡፡ በቅርቡም በራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል ባለስድስት ወለል አዲስ ህንጻ ተገንብቶ መጠናቀቁንና ሰሞኑን ለአገልግሎት እንደሚበቃ ጠቁመዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል አገልግሎት እንዲሰጡ ዘጠኝ ጤና ጣቢያዎች፤ 40 ጤና ጣቢያዎች ደግሞ በማስፋፊያ በአዲስ መልክ መገንባታቸውን ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች እንደገለጹት፤ ባለፉት መቶ ዓመታት እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚተዳደሩ ሆስፒታሎች 1 ሺህ 384 አልጋዎች ነበራቸው፡፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት 2 ሺህ 811 አዳዲስ አልጋዎችን በመጨመር በጥቅሉ 4 ሺህ 195 ማድረስ የተቻለ ሲሆን፤ አዲስ አበባን የጤና ቱሪዝም መዳረሻ ማድረግ ተችሏል፡፡

## የትራንስፖርት አቅርቦት

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የትራንስፖርት አቅርቦትም ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ዘርፍ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ሰፋፊ ስራዎች ቢከናወኑም አሁንም ተግዳሮት ያለበት ዘርፍ ነው። ይህን ለመፍታት ቁልፍ የሆነ የመንገድ ግንባታና መንገድን የማስፋት ስራ መከናወኑን ያነሱት ከንቲባዋ፤ የእግረኛ መንገዶች፣ ፓርኪንግ፣ የብስክሌት መንገድ በመስራት በቴክኖሎጂ የታገዘ የፓርኪንግ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑን አንስተዋል፡፡ በዚህም በአሁኑ ጊዜ የከተማዋ የመንገድ ሽፋን ከ12 ነጥብ 8 በመቶ ወደ 20 በመቶ መድረሱን አብራርተዋል፡፡ ብቁ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ እንዲኖር ለማስቻልም በርካታ ስራ ተሰርቷል ሲሉ አክለዋል፡፡ ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ የነበረው የህዝብ ፓርኪንግ 3 ሺህ ተሽከርካሪ ማቆም የሚችል ነበር። አሁን 163 ሺህ ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ ማቆም የሚችል የህዝብ ፓርኪንግ መኖሩን አክለዋል፡፡ በወቅታዊ ሁኔታ የተከሰተውን የትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ የአውቶብስ ቁጥር ከመጨመር ባለፈ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን በመጠቀም እየተሰራ መሆኑን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

በአዲስ አበባ የአውቶቡስ ስምሪት በፊት ከነበረው ከ100 አሁን ወደ 212 መስመሮች አድጓል፡፡ በስምሪት የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ደግሞ በቴክኖሎጂ የታገዘ ስራ እየተሰራ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመት ስምሪቱ ሙሉ በሙሉ ወደ ስማርት ትራንስፖርት ስርአት ይቀየራል ሲሉ ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡

## ወጣቶችና ስፖርት

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ወጣቶችና ህጻናት ላይ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው ብለዋል፡፡ በዚህም በርካታ የስፖርት ማዝወተሪያ ማዕከላት እየተገነቡ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ 495 የነበረውን የስፖርት ሜዳ አሁን ከ2 ሺህ በላይ አድርሰናል። ስፖርትና ሜዳ ወደ ሰፈርና ወደ ሰው እንዲጠጋ አድርገናል፡፡ በተጨማሪም ትልልቅ ስታዲየሞችን እየሰራን ነው ብለዋል፡፡ እነዚህ ስታዲየሞች ሲጠናቀቁ ዓለም አቀፍ ሁነቶች የማስተናገድ አቅምን በከፍተኛ ቁጥር ይጨምራል። ስራው ከታች ያሉትን፣ መካከል ያሉትንና ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ታሳቢ በማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል። በሚያዝያ ወር ብቻ 3 ዓለም አቀፍ ሁነቶች መከናወናቸውንም ጠቁመዋል። ይህም ወጣቶችን የሚያነሳሳ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መሰረተ ልማት መገንባት ብቻ ሳይሆን ተተኪ ለማፍራትም በልዩ ትኩረት እየተሰራ ነው፡፡ የሰው ሃይል ስልጠና እየተከናወነ ነው፡፡ ከ3 ሺህ በላይ ልዩ ድጋፍ የሚደረግላቸው ወጣቶች መኖራቸውን አስታውቀዋል፡፡ ከንቲባዋ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# ለምርጫው ስኬት ከወጣቱ ምን ይጠበቃል?

**በስንታየሁ ምትኩ**

የአንድ ሀገር የዲሞክራሲ ሥርዓት ከሚለካባቸው መስፈርቶች መካከል በየወቅቱ የሚካሄዱ ምርጫዎች ነጻ፣ ፍትሐዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ መሆን አንዱ ነው፡፡ ምርጫ የዜጎች ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነት የሚረጋገጥበት መድረክ ብቻ ሳይሆን፣ የሀገር የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወሰንበት ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍም ነው፡፡ በተለይ አብዛኛው ሕዝብ ወጣት በሆነበት ሀገር የምርጫ ውጤታማነት በቀጥታ ከወጣቱ ትውልድ ሕይወትና የነገ እጣ ፈንታ ጋር የተቆራኘ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያም ሆነ አዲስ አበባ ይህ የኅብረተሰብ ክፍል ከአጠቃላይ ህዝብ 70 በመቶ የሚሆነውን እንደሚሸፍን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ “ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ” የተሰኘ ሀሳብ አመንጪ ተቋም በ2007 ዓ.ም ባዘጋጀውና “ወጣትነት ከህግ አንጻር በኢትዮጵያ” የሚል ርዕስ በተሰጠው የጥናት ሰነድ ላይ እንደሰፈረው፣ “በማንኛውም ኅብረተሰብ ወጣቱ የአፍላ ጉልበት፣ የብሩህ አዕምሮና እምቅ ሀይል ባለቤት ነው፡፡ ያለዚህ የኅብረተሰብ ክፍል የነቃና የተደራጀ ተሳትፎ የሚታለሙት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታዎችና የልማት እንቅስቃሴዎች ግባቸውን ሊመቱ አይችሉም፡፡ ወጣቱ የዛሬው ሀገር ገንቢ ብቻ ሳይሆን የነገው የሀገር ተረካቢም ጭምር በመሆኑ የአንድ ሀገር የወደፊት ዕጣ ፈንታም ከዚህ የኅብረተሰብ ክፍል እድል ጋር የተቆራኘ ነው፡፡”

አዎ! ይህንን በቁጥር ግዙፍ፣ ባለብሩህ አዕምሮ፣ እምቅ አምራች ሀይል፣ ሀገር ገንቢና ተረካቢ የኅብረተሰብ ክፍል በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ አስፈላጊ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የወጣቱን ንቁ ተሳትፎ ከሚሹ ጉዳዮች መካከል 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ አንዱ ነው፡፡ በምርጫው ሂደት የወጣቶች ንቁ ተሳትፎ መኖር ለሀገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ ወሳኝ ነው።

ወጣት ሰላም በላይነህ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 ነዋሪ ናት፡፡ የምርጫ ካርድ በማውጣት በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ “ይበጀኛል”፤ “ሀገርን ወደተሻለ ደረጃ ያሻግራል፤ ሰላም፣ እድገትና ብልፅግናን ያመጣል” ለምትለው የፖለቲካ ፓርቲ ድምፅ ለመስጠት እየተጠባበቀች ትገኛለች፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር አባል በመሆን ንቁ ተሳትፎ እያደረገች እንደምትገኝ ለዝግጅት ክፍላችን የገለፀችው ወጣት ሰላም፣ ወጣቱ የምርጫ ካርዱን በማውጣት የዜግነት መብቱን እንዲጠቀም ቅስቀሳ ስታደርግ ቆይታለች። በድምፅ መስጫው ዕለት በታዛቢነት እንደምትሳተፍም ገልጻለች፡፡

በቀሪ ጊዜያት ወጣቱ ከራሱ አኳያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ዓይነት አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦችን ይዘው እንደመጡ በአግባቡ በመከታተል የተሻለ ለሚለው ድምፁን ለመስጠት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እንደ ወጣት ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የወጣቱ ኃላፊነት ትልቅ መሆኑን የምትገልፀው ወጣት ሰላም፣ ከዚህ አኳያ ከምንም በላይ ሰላምን በማስቀደም መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ የምርጫው ሰላማዊና ደሞክራሲያዊ ሆኖ መጠናቀቅ ወጣቱ ተጠቃሚ እንዲሆንና ጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑን ተናግራለች፡፡



ፎቶ- ከፋይል
የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉዓለም ኃ/ማርያም



ፎቶ- ከፋይል
የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ፕሬዚዳንት በረከት ብርቢርሳ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪው ወጣት አብዲ ቦንሳ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፅ ለመስጠት የምርጫ ካርድ በማውጣት የድምፅ መስጫ ዕለትን እየተጠባበቀ እንደሚገኝ ይናገራል፡፡ “መምረጥና መመረጥ የዜግነት መብታችን ነው፡፡ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ እኩል የመሳተፍ ዕድል ይፈጥርልናል። በምንመርጠው አካልም የመወከል፣ በመረጥነው አካል የኢኮኖሚን ጨምሮ የተለያዩ ጥያቄዎቻችንና ፍላጎታችን ምላሽ እንዲያገኝ ያስችላል” ይላል፡፡

ወጣቱ በምርጫው ሂደት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለበት የሚመክረው ወጣት አብዲ፣ ድምፁንም ምክንያታዊ በመሆን ዘላቂ ሰላምና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማምጣት የተሻለ ሀሳብ ይዞ ለሚቀርብ የፖለቲካ ፓርቲ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ባሻገር ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ በሰላማዊ መንገድ በመንቀሳቀስ፣ ሰላምን ሊያውኩና ሁከት ሊፈጥሩ ከሚችሉ ድርጊቶች በመቆጠብ ለምሳሌ፡- በማህበራዊ ሚዲያ ስለሰላማዊ ምርጫ ፋይዳ ግንዛቤ በመፍጠር፣ ችግር ሲፈጠርም ከፀጥታ አካሉ ጋር አብሮ በመቆም የራሱን አስተዋፅኦ ማበርከት እንደሚጠበቅበት ይመክራል፡፡

## ማህበሩ ምን እየሰራ ነው?

የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የከተማዋ ወጣቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ዘርፎች ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግን ዋና ዓላማው በማድረግ የሚሰራ ማህበር ነው። በአሁኑ ወቅትም 500 ሺህ አባላት አሉት፡፡ የማህበሩ ፕሬዝዳንት ወጣት በረከት ብርቢርሳ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጸው፤ በከተማዋ ከሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች አብዛኛው ወጣት እንደመሆኑ በነገው የሀገሪቱና የከተማዋ አቅጣጫና እጣ ፈንታ ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ለዚህም ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታል፡፡

ዘላቂነት ያለው ሰላምና ልማት በመኖሩ ዋነኛ ተጠቃሚ የሚሆነው ወጣት ነው። ግጭትም ካለ ተጎጂ የሚሆነው ራሱ እንደሆነ የሚያነሳው ወጣት በረከት፣ የእያንዳንዱ ወጣት ድምፅ ዋጋ እንዳለው በመረዳት በ7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ የወጣቱ በምርጫው መሳተፍ ሕገ መንግስታዊ የዴሞክራሲ መብቱን የመጠቀም አካል ነው፡፡ በራሱ “ነገ ይመራኛል” የሚለውን የሚመርጥበትን፤ በመረጠውም የሚተዳደርበትን ዕድል ይፈጥራል። ይህም በሀገሩና በሚመሰረተው አስተዳደር ያለው የባለቤትነት ስሜት ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

የማህበሩ ፕሬዝዳንት ወጣት በረከት እንደሚናገረው፣ ምርጫው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ወጣቱ የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ከማድረግ አኳያ ማህበሩ በተለያየ መልኩ እየሠራ ይገኛል፡፡ አንደኛ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ነው፡፡ ማንኛውም እድሜው ለመራጭነት የደረሰ ወጣት የምርጫ ካርድ እንዲያወጣ በተለይም የማህበሩ አባላት የምርጫ ካርድ እንዲያወጡ፣ ሌሎችም አባል ያልሆኑ ጭምር፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፅ መስጠት የሚችሉ ወጣቶች እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ የስነ ዜጋ ትምህርት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ካርድ ከማውጣት ባሻገር በድምፅ መስጫ ዕለት ድምፃቸውን እንዲሰጡና ለዚህም ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያካሂዷቸውን የምርጫ ዘመቻዎች፣ አማራጭ የፖሊሲ ሀሳባቸውንና ፕሮግራሞቻቸውን መከታተል፣ የወጣቱን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ለማሳደግ የተሻለ የፖሊሲ ሀሳብ ያለውን ለይተው እንዲያውቁ የማስተማር ሥራ እየተሰራ ነው፡፡

በወረዳ፣ በክፍለ ከተማና በከተማ ደረጃ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተዘጋጁ ስለምርጫው ግንዛቤ የሚፈጥሩ በራሪ ወረቀት (ብሮሸሮችን) በማሰራጨት፣ ቤት ለቤትና በድምፅ ማጉያ በከተማዋ በሁሉም ወረዳዎች፣ በአደባባዮችና ሰዎች በብዛት በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በመንቀሳቀስ ቅስቀሳ ተደርጓል። ማህበሩ ይህንን ለማከናወን ያስቻለው ዘንድም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ትምህርት (ስነ ዜጋ) እና በታዛቢነት ለመሳተፍ የምስክር ወረቀት አግኝቷል፡፡

በተጨማሪም በምርጫው ዕለት 2 ሺህ 228 ታዛቢዎችን በማሰማራት መራጩ በነጻነት፣ ያለማንም ጣልቃ ገብነትና ጫና የፈለገውን መምረጡን፣ የምርጫ ሂደቱ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መካሄዱን እንደሚከታተል ወጣት በረከት ገልጿል፡፡

ከዚህ ባሻገር ማህበሩ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በፖሊሲያቸው የወጣቱን ጉዳይ እንዲያካትቱ፣ ወጣቱም በፖለቲካው ለምሳሌ በምርጫው በመምረጥ ብቻ ሳይሆን በፈለገው የፖለቲካ ፓርቲ በመታቀፍ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ግንዛቤ በመፍጠር ሲሰራ መቆየቱንም አንስቷል፡፡

ምርጫ አንዱ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማጠናከሪያ፣ የተለያየ ልዩነት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቀራርበው ፖሊሲና ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ የሚያቀርቡበት መሳሪያ እንደመሆኑ፣ ወጣቶች ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ መፍታትን፣ ውይይትን፣ በምርጫው አሸናፊ የሆነ አካል ውጤት በፀጋ መቀበልን መለማመድ አለባቸው፡፡ ከምንም በላይ ሀገር የምትቀድም በመሆኗ ወጣቱ ሰላምን በማስቀደም መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡ ከቤት ጀምሮ ሰላም በመፍጠር፣ አካባቢውንና ከተማውን በመጠበቅ መሳተፍ ይኖርበታል፡፡ በማህበራዊ ሚዲያም ሆነ በማንኛውም መንገድ ሀሰተኛ መረጃዎችን ከማሰራጨት በመቆጠብ፤ ከፀብ ቀስቃሽ እንቅስቃሴዎች በመራቅ፣ በሀሳብ የበላይነት በማመን መንቀሳቀስ እንዳለበት ወጣት በረከት አስገንዝቧል፡፡

በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ሙሉዓለም ኃ/ማርያም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ በኢትዮጵያ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

**ወጣቱ በድምፅ መስጫ ዕለት ‘ይጠቅመኛል፤ ሀገርን ይለውጣል’ ለሚለው የፖለቲካ ፓርቲ ድምጹን መስጠት ይጠበቅበታል። የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክር የፖሊሲ ሀሳብና ፕሮግራማቸውን ሲያቀርቡ ወጣቱንና ሀገሪቱን ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችሉ ጉዳዮችን እንደያዙ ማወቅ ይኖርበታል**

# ከጥሻ ወደ መናፈሻ

- **የወንዝ ዳርቻ ልማቱ አካባቢዎቹን ለመዝናኛ ተመራጭ እያደረጋቸው እንደሆነ ነዋሪዎች ገልጸዋል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በተለምዶ የራስ መኮንን ድልድይ ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ በሚደረግ ጉዞ ላይ የሚገኝ መሸጋገሪያ ነው፡፡ በዓድዋው ጀግና ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የተሰየመው ድልድይና ምንጭ፣ ዝነኛው 70 ደረጃ፣ ወንዝና ሌሎች መገለጫዎችን አቅፎ ይዟል፡፡ ትናንት በቆሻሻ ክምር፣ ከእንጨትና ጭቃ በተሰሩ ደሳሳ ቤቶች፣ በፈራረሱ አጥሮች፣ በጥሻ የተሸፈነ፣ የመጥፎ ጠረን ምንጭ የነበረ፣ ሲመሽ ጨለማው ያስፈራ የነበረው ይህ የራስ መኮንን ድልድይ ራስጌና ግርጌ፤ ዛሬ መልኩን ቀይሮ የከተማዋ የውበት ማማ ሆኗል፡፡



ፎቶ በገነት ወንድሙ

በራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ የሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ልማት በከፊል

አቶ መኩሪያ ጌታቸው ትውልድና እድገታቸው ሽሮሜዳ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነው፡፡ ያገኘናቸው ከሚያቃጥለው ፀሐይ እረፍት ለማድረግ ከራስ መኮንን ድልድይ ራስጌ ባለው መናፈሻ ውስጥ ካለው ዛፍ ስር ቁጭ ብለው ነበር፡፡ በቅርብ ርቀት ላይ የሚኖሩ በመሆኑ ታሪካዊውን የራስ መኮንን ድልድይ አካባቢን በተደጋጋሚ ይመላለሱበታል፤ በደንብም ያውቁታል። “የአሁኑና የቀድሞው ሁኔታ በፍፁም አይገናኝም፡፡ እዚህ አካባቢ የነበረውን ገጽታ በቃላት ለመግለፅ ያስቸግራል፡፡ ወንዙና አካባቢው በቆሻሻ የተሞላ ነበር” ይላሉ፡፡

በአካባቢው የተሰራውን የወንዝ ዳርቻ ልማት ሲያልፉ ሲያገድሙ ሲመለከቱ መቆየታቸውን የሚያነሱት አቶ መኩሪያ፣ “አሁን ላይ ለዓይን በሚማርክ፣ የመንፈስ እርካታን በሚያጎናጽፍ መልኩ ንጹህና ውብ ሆኗል፡፡ ዛሬ ለሁለተኛ ጊዜ እረፍት ለማድረግ መጥቼ ነው ያገኘሽኝ፡፡ በጣም ያምራል፡፡ ከዚህ ቀደም በከተማዋ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት አረንጓዴ አካባቢ ማየት ብርቅ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም መስራት ሳንችል ቀርተን ሳይሆን ሀሳቡ ስላልነበረን ነው፡፡ አሁን ግን አቅም የለንም በሚል ወደኋላ እንደማይባልና ሀገርን የሚቀይር ሥራ መሥራት እንደሚቻል ታይቷል፡፡ እንዲህ ዓይነት ለውጥ በከተማዋ በራስ መኮንንና አፍንጮ በር ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች በስፋት ታይቷል” ይላሉ፡፡

በአዲስ አበባ ሰሜን ሆቴል አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ታደሰ አበራ በበኩላቸው፣ የራስ መኮንን ድልድይ አካባቢን ድሮ ከወንዙ በሚወጣው መጥፎ ሽታ የተነሳ አፍንጫቸውን ይዘው የሚያልፉበት አካባቢ እንደነበር እና አሁን ላይ የአካባቢው ለውጥ ግርምት ፈጥሮባቸው በእግር እየተንቀሳቀሱ ለማየት እንደመጡ ይናገራሉ፡፡ “ሰው ውብ የሆነ ነገር ማየት፣ ንፁህ አየር መተንፈስ ይፈልጋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ስፍራዎች ትውልዱ ንጹህ የሆኑ ነገሮች እያየ አዕምሮው እንዲታደስና ለሀገሩ የሚጠበቅበትን ለመወጣት እንዲነሳሳ

> **የራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ዛሬ በውስጡ ሳር፣ አበባ፣ ዛፍ፣ መቀመጫ ወንበሮች፣ በአረንጓዴ ተክሎች መሀል የተነጠፉ ውብ የእግረኛና መሮጫ መንገዶች፣ ግድቦች፣ ካፌና ሬስቶራንቶችን ጨምሮ ነዋሪዎችና ጎብኚዎች አረፍ ብለው የሚዝናኑበት፣ በእግር በነፃነት እየተራመዱ ነፋሻማውን አየር የሚወስዱበት፣ ለማስታወሻ ፎቶ የሚነሱበት ውብ አካባቢ ሆኗል**

ያደርገዋል፡፡” ሲሉ ለውጡ የሚያስገርምና ለትውልድ ግንባታም ትልቅ ትርጉም ያለው መሆኑን አስረድተዋል፡፡ “እኔ መልካም የሆነ ነገር እያየሁ ነው፡፡ ልጆቼ ደግሞ የበለጠ ልጆቻቸውንና ኢትዮጵያን ይዘው ያድጋሉ ብዬ አስባለሁ፡፡” ሲሉም ለወደፊቱ የሀገሪቱ እድገት የሚኖረውን ብሩህ ተስፋ ጠቁመዋል፡፡

የራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ዛሬ በውስጡ ሳር፣ አበባ፣ ዛፍ፣ መቀመጫ ወንበሮች፣ በአረንጓዴ ተክሎች መሀል የተነጠፉ ውብ የእግረኛና መሮጫ መንገዶች፣ ግድቦች፣ ካፌና ሬስቶራንቶችን ጨምሮ ነዋሪዎችና ጎብኚዎች አረፍ ብለው የሚዝናኑበት፣ በእግር በነፃነት እየተራመዱ ነፋሻማውን አየር የሚወስዱበት፣ ለማስታወሻ ፎቶ የሚነሱበት ውብ አካባቢ ሆኗል፡፡

ከሞያሌ ቤተሰብ ለመጠየቅ ወደ አዲስ አበባ የመጡት ወጣት ጥንዶች አቡሽ ታሪኩ እና አስቴር ዘርአብሳ በወንዝ ዳርቻው ላይ በተሰራው መቆጣጠሪያ አነስተኛ ግድብ ዳር ፎቶ ግራፍ እየተነሱ ሲዝናኑ ነበር ያገኘናቸው፡፡ አካባቢውን እንዴት እንዳገኙት ጠይቀናቸው፣ “ምንም እኮ መናገር አያስፈልግም፤ እንደምታየው ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው ይህንን አካባቢ ያየሁት፡፡ ሳሩ፣ የእግረኛ መንገዱ፣ አበቦች... ሁሉ ነገር በጣም ደስ ይላል። ለማስታወሻ የሚሆን ፎቶ ተነስተናል፤ በጣም ደስ ብሎናል፡፡” ስትል ወጣት አስቴር ዘርአብሳ የነበራቸውን ቆይታ ነግራናለች፡፡

የራስ መኮንን አካባቢ የወንዝ ዳርቻ ዘመናዊ ካፌዎች፣ ስም ያላቸው ድርጅቶች ቡና የሚሸጡበት የቡና ፓርክ ጭምር አካትቶ ይዟል፡፡ በራስ መኮንን ካፌና ሬስቶራንት በረንዳ ላይ ከባለቤታቸው ጋር ተቀምጠው ሻይ ቡና ሲሉ ያገኘናቸው አቶ ሽመልስ ቀለመወርቅ፣ የአካባቢውን ለውጥ “ስር ነቀል” ነው ሲሉ ይገልጹታል። ከዚህ ቀደም አንዳንድ ሱቆች የነበሩበት ቢሆንም የቆሻሻ መጣያ፣ በአረምና ጥሻ የተዋጠ ነበር፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ “እንደ መሻገሪያ መንገድ ሮጠን እናልፈው፣ ወንዙንም ዞር ብለን አናየውም ነበር፡፡ አሁን ግን ያ ተቀይሮ ቁጭ ብለን እረፍት የምናደርግበትና የምንዝናናበት ስፍራ ሆኗል፡፡ ንፅህናው፣ አበቦቹ፣ ነፋሻማው አየር... ልዩ ነው፡፡” በማለት በፈገግታና በአድናቆት ስሜታቸውን ገልጸውልናል፡፡

“የአዲስ አበባ ወንዞች ትንሣኤ” በሚል ርዕስ ከሦስት ወር በፊት በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በተላለፈው ጥናታዊ ፊልም ላይ የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት፣ የራስ መኮንን ድልድይ ላይ አዲስ የመስታወት የእግረኛና ሳይክል መተላለፊያ ድልድይ ተሰርቷል፡፡ ድልድዩ ወደ ዓድዋ ጦርነት የተደረገውን ዘመቻ በሚያሳይ መልኩ የጋሻና ጦር ምልክቶች ተካትተውበት በሚያምር መልኩ ተገንብቶ፤ ብዙዎች የሚዝናኑበትና ለማስታወሻ ፎቶ የሚነሱበት ስፍራ ሆኗል፡፡ የራስ መኮንን ምንጭና መታሰቢያ ሀውልት የሚገኝበት አካባቢም ከዚህ ቀደም የቆሸሸና ትኩረት ተነፍጎት የቆየ ቦታ የነበረ ሲሆን በወንዝ ዳርቻ ልማቱ ፀድቷል፤ ምንጩም በፏፏቴ መልክ እንዲወርድ ተደርጓል።

በአካባቢው የትናንት ጥሩ ነገሮች ልቀውና እሴት ተጨምሮባቸው እንዲታዩ ተደርገዋል፡፡

ከራስ መኮንን ምንጭ አለፍ ብሎ ደግሞ የተለየ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ባለው ስፍራ የቡና ፓርክ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጥላሁን ወርቁ እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ሀገር እንደመሆኗ ይህንን ለማሳየት የቡና ችግኝ የተተከለበትና ቡናን በመሸጥና በማስተዋወቅ የሚታወቁ ድርጅቶች የሚሰሩበት የቡና ፓርክ እንዲገነባ ተደርጓል፡፡ ከቡና ፓርኩ ፊት ለፊት፤ ማጾ ባለው ስፍራ ካፌና ሬስቶራንት፣ ዛፍ፣ አበቦች፣ የተለያዩ ዕፅዋት ያሉበት መናፈሻ ይገኛል፡፡ በተጨማሪ በአካባቢው የሚያልፈው ወንዝ ፍሰቱን ጠብቆ በሥርዓት እና በተመጠነ መልኩ መውረድ እንዲችል የሚያደርግ መቆጣጠሪያ ግድብም (Check dam) ተገንብቷል፡፡

አቶ ስዩም ከበደ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት አስተዳደር ባለሥልጣን በምክትል ዋና ዳይሬክተር ማዕረግ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚናገሩት፣ ከታሪካዊው የራስ መኮንን ድልድይ አንስቶ እስከ አፍንጮ በር እና ሌሎች አካባቢዎች የወንዝ ዳርቻ እና የኮሪደር ልማቱ ከመጀመሩ በፊት በከፍተኛ ደረጃ የተበከሉና የጤና ስጋት የነበሩ

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# ስለመስሪያ ቦታዎች ደንቡ ምን ይላል?

ጠናበል ለማ (ዓቃቤ ህግ)

## መግቢያ

መሠረተ-ልማት የተሟላላቸው፣ ምቹና ደረጃቸውን የጠበቁ መስሪያ ቦታዎች እና የለሙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለኢንተርፕራይዝና ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ በፍትሐዊነት በማቅረብ ድጋፍ መስጠት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤ የነባር ወይም አዳዲስ ግንባታዎች የተጠናከረ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት ከብክነትና ከሕገ-ወጥነት በጸዳ መልኩ የመስሪያ ቦታዎችን ማልማት፣ ማስተላለፍና ማስተዳደር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የመስሪያ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ ለማዋል ባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ ግልፅ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ከሌብነትና ብልሹ አሠራር የጸዳ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የአዲስ አበባ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 94 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### 1.የመስሪያ ቦታ የቃሉ ትርጉምና ግንባታ

በደንቡ አንቀጽ 2/5 በግልጽ እንደተመለከተው መስሪያ ቦታ ማለት በመንግሥት፣ በግል፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ በመንግሥት ቦታ ላይ ተገንብተው ኢንተርፕራይዞችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት የሚያመርቱበት፣ የሚያሳዩበት፣ የሚሸጡበት ወይም አገልግሎት የሚሰጡበት የሥራ ቦታ ነው፡፡ የመስሪያ ቦታዎች ሲገነቡ ማካተት ያለባቸውን ነገሮች በደንቡ አንቀጽ 4/11 ተደንግጎ ያለ ሲሆን፤ የሚገነቡ የመስሪያ ቦታዎች የሕጻናት ማቆያ፣ የሠራተኞች መመገቢያ፣ የጋራ መጸዳጃና የሰውነት መታጠቢያ እና አረንጓዴ ቦታን ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 2.የመስሪያ ቦታ የሚተላለፍላቸው የሥራ መስኮች

የመስሪያ ቦታዎች የሚተላለፍላቸው የሥራ መስኮች እንደየሥራ መስካቸው በ5 የመስሪያ ቦታዎች ምድብ የተከፋፈሉ ሲሆን እነዚህም በደንቡ አንቀጽ 7/1 በዝርዝር የተገለጹ በመሆናቸው የመስሪያ ቦታዎች የሚተላለፉት ከዚህ በታች ላሉት ንዑስ ዘርፎች ይሆናል፡-

**ሀ. ጂ+4 ማምረቻ ሕንጻ፡-** የልብስ ስፌት ሥራ፣ የሸማ ሥራ፣ የቆዳ ውጤቶች ሥራዎች፣ የጥልፍ ሥራ፣ ሹራብ ሥራ፣ ሕንጻ ላይ የሚስተናገዱ የፈጠራ ሥራዎች፣ ሕትመትና የወረቀት ሥራዎች፣ ከተዘረዘሩት ጋር ተቃርኖ የሌላቸው ሌሎች የምርት ማምረት ሥራዎች

**ለ. ጂ+2 ማምረቻ ሕንጻ፡-** የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ ደረቅ ምግብ ዝግጅት፣ የመድኃኒት ማምረትና የውበት መጠበቂያ፣

**ሐ. ወርክ ሾፕ፡-** የእንጨት ሥራዎች፣ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ የኮንስትራክሽን ግብአት፣ የመድኃኒት ማምረትና የውበት መጠበቂያ፣ የከበሩ ማዕድናትና ጌጣጌጥ ሥራ፣ የኬሚካል ምርቶች፣

**መ. ሼድ፡-** የኮንስትራክሽን ግብአት ምርት፣ የእንጨት ሥራዎች፣ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራዎች፣ የከተማ ግብርና ሥራዎች፣ የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ የደረቅ ምግብና የባልትና ውጤቶች ምርት፣ ፕላስቲክ ሥራዎች፣ የፋይበር ግላስ ሥራዎች፣ ወረቀትና ፕላስቲክ መልሶ መጠቀም፣ የዕደ-ጥበብ ሥራዎች ወይም በእጅ የሚመረቱ ምርቶች፣ ሳሙናና ዲተርጀንት (ንጽህና መጠበቂያ) ማምረት፣ ከረሜላ ማምረት፣ ቀለምና ቫርኒሽ ማምረት፣ የሕትመትና ወረቀት ሥራዎች፣ የመድኃኒት ማምረትና የውበት መጠበቂያ፣ እና



**ሠ. ሞሎች፣ የመሸጫ ሕንጻዎች፣ ተለጣፊ ሱቆች፣ በመንገድ ዳርቻ የሚተከሉ የአውቶቢስ ሱቆች፣ መደብሮች እና በኮንደሚኒየም የንግድ ሱቆች፣ ተንቀሳቃሽ ሱቆች እና ሌሎች መስሪያ ቦታዎች፡-**

በሀገር ውስጥ የተመረቱ የእንጨትና ብረታ ብረት ውጤቶች፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ውጤቶች፣ ካፌና ሬስቶራንት፣ ሳሙናና ዲተርጀንት ውጤቶች፣ የሕትመት፣ ማስታወቂያና የወረቀት ውጤቶች፣ የኤሌክትሮኒክስና ሶፍትዌር ልማት፣ የጥገና ሥራዎችና የጽሕፈት አገልግሎት፣ የግብርና ውጤቶች ማቀነባበሪያ ውጤቶች፣ የባህላዊ ዕደ-ጥበብና ጌጣጌጥ ሥራ ውጤቶች፣ ለአምራች ኢንተርፕራይዝ የሚያገለግሉ የእቃ አቅርቦት፣ የመድኃኒትና የውበት መጠበቂያ፣ ፕላስቲክና የፕላስቲክ ውጤቶች ሽያጭ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 3. የመስሪያ ቦታ ተከራይ የቆይታ ጊዜ፣ መብቶችና ግዴታዎች

በደንቡ አንቀጽ 16/1 መሠረት የመስሪያ ቦታ ተከራዮች ውል ከገቡበት ቀን ጀምሮ በየዓመቱ እየታደሰ ለ5 ዓመት ብቻ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ መብቶችና ግዴታዎች ከአንድ አከራይ ተከራይ ስምምነት ከውልና ከሕግ የሚመነጩ ሲሆን በደንቡ አንቀጽ 21/1-4 ተደንግገው የምናገኛቸው ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

1. የመስሪያ ቦታውን በውሉ መሠረት በነጻነት የመጠቀም
2. የጋራ መገልገያዎችን ከሌሎች ተከራዮች ጋር መጠቀም
3. የመስሪያ ቦታውን ከሚያስተዳድረው አካል አስፈላጊውን መረጃና ድጋፍ ማግኘት
4. መሠረተ-ልማት እንዲሟላለት የመጠየቅ መብቶች ናቸው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት መብቶች ያሉት ተከራይ የሚከተሉት ግዴታዎችም ይኖሩበታል፡፡ በደንቡ አንቀጽ 22/1-11 መሠረት ተገልጸው ይገኛሉ፡፡

የመስሪያ ቦታ ኪራይ፣ የመብራት፣ የውኃ፣ የጥበቃና ሌሎች የጋራ አገልግሎቶች ክፍያ በወቅቱ መፈጸም በግቢው ውስጥ በሚከናወኑ የልማት፣ ጽዳትና ውበት ሥራዎች ላይ የመሳተፍ፣ የጋራ መገልገያ ንብረቶችን በንጽሕና የመያዝና የመጠበቅ፣ የመስሪያ ቦታውን ለታለመለት ዓላማ እና ውል ለገባበት ተግባር ብቻ ማዋል፣ በመስሪያ ቦታ ይዞታ ውስጥ ምንም ዓይነት ሕገ-ወጥ ግንባታ አለመገንባትና ከተፈቀደላቸው የመስሪያ ቦታ ውጭ አስፋፍቶ አለመያዝ፣ የእሳት አደጋ፤ ጤናና ሰላምን ሊያውኩና የአካባቢ ብክለትን ሊያመጡ የሚችሉ ተግባራትን አለመፈጸም፣ የእሳት አደጋ መከላከያና የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሣሪያ፣ በመስሪያ ቦታው ውስጥ በግልጽ ቦታ ማስቀመጥ፣ ተከራይ አከራይ የሚጠይቀውን መረጃ የመስጠትና ትብብር የማድረግ፣ ተከራይ የተከራየውን የመስሪያ ቦታ ለ3ኛ ወገን አለማስተላለፍ፣ የ5ኛ ዓመት የውል ጊዜው ሲጠናቀቅ የመስሪያ ቦታውን የመልቀቅ እና ማንኛውም የመስሪያ ቦታ ተጠቃሚ የሆነ ተከራይ የአባላቱ ብዛት ሲጓደል ምትክ አባላትን ተክቶ መሥራት ይኖርበታል፡፡

### 4. የመስሪያ ቦታ ተከራይ ቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት ስንመለከት፡-

በደንቡ አንቀጽ 23/1-6 ያሉት ሲሆኑ እነርሱም፡-

1. ከተገልጋይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት በመዘርጋት እንዲፈታ ይደረጋል፤
2. ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ በመጀመሪያ ደረጃ አገልግሎቱን ለሰጠው የሥራ ክፍል በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤
3. ቅሬታው የቀረበበት የሥራ ክፍል ለቀረበው አቤቱታ በ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ምላሽ መስጠት አለበት፤
4. ቅሬታ የቀረበበት የሥራ ክፍል በሰጠው ምላሽ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በ7 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለክፍለ ከተማ ጽ/ቤት ኃላፊ፤ በማዕከል ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ይሆናል፤
5. በጽ/ቤት ኃላፊ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን በ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ሊያቀርብ ይችላል፤
6. አቤቱታ የቀረበለት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቤቱታው በቀረበለት በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል፤ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ስለሚል የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት ደግሞ ይህንን ደንብ በስፋት ማንበብ ይገባናል፡፡

# የመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ ሁነቶች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል፣ የመጽሐፍት እና ሐሳብ ውይይት፣ የሥነ-ጥበብ አውደ ርዕይ፣ የቴአትር ምርቃት እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ

ለሁለት ቀናት ሲካሄድ የነበረው የመጀመሪያው የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ ተጠናቀቀ። የአፍሪካን እውነተኛ ገጽታ ለዓለም ለማስተዋወቅና የዲጂታል ትርክቱን በባለቤትነት ለመምራት ያለመው የመጀመሪያው የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ (ASMIS 2026) በአዲስ አበባ ዓድዋ ድል መታሰቢያ በትናንትናው እለት ተጠናቅቋል፡፡

በጉባኤው ለመታደም ከ30 የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ 321 ሚሊዮን በላይ የማህበራዊ ሚዲያ ተከታዮች ያሏቸው 61 ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ በተጨማሪም 150 ሚሊዮን ተከታዮች ያላቸው 120 ኢትዮጵያውያን የይዘት ፈጣሪዎች በጋራ በመሰባሰብ፣ የዓለም የዲፕሎማሲ ማዕከል በሆነችው አዲስ አበባ አዲስ የዲጂታል ታሪክ ጽፈዋል። ጉባኤው የአፍሪካ የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ጉባዔ ኃላፊነት የሚሰማቸው የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችን ለማበረታታት፣ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለማጠናከር፣ ትብብርን ለመፍጠርና አዲስ አበባን የባህልና የዲጂታል ማዕከል ለማድረግ ያለመ ነው። ተሳታፊዎቹ የተለያዩ የመዲናዋ የልማት ስራዎችን ጎብኝተዋል፡፡

## የመጽሐፍት እና የሐሳብ ውይይት

83ኛው ዙር የዐውደ ፋኅስ የመጽሐፍት እና የሐሳብ ውይይት ነገ ይደረጋል፡፡ የውይይቱ ርዕስ "የግለ ታሪክ መጻሕፍት ቅኝት" (በተመረጡ የአማርኛ መጻሕፍት ላይ) የሚል ነው፡፡ በመርሃ ግብሩ ላይ ደራሲ እና አርታኢ ቢኒያም አቡራ መነሻ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ መርሃ ግብሩ ነገ ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብት እና ቤተ መጻሕፍት (ወመዘክር) ይካሄዳል፡፡

## የሥነ ጥበብ አውደ ርዕይ

በአይነቱ ልዩ የሆነ የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ለእይታ ሊበቃ ነው፡፡ አውደ ርዕዩ "የኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ከዋክብት በእውቁ ጀርመናዊ ፎቶግራፈር ደርክ ስኪባ ካሜራ ሌንስ ሲታዩ" የሚል ነው፡፡ በስንኝ ክርኤቲቭስ እና በጎተ ኢኒስቲቱዩት ትብብር የተዘጋጀ አውደ ርዕይ ማክሰኞ 11፡30 ጀምሮ በጀርመን ባህል ማዕከል ይከፈታል።

በሌላ መረጃ "ትስስር" የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ነው፡፡ የአብዱልቃድር መሐመድ፣ ኢሳ ታደለ እና ምስለኬ እሸቱ ስራዎች የቀረቡበት ይህ የቡድን የግራፊክስ የስዕል አውደ ርዕይ እየታየ የሚገኘው በፈንድቃ የባህል ማዕከል ሲሆን እስከ ግንቦት 17 ቀን 2018 ዓ.ም. ድረስ በእይታ ላይ ይቆያል፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## የቴአትር መርሃ-ግብር

አዲሱ የአፋን ኦሮሞ ትውፊታዊ ቴአትር "ሰዴታ" ነገ ይመረቃል፡፡ በአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ተፅፎ የተዘጋጀው ይህ ጥበባዊ ስራ የኦሮሞ ህዝብ ያለውን የቀደመ ስልጣኔና ማህበራዊ ትስስር በሚያንጸባርቅ መልኩ የተቃኘ ሲሆን፣ በተለይም በገዳ ስርዓት ውስጥ የሴቶችን የላቀ ሚና፣ ክብርና ውሳኔ ሰጪነት ለተመልካች ያቀርባል።

ይህ በደራሲ የውብዳር መለያ ተፅፎ በዳይሬክተር ይድነቃቸው ወርቁ የተዘጋጀው ቴአትር፣ በኦሮሞ ማህበረሰብ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ የ"ሲንቄ"ን አይነተኛ ፋይዳ ማለትም እርቅን በማውረድ፣ ሰላምን በማስፈንና የሴቶችን መብት በማስከበር ረገድ ያለውን አቅም በጉልህ የሚያሳይ ነው።

ቴአትሩ ዘመናዊ የመድረክ አቀራረብን ከጥንታዊው ትውፊት ጋር አዋህዶ የያዘ ሲሆን፣ በውስጡም ትውፊታዊ ሙዚቃዎችን፣ አልባሳትንና የቋንቋ ውበትን አጣምሮ በመያዝ ለአንድ ሰዓት ከ40 ደቂቃ ያህል በመድረክ ላይ የሚቆይ ይሆናል።

የአዲስ አበባ ቴአትር ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ይህንን ስራ ለተመልካች ማቅረቡ የሀገራችንን የጥበብ ዘርፍ ለማሳደግና የወል ትርክትን ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑን ገልጾ፣ ስራው በአፋን ኦሮሞ ለሚዘጋጁ የቴአትር ስራዎች አዲስ የጥበብ መንገድ ይከፍታል ብሏል። "ሰዴታ" ቴአትር ነገ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ይመረቃል፡፡


በሌላ መረጃ በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ ቅዳሜ ከ7፡30 ሲሆን "12ቱ እንግዶች" ቴአትር እንዲሁም 11፡30 ደግሞ "ሽምጋይ" ቴአትር ይታያል። እሑድ በ7፡30 "ንጉሥ አርማህ" ቴአትር፣ እንዲሁም "እምዩ ብረቷ" የተሰኘው ቴአትር በ11፡30 ላይ ይታያሉ። በብሔራዊ ቴአትር ለሚታዩ ቴአትሮች ተመልካቾች ጊዜያቸውን ለመቆጠብ በ"ሁሉ በጄ" መተግበሪያ በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል። በተጨማሪም ባልቻ አባነፍሶ ቴአትር እሑድ በ8:00 ሰዓት በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የሚታይ ሲሆን፤ ትኬት በኦን ላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም "አዮ ቦራ" የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ የህፃናት ቴአትር ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት በህፃናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ለእይታ ይቀርባል፡፡ በተመሳሳይ "የሰማይ ልጆች" የተሰኘው ቴአትር እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ፍላሚንጎ በሚገኘው በህፃናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ይታያል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ በዳር የሚገኙ ቁጥሮች ግልባጭ ድምር የመሀለኛውን ቁጥር ይሰጠናል፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያው ባለሶስት ጎን 72+51+33=156 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የመጨረሻው 37+12+25=**74** ነው፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር ይሆናል፡፡




## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት እትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 3 | 15 | 4 |
| 7 | 38 | 5 |
| 3 | ? | 5 |

# የመዲናዋ የጥበብ ዳናዎች

**በአብርሃም ገብሬ**

አዲስ አበባ እንደ ስሟ “አዲስ አበባ” ሆና ለመታየት በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ውስጥ ትገኛለች። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በመዲናዋ እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማትና የከተማ መልሶ ማልማት ስራዎች የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ ለነዋሪዎቿና ለጎብኚዎቿ ሥነ-ውበታዊ (Aesthetic) ትርጉም እየሰጡ ይገኛሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ደግሞ የቅርጻቅርጽ ስራዎች እና የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ውጤቶች የከተማዋን ታሪክ፣ ባህልና የወደፊት ርዕይ የሚተርኩ “የዓለት ላይ ጥበባዊ ተራኪዎች” በመሆን ጎልተው ወጥተዋል። እነዚህ የጥበብ ውጤቶች ለከተማዋ ነዋሪና ጎብኚዎች ቀልብን ቆንጥጠው የሚይዙ የጥበብ ድልድዮች ሆነዋል።

የመዲናዋ የገጽታ ለውጥ መንገዶችን ከማስፋት ባሻገር ከተማዋን ወደ አንድ ግዙፍ የኪነ-ጥበብ ጋለሪነት እየቀየራት ይገኛል። በአሁኑ ወቅት እየተገነቡ ያሉ አዳዲስ ፓርኮች፣ ሙዚየሞችና አደባባዮች በቅርጻቅርጾች ሲያጌጡ፣ አዲስ አበባን በአህጉሪቱ ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ እነዚህ ስራዎች የከተማ ውበትን (Urban Aesthetics) በማሳደግ ረገድ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ሲሆን፣ ዜጎች ከከተማቸው ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያጠናክሩና ለአዲስ አበባ አዲስ ታሪካዊና ሥነ-ውበታዊ ማንነትን የሚያላብሱ ናቸው። እኛም በዚህ ጽሑፍ የእነዚህ አዳዲስ ቅርጻቅርጾች ጥበባዊ ፋይዳና ለከተማዋ የቱሪዝም ዕድገት ያላቸውን አስተዋጽኦ በጨረፍታ እንቃኛለን።

## የቅርጻቅርጽ ጥበብ እና የአዲስ አበባ የውበት ሽግግር

አና ጃንቻታ የተባሉ ምሁር “The Role of Public Visual Art in Urban Space Recognition” በሚል ርዕስ በፈረንጆቹ በ2010 በ‘ሪሰርች ጌት' ገጸ-ድር ላይ አንድ ጥናታዊ ጽሑፍ አሳትመዋል፡፡ በዚህ ጥናት ላይ እንደሰፈረው በከተማ ፕላን ውስጥ ቅርጻቅርጾች እንዲሁ ለዕይታ ማጌጫ ብቻ ሳይሆን፤ የዚያን ከተማ ማንነት የሚገልጹ፣ በህዝባዊ ስፍራዎች ህይወት የሚዘሩና የኪነ-ጥበብን እሴት ወደ አደባባይ የሚያወጡ ጥበባዊ ዕሴቶች ናቸው። ይሄን መነሻ በማድረግ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ አደባባዮች፣ የወንዝ ዳር ልማት ዳርቻዎች፣ መናፈሻዎችና አዳዲስ መንገዶች ዳር የሚቆሙ ቅርጻቅርጾች የከተማዋን የሥነ ውበት ገጽታ ከፍ አድርገውታል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በከተማዋ ውስጥ እየተሰሩ ያሉ ቅርጻቅርጾችና ክፍት የመዝናኛ ሥፍራዎች በከተማዋ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ለዐይን እረፍት የሚሰጡ፣ ለምናብ ደግሞ ጥልቅ ምስልን የሚከሰቱ መሆናቸው ከምሁሩ ሃሳብ መሳ ለመሳ የሚሄዱ ፕሮጀክቶች ያደርጋቸዋል።

ደራሲና የኪነ ጥበብ ሃያሲው ገዛኸኝ ድሪባ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጠው አስተያየት፣ ከዚህ ቀደም በከተማዋ የነበሩ ቅርጻቅርጾች በአብዛኛው በታሪክና በፖለቲካዊ ድሎች ላይ ያተኮሩ ነበሩ። አሁን ግን ዘመናዊነትን፣ ተፈጥሮን፣ የሰው ልጅን ጥረትና የሀገሪቱን ብዝሃነት የሚወክሉ ረቂቅ (Abstract) እና ተጨባጭ ስራዎች መበራከታቸው ከተማዋን የክፍት ሥፍራ ጋለሪ (Open-air Gallery) እያስመሰላት ይገኛል። ይህም ነዋሪው ከጥበብ ጋር በዕለት ተዕለት ውሎው እንዲገናኝና የሥነ-ውበት ግንዛቤው እንዲዳብር ያስችላል በማለት አጫውቶናል።

የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል በመዲናዋ የተሰሩ አዳዲስ ቅርጻቅርጾችን ባሰሰበት ጉብኝቱ፣ በአፍንጮ በር አካባቢ የሚገኘውን የወንዝ ዳርቻ ልማት ፓርክን ተመልክቷል። ቀደም ሲል የቆሻሻ መጣያ የነበረው ይህ ሥፍራ፣ ዛሬ አረንጓዴ ለብሶና በሥነ-ጥበብ ስራዎች ተውቦ ለከተማዋ ነዋሪዎችና ለጎብኚዎች ልዩ መስህብ ሆኗል። በፓርኩ ውስጥ የኢትዮጵያን ማህበረሰብ ማንነትና ከማህበረሰቡ ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸውን እንስሳት የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ቅርጻቅርጾች ዋጋ ተሰጥቷቸው በክብር ተገንብተዋል። ከዚህ በተጨማሪም የታላቁ ደራሲ ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር መታሰቢያ ሐውልት በዚህ ሥፍራ መገኘቱ፣ ለፓርኩ ጥበባዊና ታሪካዊ ግርማ ሞገስን አላብሶታል።

ይህ በአፍንጮ በር ዙርያ የታየው ለውጥ፣ በአግባቡ የለማ ሥፍራ እንዴት ወደ ትልቅ ሥነ-ጥበባዊና ሥነ-ውበታዊ ዕሴትነት ሊለወጥ እንደሚችል ትልቅ ማሳያ ነው። በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች በሥፍራው ሲዝናኑ፣ ቅርጻቅርጾቹን በአድናቆት ሲጎበኙና ለትውስታ የሚሆናቸውን ፎቶግራፎች ሲነሱ መመልከታችን፣ የከተማ ውበት ስራዎች ያላቸውን ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ፋይዳ ያረጋግጣል። በአንድ ወቅት የቆሻሻ መጣያና ሌባ ንብረት ቀምቶ ሮጦ ይደበቅበት የነበረ ሥፍራ ዛሬ ወደ ጥበብ ማዕከልነት ማደጉ፣ ለአዲስ አበባ የከተማ ውበት ሽግግር እንደ ስኬታማ ምሳሌ ሊወሰድ የሚችል ተሞክሮ ነው።

ደራሲና ሃያሲ ገዛኸኝ እንዳጫወተን የከተማ ውበት ከህንፃዎችና ከአደባባዮች ማሳመር የተሻገረ ትርጉም አለው። በቅርጻቅርጾችና በፓርኮች የተዋበች ከተማ ለነዋሪዎቿ አዎንታዊ ስሜትን ትፈጥራለች። ሰዎች ውብ በሆኑ አደባባዮችና ፓርኮች ውስጥ ሲንሸራሸሩ፣ ጥበብን ሲያደንቁና በጋራ ሲዝናኑ ማህበራዊ ትስስራቸው ይጠነከራል። ቅርጻቅርጾች ሰዎች የሚገናኙባቸው፣ ፎቶ የሚነሱባቸውና ትውስታ የሚፈጥሩባቸው “የማንነት መገለጫዎች” ይሆናሉ።

እኛም አፍንጮ በር አካባቢ ባለው ፓርክ ውስጥ ካየናቸው ቅርጻቅርጾች መካከል ፈረሶች ይገኙበታል፡፡ ፈረስና ጀግንነት ደግሞ በኢትዮጵያ ባህል ውስጥ የጠበቀ ትስስር አላቸው፡፡ በቀደመው ዘመን ሃገር በውጭ ጠላቶች ስትወረር ፈረሶች አብረው ዘምቷል፡፡ ስንቅና አስፈላጊ ግብዓቶችን ለጀግኖች አድርሰዋል። ቀደምት ነገስታት ቅጽል ስማቸው በፈረሳቸው ስም እስከመጠራት የደረሱት በዚህ ውለታቸው ምክንያት ይመስላል። ከዚህ አንጻር የፈረስ ቅርጻቅርጽ፣ አዲስ አበባ የታሪካዊ ጀግንነትና የክብር መዲና መሆኗን ይዘከራል። በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች የተሰሩት እነዚህ ቅርጻቅርጾች እንዲሁ የድንጋይ ወይም የብረት ስብስቦች ሳይሆኑ፣ የሀገሪቱን የነፃነት ተጋድሎና የአርበኝነት መንፈስ ወደ ዘመናዊው የከተማ ገጽታ ያመጡ ህያው ትረካዎች ናቸው። በከፍተኛ ጥበብ የተሰሩት እነዚህ ፈረስና ፈረሰኞች፣ ከተማዋ በዘመናዊነት ስትገነባ ታሪካዊ መሠረቷንና ማንነቷን ሳትረሳ መሆኑን ለነዋሪውና ለጎብኚው በዝምታ ያስረዳሉ።

ሌላው በከተማዋ ውስጥ ከሚታዩ የዱር እንስሳት መካከል ዋልያ ነው፡፡ ለአብነትም ሁለት ዋልያዎች ሲጋጠሙ የሚያሳየው ቅርጻቅርጽ፣ ከተማዋ ከተፈጥሮና ከዱር እንስሳት ሀብቷ ጋር ያላትን ቁርኝት የሚገልጽ ነው። ይህ ስራ በከተማዋ የኮንክሪት ህንፃዎች መካከል የተፈጥሮን ግርማ ሞገስ በማምጣት የዐይን እረፍትና ልዩ ስሜት ይፈጥራል። ዋልያ የኢትዮጵያ ብቻ ተወላጅ (Endemic) እንደመሆኑ፣ እንዲህ ያሉ ስራዎች በከተማዋ አደባባዮች ላይ መኖራቸው አዲስ አበባን የብዝሃ-ሕይወትና የብሔራዊ ኩራት መገለጫ እንድትሆን ያደርጋታል።

እነዚህ ቅርጻቅርጾች የተተከሉባቸው ቦታዎችና የተቀረጹበት ጥበባዊ ጥራት የከተማዋን ውበት ወደ ሌላ ደረጃ ያሸጋገሩ ናቸው። የቅርጻቅርጾቹ መጠን፣ አቀማመጥና የተሰሩበት ቁስ (Material) ከከባቢው አየርና ከሰማዩ ሰማያዊ ቀለም ጋር ተስማምተው እንዲታዩ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። ይህ ደግሞ አዲስ አበባን ለፎቶግራፍ ተስማሚ (Photogenic) ከማድረጉም በላይ፣ ማህበረሰቡ ጥበብን በቅርበት እንዲያደንቅና የከተማዋን ሥነ-ውበታዊ ለውጥ እንዲረዳ ያደርገዋል።

እነዚህ ምስሎች አዲስ አበባን የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የሚከናወነውን ስራ ተግባራዊ ውጤት ያሳያሉ። አንድ ጎብኚ በእነዚህ ግዙፍና ጥበባዊ ቅርጻቅርጾች ፊት ቆሞ ፎቶ ሲነሳ ወይም ትርጉማቸውን ሲረዳ፣ በከተማዋ ያለው ቆይታ ትርጉም ያለውና የማይረሳ ትውስታ የተሞላበት ይሆናል። እነዚህ የኪነ-ጥበብ ስራዎች መዲናዋን በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚናፈቅ ውበት ያላት “የጥበብ ከተማ” የማድረግ አቅም አላቸው።

## አዲስ አበባን እንደ ፓሪስ

የአዲስ አበባ የከተማ ውበትና የቅርጻቅርጽ ግንባታ ሂደት ጋር በተያያዘ፣ እንደ ትልቅ ተሞክሮ የምትወሰደውና በዘርፉ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምትታወቀው ከተማ ፓሪስ (ፈረንሳይ) ናት። ፓሪስ “የጥበብ መዲና” የምትባለው እንዲሁ ሳይሆን፣ የኪነ-ጥበብ ስራዎችን ከከተማ ፕላንና ከቱሪስት መስህብነት ጋር እንዴት ማቀናጀት እንደሚቻል ለዓለም ያስመሰከረች በመሆኑ ነው፡፡

“Paris Downtown Community Improvement Plan Application for Financial Incentives” በሚል ርዕስ ‘ብራንት ሲኤ' የተባለ ገጸ-ድር በፈረንጆቹ ጥቅምት 2014 አንድ ጥናት አስነብቦ ነበር፡፡ በዚህ ጥናት መሰረት፣ የፓሪስ ትልቁ ተሞክሮ የቅርጻቅርጽ ስራዎችንና የኪነ-ጥበብ ውጤቶችን በየመንገዱ፣ በየፓርኩና በየአደባባዩ በመስራት ከተማዋን ወደ አንድ ግዙፍ ክፍት የጥበብ ሙዚየም መለወጧ ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ ‘ቱይለሪ ጋርደን' (Tuileries Garden) ያሉ ታዋቂ ፓርኮች በውስጣቸው ከመቶ በላይ ጥንታዊና ዘመናዊ ቅርጻቅርጾችን የያዙ ሲሆን፣ ይህም ነዋሪውና ቱሪስቱ በከተማዋ ሲንቀሳቀስ ጥበብን እንደ አየር እንዲተነፍሳት ያደርጋታል። አዲስ አበባም በአሁኑ ወቅት የጀመረችው መንገዶችና ፓርኮችን በቅርጻቅርጽ የማስዋብ ስራ፣ ልክ እንደ ፓሪስ ከተማዋን ለዐይን የምትማርክና ሥነ ጥበባዊ ማዕከል የማድረጊያ ትክክለኛ መንገድ ነው፡፡

በሌላ በኩል፣ ፓሪስ የከተማ ውበትን ከቱሪዝም ኢኮኖሚ ጋር በማስተሳሰር ረገድ ውጤታማ መሆኗን ማየት ይቻላል። በከተማዋ የሚገኙት ግዙፍ የኪነ-ጥበብ ስራዎችና ሙዚየሞች በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጎብኚዎችን የሚስቡ የኢኮኖሚ ምንጮች ናቸው። አዲስ አበባም አዳዲስ ሙዚየሞችንና ቅርጻቅርጾችን በስትራቴጂያዊ ቦታዎች ላይ መገንባቷ፣ ከተማዋን ልክ እንደ ፓሪስ ሁሉ የዓለም ቱሪስቶች የሚናፍቋት የባህልና የኪነ-ጥበብ ማዕከል ለማድረግ ትልቅ ዕድል ይሰጣታል።

በአጠቃላይ አዲስ አበባ እየተላበሰች ያለችው አዲስ ገጽታ የጥበብ፣ የታሪክና የዘመናዊነት ቅልቅል ነው። አዳዲስ ቅርጻቅርጾች፣ ፓርኮችና ሙዚየሞች የከተማዋን ሥነ-ውበታዊ እሴት ከመጨመር ባለፈ፣ ለኢኮኖሚና ለቱሪዝሙ እድገት የጀርባ አጥንት የመሆን አቅም አላቸው። አሁን እንደምናየው ጥበብ በአደባባይ ስትወጣ፣ ከተማዋ በዝምታ መናገር ትጀምራለች፡፡ ያ ደግሞ ለአዲስ አበባ አዲስ የዕድገት ምዕራፍ ነው ሊባል ይችላል።



ፎቶ- ከፋይል
አዲስ አበባን ያስዋቡት አዳዲስ የሥነ ጥበብ አሻራዎች

# የአፍሪካን እውነተኛ መልክ የማሳየት ኃላፊነት

- የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ የአህጉሪቱን እውነተኛ ገጽታ ለዓለም ማህበረሰብ የማስተዋወቅ ዕድል እንደሚፈጥር ተጠቁሟል




ፎቶ- ከገፀ ድር
በድምሩ 321 ሚሊዮን ተከታዮች ያሏቸው 61 የማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች የአዲስ አበባን የልማት ስራዎች ጎብኝተዋል

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የመጀመሪያው የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ (ASMIS 2026) ሲጀመር፣ ተሳታፊዎቹ የረገጡት መሬት የአህጉሪቱ የነፃነት ተምሳሌት የሆነውን የዓድዋን ታሪክ የሰነደ ስፍራ ነው። ይህ የአጋጣሚ ነገር አይደለም፤ ኢትዮጵያውያን በጦር ሜዳ ያጸኑትን የአፍሪካ ኩራት፣ የዛሬው ትውልድ በዲጂታሉ ዓለም የዲጂታል ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ መነሳቱን የሚያሳይ ትልቅ ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

አዲስ አበባ የ2026ቱን የመጀመሪያው የአፍሪካ የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ (ASMIS) አሰናድታለች። በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚሊዮኖች ተከታይ ያሏቸውን የአህጉሪቱ ግንባር ቀደም የዲጂታል ታሪክ ተራኪዎች ያገናኘው መድረክ፣ ከቁጥር የተሻገረ ትልቅ ዓላማን ሰንቋል። የአህጉሪቷ ልጆችም የውጭ አካላት የአፍሪካን ታሪክ በማጠልሸት የሚፈጥሩትን የተሳሳተ ስዕላዊ ዕይታ ለማረም ማህበራዊ ሚዲያን ለበጎ ዓላማ መጠቀም እንደሚጠበቅባቸው ነው ያረጋገጡት። የአህጉሪቱን ታሪክ ከውጭ በሚመጡ አካላት የሚቃኙበትን ስሁት ትርክት ለማስተካከልም መድረኩ ከውክልና የተሻገረ የተጽዕኖ፣ የቁጥርና የወደፊት አመለካከትን የሚቀርፅ መሆኑ ይታመናል።

በዚህ ጉባኤ ላይ የታደሙት ከ30 የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ 61 ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ብቻ አይደሉም፤ ከጀርባቸው ያሉት 321 ሚሊዮን ተከታዮች ናቸው። እነዚህ ወጣቶች በአንድ ቪዲዮ፣ በአንድ ፎቶግራፍ ወይም በአንድ አጭር ጽሑፍ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን አስተሳሰብ የመቀየር አቅም አላቸው።

ከእነዚህ ጎን ለጎን 150 ሚሊዮን ተከታዮች ያሏቸው 120 ኢትዮጵያውያን የይዘት ፈጣሪዎች መገኘታቸው፣ ኢትዮጵያ በአህጉሪቱ ዲጂታል እንቅስቃሴ ውስጥ ያላትን ጉልህ ሚና ያሳያል። በአጠቃላይ ወደ ግማሽ ቢሊዮን የሚጠጋ ተከታይ ያላቸው እነዚህ “የአዲሱ ዘመን አምባሳደሮች” በአዲስ አበባ መሰብሰባቸው፣ ከተማዋ የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን ወደ ዲጂታሉ ዓለም እያሸጋገረች መሆኑን ያረጋግጣል።

ለበርካታ አስርት ዓመታት የአፍሪካ ታሪክ ሲነገር የኖረው በሌሎች ነበር። ረሃብ፣ ጦርነትና ድህነት ብቻ የአህጉሪቱ መገለጫ ተደርገው ሲቀርቡ ቆይተዋል። የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ (ASMIS 2026) ይህንን የተዛባ ምስል ለመስበር የተነሳ ሲሆን፣ “የአፍሪካን እውነተኛ ገጽታ ለዓለም ማስተዋወቅ” የሚለው መሪ ቃል፣ ተጽዕኖ ፈጣሪዎቹ ካሜራዎቻቸውን ወደ አህጉሪቱ ልማት፣ ጥበብ፣ ፈጠራና ውበት እንዲያዞሩ ጥሪ አቅርቧል። ጉባኤው በንግግር ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ ተሳታፊዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ ያደረጉት ጉብኝት አንዱ የዚሁ አካል ነው። አዲስ አበባ የምታሳየው እድገት፣ የመሠረተ ልማት ግንባታና የኮሪደር ልማት ውጤቶች በእነዚህ ፈጣሪዎች አማካኝነት ለዓለም ሲጋሩ፣ ስለ ኢትዮጵያም ሆነ ስለ አፍሪካ ያለው አመለካከት በአዎንታዊ መልኩ እንዲቀየር ያደርጋል።

አዲስ አበባም ለጉባኤው ተሳታፊዎች ያደረገችው አቀባበልና ጉብኝት የአፍሪካ መዲና የሚለውን ስያሜዋን በተግባር የሚያጎላ ነው። ተጽዕኖ ፈጣሪዎቹ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ተዘዋውረው ያዩት ግንባታ፣ የአረንጓዴ ልማትና የከተማ ውበት፣ አፍሪካ ራሷን ለመለወጥ ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው። ይህ ጉብኝት ለኢትዮጵያ ትልቅ የቱሪዝም ማስተዋወቂያ እድል ነው። 120 ኢትዮጵያውያን የይዘት ፈጣሪዎች ከሌሎች አህጉራዊ ወንድሞቻቸው ጋር በመቀናጀት “አዲስ የዲጂታል ታሪክ” ለመጻፍ መዘጋጀታቸው፣ በሀገራት መካከል ያለውን የዲጂታል ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግረዋል።

የትርክት ባለቤትነት (Narrative Ownership) የዚህ ጉባኤ ዋነኛ ግብ ነው። አፍሪካውያን የራሳቸውን ታሪክ ራሳቸው ካልነገሩ፣ ሌሎች እንደፈለጉ ይተርኳቸዋል። የዲጂታል መድረኩ ደግሞ ይህንን ለማድረግ ከማንኛውም ዘመን የተሻለ እድል ፈጥሯል። ጉባኤው ተጽዕኖ ፈጣሪዎቹ እንዴት በጋራ መሥራት እንዳለባቸው፣ አህጉራዊ አንድነትን እንዴት እንደሚሰብኩና የኢኮኖሚ ትስስርን በማህበራዊ ሚዲያ እንዴት እንደሚያሳድጉ ይመክራል። ይህ የባለቤትነት ስሜት የአፍሪካን ነፃነት በዲጂታል ሉል የማረጋገጥ ያህል ትልቅ ትርጉም እንዳለው ተገልጿል፡፡

የፐልስ ኦፍ አፍሪካ አስተባባሪ በረከት ሲሳይ ስለጉባኤው በሰጡት ማብራሪያ፣ የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ (ASMIS 2026) ዋነኛ ዓላማ በተፅዕኖ ፈጣሪዎች መካከል ትብብር በመፍጠር በአፍሪካ ጉዳዮች ላይ የጋራ ድምጽ ማሰማት የሚችሉበትን ዕድል ማመቻቸት ነው ብለዋል። የአፍሪካን ትክክለኛ ገፅታ ለተቀረው ዓለም ለማስተዋወቅ ብሎም ስለአፍሪካ በተደጋጋሚ የተነዛውን የተሳሳተ ትርክት ለመቀየር ማህበራዊ ሚዲያ የሚኖረውን አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑን ገልፀዋል። ጉባኤው በአፍሪካዊያን መካከል የጋራ መግባባትና አንድነት ለመፍጠር የማኅበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች በጋራ የሚሰሩበትን ዕድል ለማመቻቸት መልካም አጋጣሚ እንደሚሆንም ጠቁመዋል።

የአፍሪካ የማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ጉባኤ ተሳታፊዎችም “ታሪካችንን በራሳችን አንደበት የምንነግርበትና የምንሰንድበት ጊዜ አሁን ነው” ይላሉ፡፡ እንደዚሁም የአፍሪካ የማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ ዕርስ በዕርስ ለመማማር እና ልምድ ለመለዋወጥ ትልቅ እድል ይዞ መምጣቱን ተሳታፊዎች ይገልጻሉ። “ይህን የአፍሪካውያንን ዘመን እውነታ እኛ አፍሪካውያን ልንማርበትና ለተቀረው የዓለም ማህበረሰብ የምናስተዋውቅበት ታሪካዊ አጋጣሚን አዲስ አበባ ፈጥራልናለች” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡

ከደቡብ ሱዳን የመጣችው የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪ አዲት ሱዛን ሰዎች ብዙ ጊዜ የአፍሪካን መጥፎ ገፅታ እንጂ ያላትን አቅም፣ ጸጋና በረከት አይነግሩም ብላለች፡፡ አፍሪካ ከዓለም ማዕዘናት ሁሉም ሊጎበኟት የሚገባ ውብ አህጉር መሆኗን በመጥቀስ ጉባኤው የአህጉሪቱ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን ወደ አንድ ማምጣቱ ያጋራ ትስስርን እንደሚያጠናክር ገልጻለች፡፡ ፐልስ ኦፍ አፍሪካ ከኤ.ጂ.ኤ የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዝ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት ጉባኤ የማህበራዊ ሚድያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን አንድ ማድረግ ያስችላልም ብላለች።

ማላዊያዊው ኬቨን ጉምቢም በበኩሉ፣ አፍሪካ ሁሉም ሀብቶች፣ የሚያምሩ ታሪኮች እና የውብ ጥበቦች አድባር የሆነች አህጉር መሆኗን ገልጿል፡፡ “ብዙውን ታሪካችንን ሌሎች ሲነግሩን ቆይተዋል” ያለው የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪው፣ ታሪካችንን በራሳችን አንደበት የምንነግርበትና የምንሰንድበት ጊዜ አሁን ነው ብሏል፡፡

የአፍሪካ የማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ ይዞት የመጣው ሀሳብ ግሩም መሆኑን የገለጸው ደግሞ ከዩጋንዳ የመጣው የማህበራዊ ሚድያ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሞሰስ ኬዩኔ ነው። አፍሪካውያን በዚህ መንገድ መገናኘታቸው ዕርስ በዕርስ እንዲተዋወቁ፣ ባህላቸውን እንዲጋሩ እና እንዲያሳድጉ መልካም አጋጣሚ መሆኑን ገልጿል።

የማህበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች እንደገለፁት ተዘዋውረው የተመለከቷቸው የልማት ስራዎች የኢትዮጵያ ሁለተናዊ ፈጣን እድገት ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን ኩራት፣ የአፍሪካውያን የቀጣይ ጉዞ የተመላከቱበት ስለመሆኑ አንስተዋል፡፡ “ይህን እውነታ እኛ አፍሪካውያን ልንማርበትና ለተቀረው የዓለም ማህበረሰብ የምናስተዋውቅበት ታሪካዊ አጋጣሚ በመሆኑ ሙያችንን በመጠቀም የተጣለብንን አፍሪካዊ ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅብናል” ሲሉም ገልፀዋል።

የአፍሪካን እውነተኛ ገጽታ ለዓለም ለማስተዋወቅና የዲጂታል ትርክቱን በባለቤትነት ለመምራት ያለመው የመጀመሪያው የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ (ASMIS 2026) በአዲስ አበባ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ለሁለት ቀናት ተካሂዷል። ተሳታፊዎች ከጉባኤው ጎን ለጎንም ሰው ሰራሽ አስተውሎት ማዕከልን፣ ጉለሌ የእንጀራ ማዕከል፣ ዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማቶች፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች፣ አራዳ ፓርክ፣ አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል፣ ካዛንቺስ የሚገኘው ስፖርት ፓርክ እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ የልማት ስኬቶች የተጎበኙ ሲሆን፣ ኢትዮጵያውያኑ ታዋቂ የሶሻል ሚዲያ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ጭምር በጉብኝቱ ተሳትፈዋል።

በአዲስ አበባው የዓድዋ ድል መታሰቢያ የተካሄደው ይህ የመጀመሪያው የአፍሪካ ማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ጉባኤ፣ አህጉሪቱ በዲጂታሉ ዓለም የነቃና የተደራጀ ድምጽ እንዲኖራት ትልቅ መሠረት ጥሏል። የይዘት ፈጣሪዎች ከአዲስ አበባ ይዘውት የሚወጡት ትርክት፣ የአፍሪካን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ በአህጉሪቱ ወጣቶች መካከል ያለውን ትስስርና የአንድነት ስሜት የሚያጠናክር ነው። አዲስ አበባም የአፍሪካ መዲናነቷን በፖለቲካዊ ዲፕሎማሲ ብቻ ሳይሆን፣ በዘመኑ የዲጂታል ዲፕሎማሲም ጭምር ዳግም አረጋግጣለች።

በጉባኤው የተገኙት ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ወደየሀገራቸው ሲመለሱ የሚዘሩት የአዎንታዊነት ዘር ለነገዋ የበለጸገች አፍሪካ ግንባታ ትልቅ ግብዓት እንደሚሆን ይጠበቃል። እንደዚሁም የኢትዮጵያን እንግዳ ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን፣ የአፍሪካን አዲስ ተስፋና ብሩህ ገጽታ በሞባይላቸውና በኮምፒውተራቸው ጭነው ይሄዳሉ። አዲስ አበባ ዛሬም እንደ ትናንቱ የአፍሪካን ድምጽ ለዓለም የምታሰማበት፣ የጥቁር ሕዝቦች የዲጂታል ነፃነት ጎህ የሚቀድበት ማዕከል ሆና ትቀጥላለች።

# ልጆች፤ ገጠመኞቻችሁን ለቤተሰብ የመንገር ልምዳችሁ ምን ይመስላል?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? በዕለት ውሏችሁ ምን አጋጥሟችሁ የውቃል? ገጠመኞቻችሁን ለቤተሰብ የመንገር ልምዳችሁስ ምን ይመስላል፡፡ ምንስ ጥቅም አስገኘላችሁ? በዛሬው ዕትም ይዘንላችሁ የቀረብነው ርዕሰ ጉዳይ በውሏችሁ ስለሚገጥሟችሁ ገጠመኝ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጓደኞቻችሁ ተሞክሯቸውን እንደሚከተለው አቅርበውላችኋል፡፡

ማርያማዊት ሃይሉ እባላለሁ፡፡ የምኖረው ከእናቴ ጋር ነው፡፡ በውሎዬ የሚያጋጥሙኝን ሁሉ ለእናቴ ሳልደብቅ እነግራታለሁ፡፡ ለምሳሌ ጓደኞቼ የወር አበባ ሲያዩ ሳጫውታት ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብኝ ትመክረኝ ነበር፡፡ በዚህም በእኔ ላይ ሲከሰት ምንም ሳልፈራና ሳልሳቀቅ እንዳስተናግድ አድርጎኛል፡፡ ውሎዬን መናገሬ ጥሩውን እንድከተልና የማይጠቅመኝን ደግሞ እንድተው ረድቶኛል፡፡

ልዑል ደመና እባላለሁ፡፡ የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ በየቀኑ በትምህርት ቤትም ሆነ በሰፈር ከጓደኞቼ ጋር የሚገጥመኝን ለቤተሰቤ እናገራለሁ፡፡ ለቤተሰቤ በመናገሬ ችግር ውስጥ እንዳልገባ ረድቶኛል፡፡ በቤተሰቦቼ ምክርም ከጓደኞቼ ጋር ተስማምቼ እና ተግባብቼ ጓደኝነቴን እንድቀጥል አድርጎኛል። የገጠሙኝን መጥፎ እና ጥሩ ነገሮችን እንድለይም ረድቶኛል፡፡

ሱመያ መሃመድ እባላለሁ፡፡ የ6ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን 12 ዓመቴ ነው፡፡ በትምህርት ቤት አንዳንድ ተማሪዎች ትምህርታቸውን



ፎቶ፡- በገነት ወንድሙ

ሱመያ መሃመድ — ልዑል ደመና — ማርያማዊት ሃይሉ

ትተው ሲወጡ እመለከታለሁ፡፡ እኔም አንዳንድ ተማሪዎች ተገቢ ያልሆነ ባህርይ አሳይተውኝ ያውቃል፡፡ እነዚህን እና ሌሎች ገጠመኞቼን የምነግረው ለእናቴ ነው፡፡ ለእናቴም ከምነግራት ገጠመኞች በመነሳት እንዴት ከገጠሙኝ ችግሮች መራቅ እና መጠንቀቅ እንዳለብኝም ትመክረኛለች፡፡ እኔም ጥሩ ገጠመኝን በመጠቀም፤ ከመጥፎው ደግሞ ራሴን ጠብቄ እንቀሳቀሳለሁ፡፡

የውሎ ገጠመኜን መናገሬ ችግሩ ለነገ እንዳይደገም እና እንድጠነቀቅ ረድቶኛል። በሴቶች ላይ ሊገጥሙ የሚችሉ ነገሮችን እንዳውቅ አድርጎኛል። ምንም ነገር ቢገጥመኝም ማልቀስና መደንገጥ እንደሌለብኝ ተረድቼበታለሁ፡፡

ልጆች እንዴት ናችሁ፡፡ ወይዘሪት ህይወት አየለ እባላለሁ፡፡ ሁለንተናዊ የልጆች እድገት ባለሙያ ነኝ። ዛሬ የምነግራችሁ በእለት ተዕለት እንቅስቃሴያችሁ ወይም ውሏችሁ ስለሚገጥሟችሁ ገጠመኞች ነው፡፡ እነዚህም ገጠመኞች ጥሩም መጥፎም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ጥሩ ገጠመኞች የምንላቸው ከአዳዲስ ጓደኞቻችሁ ጋር መገናኘት፣ ያላችሁን ነገር መካፈል፣ ከሰዎች ጋር በሃሳብ መግባባት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ልጆች በቀን ውሏችሁ ጥሩ ብቻ ሳይሆን መጥፎ ገጠመኞችም ሊኖሯችሁ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ገጠመኞች የመገለል፣ በትምህርታችሁ ዝቅተኛ ውጤት ማስመዝገብ፣ የመሰደብ፣ ፀብ ወይም መደባደብ፣ በሰውም ይሁን በመኪና አደጋ አካላዊ ጉዳት የመድረስ፣ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት፣ አድሏዊ ነገሮች መፈፀም፣ የማያስፈልጉ ንግግሮች እንደ ሰነፍ፣ አታውቅም አይገባህም የሚሉ ነገሮች በሙሉ የሚያጋጥሙ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ነገሮች እንደሚገጥሟችሁም መረዳት ተገቢ ነው፡፡


እነዚህ ነገሮች ሲገጥሟችሁ ለቤተሰቦቻችሁ መናገር አለባችሁ፡፡ መናገራችሁ ደግሞ የተለያዩ ጥቅሞችን ያስገኙላችኋል፡፡ የመጀመሪያው ጥቅሙ ከከፉ ነገሮች ወይም ከጉዳት እድትጠበቁ ያደርጋችኋል፡፡ በራስ መተማመናችሁ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋችኋል። ጥሩ ስነ ምግባር ይዛችሁ እንድታድጉ ያግዛችኋል፡፡ እንዳትከፉና ደስተኛ እንድትሆኑም ይረዳችኋል፡፡

ወላጆቻችሁ ወይም ቤተሰቦቻችሁ አዳማጮቻችሁ፣ ጠባቂዎቻችሁ እንዲሁም መጥፎ ነገር እንዳይገጥማችሁ የሚንከባከቧችሁ ናቸው፡፡ ለዚህም ችግሮቻችሁን ዛሬ እኮ እንደዚህ ገጠመኝ፣ ጓደኛዬ እንዲህ አለኝ በማለት በግልፅ ሳትፈሩ ልትነግሯቸው ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ነው ልክ የሆነውንና ያልሆነውን ምክር እንድታውቁ የሚያግዛችሁ፡፡ እያደጋችሁ ስትመጡም በአካላችሁ ላይ የሚመጣውን አካላዊ ለውጥ ሳትፈሩ ብትነግሯቸው ተጠቃሚ ትሆናላችሁ፡፡

በየቀኑ የሚገጥሟችሁ መጥፎ ገጠመኞችን አልቅሳችሁ ወይም አኩርፋችሁ እንደቀላል ማለፍ የለባችሁም፡፡ እነዚህን ነገሮች መናገር እና መፍትሄ ማግኘት መቻል አለባችሁ። ካልተናገራችሁ ራሳችሁን እንድትጠሉ፣ ሌሎችን እንዳታምኑ፣ መጥፎ ስነምግባር እንዲኖራችሁ ያደርጋችኋል፡፡ ለጉዳት እንድትዳረጉም ትሆናላችሁ፡፡

ይህን አታደርጉ የሚሏችሁ ሊጠቅሟችሁ እንጂ ሊጎዷችሁ ባለመሆኑ ምክራቸውን መስማትና ተግባራዊ ማድረግ ከእናንተ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ የእለት ገጠመኞቻችሁን ቤተሰቦቻችሁ ቢጠይቋችሁም ባይጠይቋችሁም የማውራት ልምድ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሰው ፈረሱ ጠፍር ልጓሙ ፤ ምንድን ነው?**

**መልስ፡-** ለ .እንስራ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**የሳር ግብስብሱ፤ ጉብ ይላል እንደ ንጉሱ ምንድን ነው?**

ሀ. ከምር

ለ. ድርቆሽ

ሐ. ሞሰብ

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት ጅምር

- **በአገልግሎቱ ሕብረተሰቡ በጣም ደስተኛ ሆኗል**

**በደረጀ ታደሰ**

በአዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ ዲጂታል አገልግሎት ሲጠቀም ያገኘናቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የህጻናት ሕክምና ስፔሻሊቲ የ3ኛ ዓመት ተማሪ የሆኑት ዶክተር ወርቁ አድማሱ ናቸው፡፡ እሳቸው ወደ አዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ ዲጂታል አገልግሎት የመጡት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን፣ ስለመጡበት ምክንያት እና የአገልግሎት ሁኔታውን አስመልክቶ በሰጡት አስተያየት፤ "ወደዚህ የመጣሁት ቲን ነምበር ለማውጣት ነው፡፡ የሕክምና ስፔሻሊቲ ትምህርት ለማጠናቀቅ ለሠራሁትን ጥናት (Research) የሚከፈል ገንዘብ አለ፡፡ ክፍያው በመንግስት የፋይንናስ ስርዓት ውስጥ ማለፍ ስላለበት የግድ ቲን ነበር ማውጣት አለብኝ፡፡ ለዚህ ደግሞ ፈጣንና ጥራት ያለው አገልግሎት የማገኘው በአዲስ መሶብ በመሆኑ፤ ወደዚህ መጣሁ፡፡ ምርጫዬም ትክክል ነበር እና አስፈላጊ ሰነድና መረጃዎችን አቅርቤ ከ10 ደቂቃ ባነሰ ጊዜ ውስጥ አገልግሎት ማግኘት ችያለሁ፡፡"

ዶክተር ወርቁ አክለው እንደገለጹት፤ "የተለያዩ ተቋማት የሚያቀርቧቸውን አገልግሎቶች በአንድ ላይ በማሰባሰብ እና በማስተሳሰር፣ ዘመናዊና ዲጂታል በሆነ መልኩ መሰጠት መቻሉ የሚደነቅና የሚበረታታ ነው፡፡ ይህ አገልግሎት የበለጠ ወደ ተገልጋዩ እንዲደርስ የተንቀሳቃሽ አዲስ መሶብ መጀመሩ ደግሞ የአገልግሎቱን የመሻሻል ፍጥነት ያሳያል፡፡"

አቶ ሚልኪያስ ወርቁ፣ በአዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ ዲጂታል አገልግሎት ተጠቃሚ ከሆኑ የመዲናዋ ነዋሪዎች መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ነዋሪነታቸው በአራዳ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ አራት ሲሆን፤ የመጡበት ምክንያት የተሽከርካሪ ቦሎ ለማደስ ነው፡፡ ስለ አገልግሎት አሰጣጡ እና ስለተፈጠረባቸው ስሜት አስመልክተው ሲገልጹ፤ "አገልግሎት አሰጣጡ በጣም ቀልጣፋና ደስ የሚል ነው፡፡ በቀደሙት ጊዜያት በመንግስት ተቋማት መገልገል በጣም አድካሚ፣ አሰልቺና የሚያስመርር ነበር፡፡ ለትንሽ ጉዳይ ወደተለያዩ ተቋማት መሄድ፣ ለጊዜ ብክነትና ለከፍተኛ ወጪ መዳረግ ልምድ ነበር፡፡ አሁን ላይ አዲስ መሶብ ለዚህ ችግር ወሳኝ መድሃኒት ሆኗል፡፡ እንዲህ ያለው በተንቀሳቃሽ አውቶብስ የሚሰጥ አገልግሎት መጀመሩ ደግሞ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ መንቀሳቀስ ለማይችሉ፣ ሥራ ለሚበዛባቸው ሰዎች በጣም ጥሩ ነው፡፡" ብለዋል፡፡ አያይዘውም፤ ይህን ዓይነት አገልግሎት ለማስፋት መንግስት የጀመረውን ሥራ ማጠናከር እንደሚገባው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአዲስ መሶብ የብሔራዊ መታወቂያ (ፋይዳ) በተመለከተ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያገኘነው ባለሙያ ወጣት ኤፍሬም አሰፋ፣ ወደ አዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል መንግስት



ፎቶ- ከገፀ ድር
ተገልጋዮች በተንቀሳቃሽ አዲስ መሶብ ሲገለገሉ

አገልግሎት ተቋም የተቀላቀለው፤ ተቋሙ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በይፋ ሥራውን በጀመረበት ዕለት ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሥራ ክፍሉ በታላቅ ዲሲፒሊንና የአገልጋይነት መንፈስ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ የአዲስ መሶብ ተቋም ተመርቆ ወደ ሥራ ከገባበት ዕለት አንስቶ፤ አገልግሎቱን በጥራት፣ በመጠንና በፍጥነት እያሳደገ ሕብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል፡፡ በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ይታይ የነበረውን ጉድለት ለመቀነስ ተችሏል፡፡ የተገልጋይ እርካታ ተሻሽሏል፡፡ ተደራሽነቱ እያደገ መጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በቅርቡ እንደከተማ አስተዳደር በተጀመረው የተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት መስጫ አውቶብስ ውስጥ ከብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ (ፋይዳ) ጋር የተያያዘ አገልግሎቶችን እየሰጠ ነው፡፡

ባለሙያው አክሎ እንዳብራራው፤ ዜጎች የመንግስት አገልግሎቶችን በጥራት፣ በፍጥነትና በፍትሃዊነት የማግኘት መብት አላቸው፡፡ አገልግሎቶቹን በአግባቡ የማቅረብ ግዴታ ደግሞ የመንግስት ተቋማት ነው፡፡ አዲስ መሶብም ይህንን ነው እያደረገ ያለው፡፡ በሕንፃ ተቋማት ውስጥ ከሚሰጡ ዘመናዊና የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች በተጨማሪ፤ በተንቀሳቃሽ አውቶብስ አማካኝነት አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ መጀመሩ በሕብረተሰቡ ዘንድ ደስታን ፈጥሯል፡፡

ስለ አዲስ መሶብ ተቋም አገልግሎት የማህበረሰቡ ግንዛቤ በየጊዜው እያደገ መምጣቱ፣ በአዲስ መልክ ወደ ሥራ በገባው የተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ ዲጂታል አገልግሎት ላይ መጥቶ ለመገልገል ችግር እንዳይገጥም ማገዙንም ጠቁሟል፡፡

ተደራሽነቱን በከፍተኛ ደረጃ እያሳደገ የመጣውን የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት፣ በተለይም ከተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ ዲጂታል አገልግሎት ጅምር እንቅስቃሴ ላይ በማተኮር ማብራሪያ እንዲሰጡን የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተርና የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ቴዎድሮስ ማስረሻ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ እንዳስረዱት፤ የተንሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት ወደ ሥራ የገባው በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ቁርጠኛ አመራር አማካኝነት ነው፡፡ ይህ አገልግሎት እንደ አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን እንደ አገርም የመጀመሪያው ነው። የአዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ አገልግሎት ሥራውን የጀመረው የስምንት ተቋማትን አገልግሎቶች በማካተት ነው፡፡ እነዚህም፡- የገቢ አገልግሎት (አዲስ ቲን ማውጣት)፣ የንግድ አገልግሎት (አዲስ ንግድ ፈቃድ ማውጣት እና ማደስ)፣ የጤና (ለመንጃ ፈቃድ አካላዊ የጤና ምርመራ)፣ የሲቪል ምዝገባ (የዲጂታል መታወቂያ ዕድሳት እና ልደት ሰርተፍኬት)፣ የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ (የመንጃ ፈቃድ እና የቦሎ ዕድሳት)፣ የኢትዮ ፖስታ (የመንገድ ፈንድ ክፍያ)፣ የብሔራዊ መታወቂያ (የፋይዳ አዲስ ምዝገባ እና የመረጃ እርማት) እንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት (የቅድመ ክፍያ ካርድን መሙላት) ናቸው፡፡

ለተቋማዊ አገልግሎት ታስቦ በተዘጋጀ አውቶብስ አማካኝነት እየቀረበ ያለው የአዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ አገልግሎት፣ አንድ ዘመናዊ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ማዕከል ሊኖረው የሚችለውን ገፅታ የተላበሰ፣ ምቹ የሆነ፣ አስፈላጊ መሰረተ ልማት የተሟላለት መሆኑን የጠቆሙት አቶ ቴዎድሮስ፤ "አውቶብሱ የኤሌክትሪክ ኃይልን የሚጠቀም ሲሆን፣ በአውቶብሱ ውስጥ ለሚሰጡ ዲጂታላይዝድ አገልግሎቶች ኮምፒውተሮችን፣ ላፕቶፖችን እንዲሁም ተያያዥ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ለማንቀሳቀስ የሚውለውን የኃይል አቅርቦት በአውቶብሱ ላይ በተገጠሙ የጸሐይ ኃይል ማመንጫ ፓኔሎች አማካኝነት ከፀሐይ ኃይል ይጠቀማል፡፡ በተመሳሳይ፤ በየትኛው የከተማዋ አካባቢ ተንቀሳቅሶ የሚሰጠው አገልግሎት፣ ከዋና ማዕከል ጋር ቀጥታ ትስስር እንዲኖረው የሚያስችል የኢንተርኔት ኔትዎርክ አማራጭም ተሟልቶለታል። ሦስት የተለያዩ ሲስተሞች በአውቶብሱ ውስጥ ለአገልግሎት ውለዋል። እነዚህም ሲስተሞች፡- የሰነዶች (የዶክዩመንት ማኔጅመንት)፣ የኪው ማኔጅመንት(ተገልጋዮች እንደ አመጣጣቸው የወረፋ ቲኬት የሚይዙበት) እና የተገልጋይ ግብረመልስ(የፊድባክ) ሲስተሞች ናቸው፡፡ ከሠው ኃይል ጋር በተያያዘም በልምድም፣ በስልጠናም ብቁ የሆኑ ባለሙያዎች ተሟልቷል፡፡" በማለት አብራርተዋል፡፡

የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት በየትኛውም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ነዋሪ፣ የሚኖርበት ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ሳይወስነው ባገኘው አጋጣሚ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ዘመናዊ አገልግሎት እንዲያገኝ ምቹ ሁኔታ መፍጠርን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያነሱት አቶ ቴዎድሮስ፤ በተመሳሳይ የተንቀሳቃሽ አዲስ መሶብ አገልግሎትም ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት አጋዥ ተደርጎ የቀረበ አሠራር መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት ትኩረቱ፡- የመንግስት አገልግሎትን ለማግኘት(በሥራ ባሕሪያቸው፣ በቦታ ርቀት እና መሰል ምክንያት) የሚቸገሩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ማድረግ ላይ ነው፡፡

ኃላፊው አክለው እንደገለጹት፤ የተንቀሳቃሽ የአዲስ መሶብ አገልግሎት ሥራውን የጀመረው፣ በይፋ ተመርቆ ለአገልግሎት ከበቃበት ዕለት ጀምሮ ነው። በመጀመሪያው ዕለት በዋና መሥሪያ ቤቱ መገናኛ አካባቢ ለተገልጋዮች አገልግሎት ሰጥቷል፡፡ ከዚያ በኋላም፤ በከተማዋ በሚገኙ ክፍለ ከተሞች በመንቀሳቀስ፣ በተመረጡና ተገልጋይ በሚበዛባቸው አካባቢዎች አገልግሎቱን ማቅረቡን ቀጥሏል፡፡ በዚሁ መሰረት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ-በጀርመን አደባባይ አካባቢ፣ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ-በአፍሪካ ኮንቬንሽን ማዕከል አካባቢ፣ በየካ ክፍለ ከተማ- መገናኛ እና ሾላ አካባቢ፣ በኮልፌ ክፍለ ከተማ- በጦር ኃይሎች አደባባይ አካባቢ፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ- ሽሮሜዳ አካባቢ፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ-መስቀል አደባባይ እና ዑራኤል አካባቢ፣ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ-ጀነራል ዊንጌት አደባባይ አካባቢ፣ በልደታ ክፍለ ከተማ- ሜክሲኮ አደባባይ አካባቢ አገልግሎቱን በተከታታይነት አቅርቧል። ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ከ600 ለሚበልጡ ነዋሪዎች አገልግሎት መስጠት ተችሏል፡፡ በቀጣይ ባልተዳረሰባቸው ክፍለ ከተሞች እና በተመረጡ የከተማዋ አካባቢዎች አገልግሎቱን የማድረስ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

አገልግሎቱ ያለአንዳች መቆራረጥና መስተጓጎል እየተሰጠ ሲሆን፤ ከተገልጋዮች እየተገኘ ያለው ግብረ መልስ አዎንታዊና አበረታች ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለበለጠ ሥራ የሚያነሳሳ በመሆኑ፤ ተጨማሪ ዘመናዊ አውቶብሶችን በማዘጋጀት አገልግሎቱን በብዛት እና በስፋት ለማዳረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን፤ ይህንን ለማሳካት ጥረት እንደሚደረግ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ የአገልግሎት ዘርፍ ኃላፊ አመላክተዋል፡፡

ጷጉሜን 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በአራዳ ክፍለ ከተማ በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት አማካኝነት አንድ ብሎ የተጀመረው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት፣ ተደራሽነቱን ለማሳደግና ለማስፋት እየተሠራ ይገኛል። በ2018 በጀት ዓመት የማዕከላቱን ቁጥር ወደ አስራ አንድ የማሳደግ ዕቅዱንም ለማሳካት የሚያስችለውን አፈፃፀም ማስመዝገቡን ቀጥሏል፡፡ እስከ አሁን ባለው ጊዜ ውስጥ የማዕከላቱን ቁጥር ወደ ስድስት ማሳደግ ተችሏል፡፡

ማዕከላትን በማስፋፋት እንዲሁም የተንቀሳቃሽ አገልግሎት አማራጭን በስፋት ለአገልግሎት እያበቃ ያለው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ተቋም፣ የመንግስት አገልግሎት ላይ ያለውን ችግር በመቅረፍ ለተገልጋይ እርካታን የሚፈጥር አገልግሎት በብዛትና በጥራት ማድረሱን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዓይነቱ ልዩና የመጀመሪያ የሆነውን የአዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ ዲጂታል አገልግሎት ሚያዝያ 14 ቀን 2018 አስጀምረዋል። ለከተማዋ ዘመናዊነትና ዓለምአቀፋዊነት የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የልማት ተነሺዎችን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስራ

• በአዲስ አበባ ከተማ በአሁኑ ጊዜ 1 ሺህ 43 አርሶ አደሮች የ'ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ' ተጠቃሚ መሆናቸው ተገልጿል

**በይግለጡ ጓዴ**

በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች የከተማዋን የምግብ ፍላጎት በማሟላት ረገድ የሚጫወቱት ሚና የማይተካ ቢሆንም፣ ከከተማ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ፈተናዎችና ዕድሎች የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን በእጅጉ ይወስኑታል። እነዚህ አርሶ አደሮች መሬታቸው ለልማት በመወሰዱ ምክንያት ለከፋ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ቀውሶች ተጋልጠው እንደነበር ይታወሳል። ይሁን እንጂ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ይህን ችግር ለመፍታት በመንግሥት በኩል ስር ነቀል የሆኑ የማሻሻያ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ አርሶ አደሮችን ድምፅ ማድመጥና ለችግር የተጋለጡትን በዘላቂነት መልሶ የማቋቋም ተግባር በትኩረት ተሰርቶበታል፤ በዚህም ሂደት አርሶ አደሩ ለዘመናት ሲጠይቅ የነበረውን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲያገኝ መደረጉ ትልቁ ትሩፋት ተደርጎ ይወሰዳል። የመሬት ባለቤትነት መረጋገጡ አርሶ አደሩ በይዞታው ላይ ያለውን ዋስትና ከማጠናከሩ ባለፈ፣ መሠረታዊ ፍጆታቸውን መሸፈን ለማይችሉ አቅመ ደካሞች የተለየ የድጋፍ ማዕቀፍ እንዲዘረጋ መንገድ ከፍቷል። ከእነዚህም አንዱ 'ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ' ነው፡፡

'ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ' ተጠቃሚዎች ተብለው የተለዩት የኅብረተሰብ ክፍሎች መሬታቸው በልማት ምክንያት ተወስዶባቸው፣ በተለያዩ ማህበራዊና አካላዊ ምክንያቶች ራሳቸውን መቻል የማይችሉ ናቸው። እነዚህ ወገኖች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን በየወሩ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ያገኛሉ። ድጋፉ ምንም ዓይነት የጉልበት ሥራ መሥራት ለማይችሉ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚሰጥ ዘላቂ ዋስትና በመሆኑ የብዙዎችን ሕይወት ታድጓል።

በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ሙሉ ያደቴ የዚህ ድጋፍ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል አንዱ ናቸው። በእርጅና እና በጤና መታወክ ምክንያት ለረጅም ጊዜ በአልጋ ላይ የቆዩት አርሶ አደሩ፣ መሬታቸው በልማት በመወሰዱ ልጆቻቸውን ለማሳደግ ተቸግረው እንደነበር ያስታውሳሉ። "መሬቱ



ፎቶ ከገፀ ድር

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የ 'ዘላቂ ቀጥታ ድጋፍ' ተጠቃሚ ከሆኑት ወገኖች መካከል ጥቂቶቹ

ሲወሰድብኝ ትርፍ ማምረቻችን ብቻ ሳይሆን የዕለት ጉርሳችንም አብሮ የሄደ መስሎን ነበር" የሚሉት አርሶ አደሩ፣ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የተጀመረላቸው ዘላቂ ድጋፍ ለቤተሰባቸው ትልቅ ተስፋ እንደሆነ ይናገራሉ።

በተመሳሳይ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ነዋሪዋ ወይዘሮ ሶፍያ ሀሰን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የልማት ተነሺ በመሆናቸው ለገጠማቸው ማህበራዊ ጫና መንግሥት በሰጠው የጋራ መኖሪያ ቤትና ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ መረጋጋት ማግኘታቸውን ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ ካለው የኑሮ ውድነት አኳያ የሚደረግላቸው 2 ሺህ 37 ብር በቂ አለመሆኑን ጠቁመው፣ ከድጋፉ ጎን ለጎን ልጆቻቸው በከብትና በዶሮ እርባታ ዘርፍ ተሰማርተው ራሳቸውን እንዲችሉ ተጨማሪ የሥራ ዕድል ቢመቻችላቸው የኢኮኖሚ ጫናው እንደሚቀልላቸው ያምናሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የአርሶ አደር ማቋቋም ልማት ቡድን መሪ የሆኑት አቶ ለገሰ ወርቁ፣ ከ2010 ዓ.ም በፊት አርሶ አደሮች መሬታቸውን አጥተው በተለያዩ አካባቢዎች ተበትነው እንደነበር ያስታውሳሉ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በ2009 እና በ2010 ዓ.ም አርሶ አደሮችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ በስድስቱ የማስፋፊያ ክፍለ ከተሞች (የካ፣ ለሚ ኩራ፣ ቦሌ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ እና ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች) ሥራ መጀመሩን አስረድተዋል።

በአሁኑ ወቅት በከተማዋ ከ38 ሺህ በላይ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ያሉ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ መሥራት የማይችሉ 1 ሺህ 43 አርሶ አደሮች የ'ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ' ተጠቃሚ ሆነዋል።

አቶ ለገሰ እንደሚሉት፣ የድጋፍ ሥርዓቱ ፍትሐዊ እንዲሆን ከወረዳዎች ጋር በመተባበር መሥራት የሚችልና የማይችልን የመለየት ሥራ በትክክል ተከናውኗል። መሥራት ለሚችሉ አርሶ አደሮች በማህበር ተደራጅተው የሚሰሩበት የመሥሪያ ቦታና መነሻ ካፒታል እየተመቻቸላቸው ይገኛል።

ለ'ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ' ቅድሚያ የሚሰጣቸው መስፈርቶች የእድሜ መግፋት፣ አካል ጉዳተኝነት እንዲሁም አባትና እናት የሌላቸው እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ናቸው። የገንዘብ ድጋፉ መጠንም እንደ ተጠቃሚው ብዛት ይለያያል፤ ለአንድ ግለሰብ 2 ሺህ 37 ብር ሲከፈል፣ ባልና ሚስት ለሆኑ 3 ሺህ 564 ብር እና አራትና ከዚያ በላይ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ደግሞ እስከ አንድ ሺህ ብር ተጨማሪ

> **"በአሁኑ ወቅት በከተማዋ ከሚገኙ 38 ሺህ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መካከል መስራት የማይችሉ 1 ሺህ 43 አርሶ አደሮች የ'ዘላቂ የቀጥታ ድጋፍ' ተጠቃሚ ናቸው፤ በዚህ መርሃ ግብር ቅድሚያ የሚሰጣቸው እድሜያቸው የገፋ፣ አካል ጉዳተኞች፣ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወላጅ አልባ ህጻናት ናቸው"**

ክፍያ ይደረጋል። ይህ አሰራር ቤተሰቦች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ ታስቦ የተዘረጋ ነው።

ከመሠረታዊ ፍጆታ ባለፈ የመኖሪያ ቤት ችግርንም ለመፍታት ሰፊ ርቀት ተጉዟል። እስካሁን ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች 22 ሺህ 195 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተላልፈዋል። ቤቶቹን ማደስ ለማይችሉና መጠለያ ለሌላቸው 24 ተለይተው የወጡ አርሶ አደሮች ደግሞ ኮሚሽኑ በየወሩ 6 ሺህ 500 ብር የቤት ኪራይ እየከፈለላቸው ይገኛል። ይህ እርምጃ አርሶ አደሩ በልማት ምክንያት ለጎዳና ተዳዳሪነት እንዳይጋለጥ የተወሰደ የመከላከያ እርምጃ ነው።

አካል ጉዳተኞችን በተመለከተም ኮሚሽኑ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። የመንቀሳቀስ አቅማቸው ለተገደበ አርሶ አደሮች ዊልቸርና ክራንች የማቅረብ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፣ በዚህ በጀት ዓመት ብቻ 38 ዊልቸርና 17 ክራንች ተገዝተው ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ዝግጅት ተጠናቋል። ይህ ዓይነቱ ድጋፍ አርሶ አደሮች በቤታቸው ውስጥና በአካባቢያቸው በተወሰነ መልኩ ተንቀሳቅሰው ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ ይረዳቸዋል።

በአዲስ አበባ ዙሪያ ለሚገኙ አርሶ አደሮች እየተደረገ ያለው ድጋፍ ከጊዜያዊ እርዳታ ባለፈ ሕይወትን በዘላቂነት ለመቀየር ያለመ ነው። ምንም እንኳን የኑሮ ውድነቱ በድጋፍ መጠኑ ላይ ጫና ቢፈጥርም፣ መንግሥት የአርሶ አደሩን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የጀመራቸው ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላካች ናቸው። አርሶ አደሩን መልሶ ማቋቋም ማለት ከተማዋን መልሶ ማቋቋም መሆኑን ተገንዝቦ መሥራት ለነገዋ አዲስ አበባ ብሩህ ተስፋን ይሰጣል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የሚመለከታቸው አካላት ከወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ባለፈ፣ እንደ ወይዘሮ ሶፍያ ጥያቄ ሁሉ፣ አቅም ላላቸው የአርሶ አደር ቤተሰቦች ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ማመቻቸት ላይ ትኩረት ቢያደርጉ፣ አርሶ አደሩ ከድጋፍ ጠባቂነት ወደ አምራችነት ተሸጋግሮ የከተማዋን የኢኮኖሚ ምሰሶነቱን ዳግም እንዲያረጋግጥ ይረዳዋል። የልማት ተነሺዎችን ክብርና ጥቅም ያስጠበቀ እድገት ለሀገር ግንባታው ስኬት መሠረት ነው።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የመዲናዋ አረንጓዴ ጋሻ

**• የአዲስ አበባ አረንጓዴ ስፍራ ሽፋን ከ2 ነጥብ 8 በመቶ ወደ 24 በመቶ አድጓል**

**በለይላ መሀመድ**

አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት፣ የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽንን ጨምሮ የተለያዩ ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ በዓለም አቀፍ ደረጃ "የአፍሪካ ዲፕሎማሲ ዋና ከተማ" በመባል ትታወቃለች። ከኒውዮርክና ጄኔቫ በመቀጠል ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ መዲናም ናት፡፡ ከተማዋ በርካታ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች፣ የዲፕሎማቲክ እንቅስቃሴዎች እና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ይካሄዱባታል፡፡

ከተማዋ የሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ እንቅስቃሴ ማዕከል እንደመሆኗ መጠን፣ ፈጣን የሆነ የከተማ መስፋፋት እያሳየች ትገኛለች። እድገቷ ታዲያ ከከተማዋ የአየር ንብረት መቋቋም (Climate Resilience) እና ከሥነ ምህዳር ጥበቃ ጋር ሚዛኑን የጠበቀ መሆን አለበት። የአረንጓዴ ልማቱ ከተማዋን ውብ ከማድረጉም ባሻገር ካርቦንዳይኦክሳይድን በመምጠጥ ንጹህ ኦክስጅን እንዲኖር በማድረግ የከተማዋን የአየር ብክለት ይቀንሳል። በዚህ አማካኝነትም የአረንጓዴ ልማት ለከተማዋ ቅንጦት ሳይሆን ለነዋሪዎቿ ጤናማ እና ዘላቂነት ላለው እድገት ወሳኝ ነው።

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንም ከሚሰራቸው በርካታ ሥራዎች መካከል የአረንጓዴ ልማትን በማሳደግ የተፈጥሮ ሚዛንን ማስጠበቅ አንዱ ነው፡፡ የዛሬው ጽሑፋችንም ትኩረቱን ያደረገው የአረንጓዴ አሻራ ልማት ለአየር ንብረት ለውጥ የሚኖረው ፋይዳ ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሙክታር ሰይድን አነጋግረናቸዋል፡፡


ከተማዋን አረንጓዴ የማልበስ ጥረት ውጤት እያሳየ ነው
ፎቶ ከገፀ ድር

እንደ አቶ ሙክታር ገለጻ፤ አንድ ከተማ 'አደገ'፣ 'ተለወጠ'፣ 'ስማርት ከተማ ሆነ' የሚባለው አረንጓዴ ልማቱና የደን ሽፋኑ እያደገ ሲሄድ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ ከተማ ስማርት ከተማ ነው ለመባል 30 በሙቶ በደን የተሸፈነ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል። አዲስ አበባ ከተማም ወደ ስማርት ከተማ የምታደርገውን ጉዞ ለማስቀጠል የአረንጓዴ አሻራዋን ለማሳደግ እየተጋች ትገኛለች፡፡ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ከተቋቋመበት ተግባርና ኃላፊነት መካከል አንዱ ከደንና ደን ውጤቶች ጋር በተያያዘ ያሉ ሥራዎች ላይ በትኩረት መሥራት እንደመሆኑ መጠን ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የአረንጓዴ ልማት በአዲስ አበባ ሲሰራ ሳይንሳዊ ዘዴን የተከተለ እንዲሆን ቁጥጥርና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በመዲናዋ የአረንጓዴ አሻራ ልማት ሥራ ላይ ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ አንዱ ሲሆን ቢሮው እንደ ከተማ ችግኝ ከማፍላት ጀምሮ የመትከልና የማልማት፣ የመጠበቅ፣ የመንከባከብ ትልቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ የጉለሌ እጽዋት ማዕከል ሌላው የአረንጓዴ ልማት ሥራን የሚሰራ ተቋም ነው፡፡ ማዕከሉ በራሱ ክልል ውስጥ የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን ችግኞች የመትከል፣ ያሉትን የመጠበቅ፣ የመንከባከብ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡ ከእነዚህ ዋና የአረንጓዴ አሻራ ተዋናዮች በተጨማሪ በአረንጓዴ አሻራ ልማት የሚሳተፉ የኃይማኖትና የግል ተቋማት እንዲሁም ግለሰቦች ናቸው፡፡ ተቋማትም ሆኑ ግለሰቦች የሚተክሏቸው ዛፎች ሀገር በቀል እንዲሆኑም ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በከተማ ደረጃ የሚተከሉ ችግኞች በትክክለኛው መንገድ እየተተከሉ መሆናቸውን የክትትል ሥራም ይሰራል፡፡ "ምን አይነት ዝርያ ያላቸው እጽዋት ናቸው የሚተከሉት?" የሚለውን ይከታተላል፤ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ሲቆረጡ የትኛው ነው የሚቆረጠው በሚል ለመንግሥት፣ ለግለሰብ፣ ለተቋማት፣ ለኤምባሲዎች ፍቃድ ይሰጣል፤ ያማክራል፡፡ የማይቆረጡትን የሀገር በቀል እጽዋትን የቆረጠ ካለ እርምጃ ይወስዳል፡፡ በፍቃድ መነሳት ያለበት ሀገር በቀል እጽዋት ካለ ማበረታታት እንዳይሆን የሮያሊቲ ክፍያ (ቀጣይነት ላለው የደን ልማት አገልግሎት የሚውል ክፍያ) እንዲከፈል ይደረጋል። በተጨማሪም የሚቆረጡ አልያም ወደ ሌላ ቦታ የሚዛወሩ ዛፎችን ፍቃድ የመስጠት ሥራ የሚሰራው ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ስለመሆኑም ዳይሬክተሩ ያነሳሉ፡፡

የፍቃድ አሰጣጡ የሚከናወነው በሁለት መልኩ ነው፡፡ በመንግሥት ተቋማት (መንግሥት የሚያስተዳድራቸው የዛፍ ቦታዎች) እና በግለሰቦች ይለያያል። የከተማ ውበትና አረንጓዴ ወይም፣ ጉለሌ እጽዋት ማዕከል ወይም ፓርኮች ኮርፖሬሽን ዛፉን ለሌላ ዓላማ ለማዋል ቢፈልጉ የቆጠራ ሥራውን የሚሰራው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው። ለምሳሌ ባህር ዛፍ በሀገር በቀል ዛፍ ይቀየር ቢባል ቆጠራ የሚያካሂደው በሕጋዊ መንገድ ለሚገዛው አካል ቆጥሮ የሚሰጠው እንዲሁ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ነው፡፡ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በእያንዳንዱ የዛፍ አይነት አሁናዊ እና ዓመታዊ የዛፍ ሽያጭ ዋጋን ያጠናል፡፡ የገበያ ዋጋ ለማህበረሰቡ ይፋ የማድርግ ሥራ ይሰራል፡፡ ግለሰቦች በሚያለሙት አረንጓዴ ልማት ሥራ ላይም ይቆረጥ አይቆረጥ በሚል ፍቃድ ይሰጣል፡፡ ከጠቀሜታው አንጻር "የትኛው ዛፍ ነው የሚቆረጠው? ለምንድነው?" የሚለውን ሁሉ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ያጠናል፡፡ በዚህ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፡፡ ከፍቃድ ውጪ የሚቆረጥ ዛፍ ካለ የቆረጠውን አካል ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ ይህ አይነት አሠራር የተዘረጋው በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ዛፍ ወደ መቁረጥ እንዳይገቡ ለማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በበላይ ሆኖ ይቆጣጠራል ማለት ነው፡፡

የደን ሽፋንን ለማሳደግ በተለይም የታሰበውን ዓላማ ማሳካት የሚቻለው አዳዲስ ችግኞች ሲተከሉ፣ በተለያየ ምክንያት በሚቆረጡ ዛፎች ምትክ ሲተከል እንዲሁም አጠቃላይ እንክብካቤ ሲደረግ መሆኑን የሚገልጹት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ አያይዘውም፤ በአዲስ አበባ የአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሃ ግብር ከመጀመሩ በፊት የአረንጓዴ ሽፋን በከተማ ደረጃ 2 ነጥብ 8 በመቶ ነበር፡፡ ባለፉት ዓመታት በየአካባቢው የሕዝብ ፓርክና መዝናኛ ስፍራዎች፣ በወረዳ በሚገኙ መዝናኛ ስፍራዎች በተጨማሪም በከተማ ደረጃ በሚገኙ ትልልቅ ፓርኮች እና በኮሪደር ልማቱ በለሙት ሰፋፊ የመንገድና የወንዝ ዳርቻዎች በተካሄደው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የከተማዋን የአረንጓዴ ሽፋን ከነበረበት ወደ 24 በመቶ ማሳደግ ተችሏል፡፡ ይህ ለውጥ ሊመጣ የቻለው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ በጋራ በመሆን በቅንጅትና በትብብር መሥራት በመቻላቸው ነው፡፡

ለዚህ እድገት የኮሪደር ልማቱ ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡ የወንዝና ወንዝ ዳርቻን ጨምሮ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች የተሰራው አረንጓዴ ልማት ሥራ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚህም ባለፈ በየዓመቱ በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በማህበረሰቡ የተካሄደው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ነው፡፡ በዋናነት ሽፋኑ የጨመረው መትከል በመቻሉ ብቻ ሳይሆን የጽድቀት መጠኑ እንዲጨምር እንክብካቤ የማድረግ ሥራው በመጠናከሩ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በተለይም ከለውጡ በፊት ብዙ ችግኞች ቢተከሉም አብዛኞቹ ይደርቁ ነበር፡፡ 100 ዛፍ ቢተከል 10 በመቶው ብቻ ነበር ይጸድቅ የነበረው። ክትትል አይደረግበትም ነበር፡፡ ማህበረሰቡም ሆነ ተቋማት ባለቤት እንዲሆኑ አልተደረገም ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ሕዝቡ ባለቤት እንዲሆን ተደርጓል። ተቋማትም በተመሳሳይ በባለቤትነትና በእኔነት ስሜት እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በየዓመቱ ከግንቦትና ሰኔ ጀምሮ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ህፃናትን ጨምሮ ሁሉም የሚመለከታቸው ተቋማት እንዴት በኃላፊነት ቦታ ተረክበው እየተከሉ እንደሆነ በተጨባጭ ታይቷል። ይህም ብቻ ሳይሆን በሚገባው ልክ እንክብካቤ በመደረጉ ሊጸድቁ ችለዋል። በዚህም የደን ሽፋኑ እያደገ መምጣቱን ዳይሬክተሩ ያስረዳሉ፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከተጀመረ ወዲህ እየተተከሉ ያሉት ችግኞች 90 በመቶ በሀገር በቀል ዛፎች እየተሸፈነ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትን ባለሙያው እንዳብራሩት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በትኩረት እየተተከሉ መሆናቸው ነው፡፡

የአዲስ አበባ አረንጓዴ ልማት የአንድ ቀን ሥራ አይደለም፡፡ ከተማዋ የአየር ንብረት ለውጥ ፈተናን የመቋቋም አቅም እንዲኖራት ዛሬ የምንወስዳቸው እርምጃዎች የነገውን ትውልድ ደህንነት ይወስናሉና ከተማዋን ወደ ዘላቂ አረንጓዴ ልማት በመለወጥ ለነዋሪዎቿ ምቹ እንድትሆን ማድረግ የሁሉም የጋራ ኃላፊነት ነው፤ የትውልድ ጥያቄም ነው። ስለሆነም ለአረንጓዴ አሻራ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል እንላለን፡፡

## በምርጫው ...
ከገጽ 7 የዞረ

አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ወጣት እንደመሆኑ፤ ይህ ግዙፍ ሀይል ባለው ቁጥር ልክ በሀገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊው ዘርፍ ዋነኛ ተዋናይና የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል። ከምርጫ ጋር በተያያዘም እድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው የመምረጥ መብት አለው፡፡ እድሜው 21 እና ከዚያ በላይ የሆነው ደግሞ የመመረጥ መብት አለው፡፡ ከዚህ አኳያ ወጣቱ ይህንን የዜግነት መብት ለመጠቀም በድምፅ መስጫ ዕለት ‘ይጠቅመኛል፤ ሀገርን ይለውጣል’ ለሚለው የፖለቲካ ፓርቲ ድምጹን መስጠት ይጠበቅበታል። የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክር የፖሊሲ ሀሳብና ፕሮግራማቸውን ሲያቀርቡ ወጣቱንና ሀገሪቱን ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር የሚያስችሉ ጉዳዮችን እንደያዙ ማወቅ ይኖርበታል፡፡

ወጣቱ የሀገርን መጻኢ እድል ለመወሰን በሚያስችለው ምርጫ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንደሚጠበቅበት የሚያነሱት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ሙሉዓለም፣ ተሳትፏቸው ማደጉ፣ በምርጫው ድምፅ የሚሰጠው መራጭ ቁጥር መጨመር የሚመሰረተው መንግሥት የወጣቱን ይሁንታ ያገኘ እና ቅቡልነት ያለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ወጣቱ በምርጫው በመሳተፍ የመረጠው የፖለቲካ ፓርቲና መንግሥት የገባውን ቃል መፈፀሙን የሚጠይቅበት፤ ቃሉን ካልጠበቀ ደግሞ በሚመጣው ምርጫ ሌላ የሚመርጥበትን ዕድል ይፈጠራል፡፡

ዴሞክራሲ ስር ባልሰደደባቸው ሀገራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወጣቶችን ለሚፈልጉት የፖለቲካ ዓላማ በበጎም ሆነ በአሉታዊ መልኩ የመጠቀም ፍላጎትና ልምድ ይታያል፡፡ በኢትዮጵያ ከ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ በፊት የወጣቱን ትኩስነትና ስሜት በመጠቀም ለራሳቸው የፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ ለመጠቀም የተሞከረበትና ግጭት የተፈጠረበት ሁኔታ እንደነበር የሚያነሱት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ሙሉዓለም፣ በአሁኑ ወቅት ባለው የፖለቲካ ስርዓት በአመራርነት ቦታ ቀላል የማይባል ወጣት ተቀምጠው ይታያሉ። የሀገሪቱ ተረካቢ፣ መሪ፣ መንግሥት፣ የሀብት ባለቤት የሚሆነው ወጣቱ እንደመሆኑ ለምርጫው ውጤታማነት በጎና ገንቢ ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡ በምርጫው ሂደት ላይ ቅሬታ ካላቸውም ሕጉን በመከተል ጥያቄዎችን ማቅረብና መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡ ሰፋ አድርጎ በማየት፣ በሰከነ መንገድ፣ ከግጭትና ብጥብጥ በመራቅና የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ለምርጫው ሰላማዊነትና ዴሞክራሲያዊነት ሚናውን መወጣት ይኖርበታል፡፡

በጥቅሉ የምርጫው በሰላም መጠናቀቅና ስኬታማ መሆን ለወጣቱ ምቹ የሥራ ዕድል፣ የፖለቲካ ተሳትፎና የተረጋጋች ሀገርን የመረከብ ዕድል ይሰጠዋል፡፡ በተቃራኒው የምርጫ ሂደቶች ግጭትና አለመረጋጋት የሚታይባቸው ከሆነ ዋነኛ ሰለባ የሚሆነው የነገዋ ሀገር ተረካቢ የሆነው ወጣት ነው፡፡ በመሆኑም የምርጫው ውጤታማ መሆን ከድምፅ መስጠት ባለፈ፣ የወጣቱን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎች የሚቀረጹበትና የሀገር ግንባታ ሂደት መሠረት የሚጠናከርበት በመሆኑ እድሉን በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል እንላለን።

## ከጥሻ ...
ከገጽ 8 የዞረ

ናቸው። በተለይ ከራስ መኮንን ድልድይ እስከ አፍንጮ በር ያለው የወንዝ ዳርቻ በጥሻ የተሸፈነ በመሆኑ እግረኞች በተለይ በምሽት ለመንቀሳቀስ የሚቸገሩበት፣ ዘረፋና የተለያዩ ወንጀሎች የሚፈፀምበት፤ ሴቶች የሚደፈሩበት፣ በወንዙ አካባቢ ሰዎች በደሳሳ ቤቶች ራሳቸውን ለጎርፍና ለኤሌክትሪክ አደጋ አጋልጠው የሚኖሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ በተጨማሪም ወንዙ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ የሚለቀቅበትና የሚጣልበት፣ ሰዎች የሚፀዳዱበት በመሆኑ በሚፈጠረው የሚሰነፍጥ ሽታ ምክንያት ሰዎች በአካባቢው አይደለም መቆየት ለማለፍ የሚቸገሩበት ሁኔታ ነበር፡፡

የአዲስ አበባ ወንዞች ለከተማዋ መቆርቆር ምክንያት ቢሆኑም በከፍተኛ ደረጃ በመበከላቸው የጤና ጠንቅ ሆነው እንደነበር ያነሱት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አቶ ስዩም፣ በወንዝ ዳርቻ ልማት የአካባቢውን ገፅታ መቀየር ተችሏል። ከላይ የተጠቀሰው አካባቢም በወንዝ ዳርቻ ልማት ታሪካዊ ስፍራዎች ታድሰው፣ ንጹህ፣ ውብና የዓይን ማረፊያ ሆነዋል፤ ካፌዎችና ሬስቶራንቶች፣ የገበያ ማዕከላት፣ የቡና ፓርክ፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ የእግረኛና መሮጫ መንገዶች፣ ማረፊያ ወንበሮች እንዲኖራቸው ተደርጎ፣ የወንዞቹ ውሃ ተጣርቶና ተመጥኖ ወደታች መፍሰስ እንዲችል የሚያደርግ መቆጣጠሪያ ግድቦች፣ ሰው ሰራሽ ግድቦች እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ተገንብተውለት፣ ልጆች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አቅመ ደካሞች የሚዝናኑበትና የሚያርፉበት ስፍራ ሆኗል፡፡ ጀርባቸውን ሰጥተው የነበሩ ቤቶችም ፊታቸውን ወደ ወንዞች አዙረዋል፡፡

የወንዝ ዳርቻው ለከተማዋ በርካታ ጥቅሞችን እያስገኘ መሆኑን አቶ ስዩም ያስረዳሉ፡፡ በወንዝ ዳርቻው ግራና ቀኝ አገልግሎት እየሰጡ ባሉ ሱቆችና ካፍቴሪያዎች፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ የመኪና መቆሚያዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎችና የተለያዩ አገልግሎቶች በርካታ ወጣቶች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። አካባቢው በርካቶች ብቻቸውን አሊያም ከቤተሰባቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ከወዳጅ ዘመዳቸው ጋር በመሆን እረፍት ለማድረግ፣ ንጹህ አየር ለመውሰድ የሚመርጡትና የሚሰባሰቡበት፣ በዚያውም ማህበራዊ ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበት ስፍራ ሆኗል፡፡

ሌላው ክረምት በመጣ ቁጥር በሚያጋጥመው ጎርፍ ጉዳት የሚደርስባቸው፣ ስጋት ውስጥ ይወድቁ የነበሩ ነዋሪዎች ተነስተው ወደ ሌላ ቦታ እንዲኖሩ በመደረጉ የጎርፍ አደጋ ስጋትን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ተችሏል፡፡ የወንዝ ዳርቻው የከተማዋን የአረንጓዴ ሽፋን በመጨመርና ገፅታ በመቀየር፤ አዲስ አበባን እንደ ስሟ ‘ውብና አበባ’ ማድረጉንም አቶ ስዩም አብራርተዋል፡፡

በእርግጥም የራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ በአንድ ወቅት ለምንም የማይመች ስፍራ ነበር፡፡ አሁን የቀድሞው ምስቅልቅል ገፅታ ታሪክ ሆኗል፡፡ ከቆሻሻነት ወጥቶ ውብና ማራኪ ገፅታን ተላብሷል፡፡ ከጨለማ ወደ ብርሃን ተሸጋግሯል፡፡ ተፈጥሮና ዘመናዊነት የተዋሃዱበት ውብ ስፍራ ሆኗል፡፡ አዲስ አበባ እንደ ስሟ ‘ውብና አበባ’ እየሆነች ስለመምጣቷ ማሳያ ከሆኑ ስፍራዎች መካከል የሚመደብ ነው፡፡ ይህ ማራኪና ድንቅ ስፍራ ውበትና ንጽህናው ተጠብቆ እንዲቀጥል በመጠበቅና በመንከባከብ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት እንላለን፡፡

## የአዲስ ...
ከገጽ 6 የዞረ

አክለውም፤ በሩጫ፣ በብስክሌት፣ በእግር ኳስ እና በሌሎች ዘርፎች በርካታ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ለምክር ቤቱ ገልጸዋል፡፡

### ኪነ-ጥበብ

ኪነ-ጥበብ ሀገር የሚሰራበት አንዱ መንገድ መሆኑን ያነሱት ከንቲባዋ፤ በዚህ ዘርፍ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን እና እየተሰሩ መሆኑን አንስተዋል፡፡ ኪነ-ጥበብ ለወል ትርክት ግንባታ የላቀ ሚና ያለው መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ለዚህም በርካታ ገንዘብ የፈጀ ዓለም አቀፍ እና ዘመናዊ የሲኒማ ኮምፕሌክስ እና ቴአትር ቤት መሰራቱን አንስተዋል፡፡ በአዲስ አበባ 53 አምፊ ቴአትሮች ተገንብተዋል። እነዚህ ደግሞ ለወጣቶችና ለሁሉም ማህበረሰብ የሚያገለግሉ መሆናቸውን ከንቲባ አዳነች አቤቤ አብራርተዋል፡፡ ሀገር ፍቅር ቴአትርን ጨምሮ ነባር የኪነ-ጥበብ ማዕከላት መታደሳቸውን ያብራሩት ከንቲባዋ፤ አንጋፋ የጥበብ ሰዎችን የማክበር ስራ መሰራቱንም አክለዋል። የስልጠና ማዕከላት መከፈታቸው እና ለአንጋፋዎች እውቅና መሰጠቱ አዳዲስ የኪነ ጥበብ ሰዎችና ወጣቶችን ለማፍራት ያስችላል ብለዋል፡፡

### የከተማ ልማት

በ2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ የነበረው ከከተማ ደረጃ በታች(የጭቃ ቤት) የሆኑ መንደሮች 74 በመቶ የነበረ ሲሆን አሁን ወደ 30 በመቶ ወርዷል ብለዋል። በዚህም በርካታ ማህበረሰብ የልማቱን አስፈላጊነት መረዳቱን አብራርተዋል። ይህም ለከተማዋ የኮንፈረንስ ቱሪዝም ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ እነዚህ የተሰሩ ስራዎች የሀገርን ክብር የጨመሩ መሆኑን አንስተዋል፡፡ በአዲስ አበባ የተሰሩት የኮንፈረንስ ማዕከላትም አሁን ላይ የዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን እያስተናገዱ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ የውጭ ምንዛሬ ከማስገኘት በዘለለ ለሀገራዊ አገልግሎት ትልቅ አበርክቶ እንዳላቸውም አንስተዋል፡፡ ለአብነትም አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል 8 ስብሰባ በአንድ ጊዜ ማድረግ ያስችላል ብለዋል፡፡ አሁንም አዲስ አበባ ላይ የተሰራው ስራ በቂ አይደለም፤ ከዚህ በላይ ይሰራል፡፡ ኮፕ 32ን ተጨማሪ አቅም አድርገን እንጠቀምበታለን ሲሉም ተናግረዋል፡፡

### መብራት

ከተማዋ በሁሉም ነገር እድሳት ላይ ነች ያሉት ከንቲባ አዳነች አቤቤ መብራት አንዱ ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ለአዲስ አበባ መብራት ብዙ ነገር ነው፡፡ ወንጀልን ለመከላከልና አገልግሎትን ለማሳለጥ እጅግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ስማርት ተደርገው ተሰርተዋል ሲሉ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡ ለአብነትም የደህንነት ካሜራ የተገጠመላቸው መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በዚህም የደረቅ ወንጀል ቁጥር ቀንሷል። ተጠርጣሪን በቀላሉ ለመያዝ መብራት ላይ የተሰሩ ስራዎች አግዘዋል፡፡ ይህ ስራ በሌሎች አካባቢ ተደራሽ ይሆናል፡፡ የመብራት ጥገናም በሌሎች አካባቢዎች እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡ የቀሩትን ቦታዎች በቅደም ተከተል እንሰራለን ሲሉም አብራርተዋል፡፡

### አገልግሎት

አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ትኩረት ያደረግነው ለውጥ ለማምጣት ነው ሲሉ ያብራሩት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በማሳያነት ጠቅሰዋል። ይህም አገልግሎቱን እያቀላጠፈ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡ በመሶብ ከ150 በላይ የአገልግሎት አይነቶች ዲጅታል ሆነው መግባታቸውን አንስተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ቅልጥፍና ማምጣቱን እና ብልሹ አሰራርን ማስቀረቱን ጠቅሰዋል፡፡ በቂ የሰው ሃይልም ለሙያውና ለአገልግሎት ብቁ በማድረግ ወደ ስራ እየተሰማራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በዚህም የነዋሪው እርካታ መጨመሩን አብራርተዋል፡፡ ይህ ስራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ከንቲባዋ ተናግረዋል፡፡

### ተጠያቂነትን በተመለከተ

ሙስናን ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው። ከንቲባዋ ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ አንዱ ማጋለጥ መሆኑን አንስተዋል፡፡ በዚህም የሴክተር መስሪያ ቤቶችን የፌስቡክ ገጽ በመጠቀም አጥፊዎችን የማጋለጥ ስራ መሰራቱን አንስተዋል፡፡ ከዚህ በዘለለም በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የሚቀርበው “አገልጋዩ” ፕሮግራም ላይ በቀጥታ ተገልጋዩ አመራሩን የሚጠይቅበት አሰራር መዘርጋቱን ተናግረዋል፡፡ “ዋርካ” ፕሮግራምም በተመሳሳይ ተጠያቂነትን ለማስፈንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ትልቅ አበርክቶ እንዳለው ከንቲባ አዳነች ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም ሌሎች እርምጃዎች መወሰዳቸውን አብራርተዋል፡፡ በዚህም 420 ያህል አመራሮችና ባለሙያዎች ተጠያቂ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡ አንዳንዶቹ ቅጣት የተጣለባቸው አሉ። የአንዳንዶቹ ደግሞ በፍርድ ሂደት ላይ ነው ብለዋል፡፡ መረጃ ከተገኘና መረጃዎች ህጋዊ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በቂ ከሆኑ በህግ እንጠይቃለን ሲሉ አስታውቀዋል፡፡ ማህበረሰቡም ጥቆማ በመስጠትና ምስክር በመሆን ትብብር እያደረገ መሆኑን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናግረዋል፡፡

### ተጨማሪ በጀት

ምክር ቤቱ ለ2018 ዓ.ም 9 ነጥብ 94 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ በጀት አጽድቋል፡፡ ምክር ቤቱ ተወያይቶ ያጸደቀው ተጨማሪ በጀት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰራተኞች በፌደራል መንግስት የተሰጠ የደምወዝ ድጎማ ብር 8 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር እና ለከተማዋ የልማት ሥራዎች የሚሆን 996 ሚሊዮን ብር ነው፡፡

በመጨረሻ ምክር ቤቱ በከንቲባ አዳነች አቤቤ የቀረቡለትን ሹመቶች አጽድቋል፡፡ በዚህም መሰረት አቶ ሰለሞን ዲባባ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆነዉ ተሹመዋል፡፡ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የቦርድ አመራሮች ሹመትም በምክር ቤቱ ጸድቋል። እንዲሁም አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ አሰግደዉ ኃ/ጊዮርጊስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ ሆነው ተሹመዋል፡፡

## የቅጥር ማስታወቂያ

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ለዋና ስራ አስፈፃሚ ጽፈት ቤት ስር ላሉ ዳይሬክቶሬቶች (በድጋሚ የወጣ )** | | | | | | | | | | |
| 1 | ከፍተኛ የህግ ባለሙያ | IX | ቢ.ኤ/ ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በህግ | አ/18.873 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| 2 | ከፍተኛ የለውጥ ስራዎች ትግበራና ክትትል ባለሙያ | IX | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ በሥራ አመራር፣ በቢዝነስ አድሚንስትሬሽን፣ በህዝብ አስተዳደር፣ በህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን | አ/18.027 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አዲስ አበባ |
| **ለቋንቋዎች ዘርፍ (በድጋሚ የወጣ)** | | | | | | | | | | |
| 3 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርታዊ አዘጋጅ | XII | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 7/5 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.673 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 4 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ትምህርታዊ ከፍተኛ ሪፖርተር | X | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 5/3 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.675 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |
| 5 | የአፋን ኦሮሞ ቋንቋ ዶክመንተሪ ረዳት አዘጋጅ | XI | ቢ.ኤ./ኤም.ኤ ዲግሪ | 6/4 ዓመት | በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋና ሥነ ጽሁፍ፣ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ቲያትሪካል አርት፣ በህግ፣ እንዲሁም በጤና፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ ትምህርት ዘርፎች ወይም በተዛማጅ የት/ት መስክ | አ/18.681 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |

**ማሳሰቢያ፡-**

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን ከግንቦት 03/2018 ዓ.ም እስከ ግንቦት 14 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስተ ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 በይዞታ መለያ ቁጥር AA000070404292 በሴሪ ቁጥር L017970 በመሀመድ ይመር አበጋዝ ስም የተመዘገበ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር አዲስ የይዞታ ካርታ ቁጥር K15-01-6-63-539-1625/00 በአቶ አበራ ጎንፋ ጎንዳሌ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 22/08/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ (አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ ሃይማኖት አበበ አለሙ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ወረዳ 03 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 70137/2 የሴሪ ቁጥር 0627656 የይዞታ ስፋት 91 ካ/ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን ወመ10/23795/18/18 በቀን 21/08/18 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቧ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለው የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ፅ/ቤት እንዲያቀርቡ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ካራቫን ሆቴል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ካርታ/የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000060401284 ሴሪ ቁጥር- R 0101386 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ/የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ10-1/101/6/7/55442/216364/02 ሴሪ ቁጥር 1528531 በወ/ሮ በለጡ በፍርዱ እዝነህ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቶ ጠሀ መሀመድ ለማ ስም የተመዘገበ ይዞታ ወረዳ 01 የካርታ ቁጥር W1/2-1-63-94-17819/02 የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን 15/08/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# ሁለገቡ የስፖርት ‘አሬና’

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ ከገፀ ድር

በአራዳ ፓርክ ውስጥ የተገነባው የስፖርት አሬና ከፊል ገፅታ

አንድ ከተማ በህንፃዎቹ ግዝፈት ብቻ ሳይሆን በነፃነት በሚተነፍስባቸው ክፍት ቦታዎቹ፣ መዝናኛ ስፍራዎችና የስፖርታዊ ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጭምር ይመዘናል። እንደ አዲስ አበባ ባሉ በፈጣን ለውጥ ውስጥ በሚገኙ ሜትሮፖሊታን ከተሞች ውስጥ አረንጓዴ ስፍራዎች፣ ዘመናዊ አሬናዎች እና የመሮጫ ትራኮች ከቅንጦት መገለጫነት ባለፈ የከተማዋ ‘ሳንባዎች’ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ እነዚህ ቦታዎች የድንጋይና የኮንክሪት ጫካውን ሰብረው የሚወጡ የጤና ምንጮች ብቻ ሳይሆኑ፣ የዜጎች ስነ-ልቦና የሚታደስባቸውና የከተማ ነዋሪነት ትርጉም በስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚደምቅባቸው የነፃነት አውድማዎች ናቸው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት አዲስ አበባ ውስጥ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ማድረግ በመንገዶች ዳር ካሉ ጠባብ የእግረኛ መንገዶችና በአጥሮች ከታጠሩ ጥቂት መጫወቻ ሜዳዎች አይዘልም ነበር፡፡ የከተማዋ ነዋሪም ለንጹህ አየርና ለሩጫ ስፍራ ፍለጋ እስከ እንጦጦ ተራራና እስከ ጃንሜዳ ለመጓዝ ይገደድ ነበር። ዛሬ ግን ይህ ምስል በከፍተኛ ፍጥነት ተቀይሯል። ቀደም ሲል ዝግና ለቆሻሻ መጣያነት ያገለግሉ የነበሩ የወንዝ ዳርቻዎች እና ክፍት ቦታዎች፣ አሁን ሰፊ የመሮጫ ትራኮችን፣ ዘመናዊ የብስክሌት መንገዶችንና ለሰውነት ማጎልመሻ ምቹ የሆኑ አረንጓዴ ፓርኮችን ታቅፈው ብቅ ብለዋል።

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ያስገኟቸው ሰፋፊ የእግረኛ መንገዶች እና የህዝብ መዝናኛ ፓርኮች፣ ስፖርትን ከጥቂቶች ልምድነት አውጥተው የብዙኃኑ የከተማ ነዋሪዎች የዕለት ተዕለት ባህል እንዲሆን አስችለዋል። ይህ ሽግግር ከተማዋን በህንፃ ብቻ ሳይሆን በነዋሪዎቿ የኑሮ ጥራትና ንቁ እንቅስቃሴ የምትለካ ዘመናዊ ሜትሮፖሊታን ከተማ እያደረጋት ይገኛል።

ሰሞኑን የተመረቀው አራዳ ፓርክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው ‘የስፖርት አሬና’፣ 5 ኪሎ ሜትር የመሮጫ፣ 5 ኪሎ ሜትር የብስክሌት መጋለቢያ፣ እንዲሁም 6 ኪሎ ሜትር የእግረኛ መንገዶችን የያዘ ነው። እነዚህ መሰረተ ልማቶች የማኅበረሰቡን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የማድረግ ባህል ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸውም ተጠቁሟል። ለነዋሪዎች ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን እንዲከተሉ የሚያስችል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልፀዋል።

አራዳ ፓርክ ከመዝናኛነት ባለፈ ትልቅ የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ትስስር ማዕከል እንዲሆን ታስቦ የተገነባ መሆኑንም ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በመልዕክታቸው ጠቅሰዋል። ለልማት ተነሺዎች ቅድሚያ የተሰጠባቸው ከ131 በላይ ሱቆች፣ የጥበብ ማሳያ ጋለሪዎች፣ እንዲሁም አብዛኞዎቹ በነጻ የሚያገለግሉ የህጻናት መጫወቻዎችን አሟልቶ ይዟል። የከተማዋ የመኪና ማቆሚያ ችግር ታሳቢ በማድረግም በአንድ ጊዜ ከ130 በላይ ተሽከርካሪዎችን የሚያስተናግድ ከመሬት በታች ያለ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያ ተገንብቶለታል።

በአዲስ አበባ ከተማ እምብርት ተገንብቶ ሰሞኑን የተመረቀው የአራዳ ፓርክ፣ ከተማዋ ወደ ዘመናዊ አሬናዎችና ሁለገብ መዝናኛዎች እያደረገች ላለው ሽግግር ትልቅ ማሳያ ነው። ይህ ፓርክ በውስጡ የያዘው ዘመናዊ ሁለገብ አሬና (Multipurpose Arena) ለቅርጫት ኳስ፣ ለቮሊ ቦል እና ለሌሎች የቤት ውስጥ ስፖርቶች ምቹ ሆኖ ከመዘጋጀቱም በላይ፣ ለታላላቅ ስብሰባዎችና ለባህላዊ ኩነቶችም ጭምር አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ የተነደፈ ነው። ይህም አሬናዎች ለስፖርት ብቻ ሳይሆን ለማህበራዊ ትስስርና ለከተማ ውበት ያላቸውን ከፍተኛ ፋይዳ በአካባቢያችን በተግባር ያሳየ ፕሮጀክት ሆኗል።

በእርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃም በርካታ አሬናዎች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ “የዓለማችን ዝነኛው አሬና” በሚል ቅጽል የሚታወቀው የኒው ዮርኩ ሜዲሰን ስኩዌር ጋርደን፣ ከቅርጫት ኳስ እስከ ቦክስ ውድድሮች እንዲሁም ለታላላቅ የሙዚቃ ኮንሰርቶች ቀዳሚ ምርጫ ሆኖ ለበርካታ አስርት ዓመታት ስለመዝለቁ የዘኒዮርክ ታይምስ ዘገባ ያሳያል። በአውሮፓ እንደዚሁ የለንደኑ “ኦ2 አሬና” በዓመት ውስጥ ከ200 በላይ ትልልቅ ኩነቶችን በማስተናገድ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። በመካከለኛው ምስራቅ እንደ “ሉሳይል መልቲ ፐርፐዝ አሬና” ያሉ ግንባታዎች በበረሃው መሃል እንደ አልማዝ የሚያበሩና የሀገራትን የዕድገት ደረጃ የሚያሳዩ አዳዲስ ምልክቶች ስለመሆናቸው የተለያዩ የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ።

እነዚህ ግዙፍ ማዕከላት እንደ አዲስ አበባ ላሉ አዳጊ ከተሞች ትልቅ ትምህርት የሚሰጡ ሲሆን፣ ስፖርታዊና ባህላዊ መሰረተ ልማቶች እንዴት የከተማን ተወዳዳሪነትና የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ ከፍ እንደሚያደርጉ በተግባር ያሳያሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ በስፖርት መሠረተ ልማትና በከተማ ልማት መካከል ያለውን ትስስር የሚያጠኑት ታዋቂው የዘርፉ ባለሙያ ፕሮፌሰር አንድሪው ዚምባሊስት እንደሚሉትም ከስፖርት ባሻገር የዛሬዎቹ አሬናዎች ዲዛይናቸው ሁለገብ በመሆኑ ለሀገራት ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ይሰጣሉ።

አንድ ትልቅ አሬና ባለበት አካባቢ የሆቴሎች፣ የምግብ ቤቶችና የትራንስፖርት አገልግሎቶች በከፍተኛ ሁኔታ ይነቃቃሉ፤ ይህም ለአካባቢው ነዋሪዎች በሺዎች የሚቆጠር የሥራ ዕድል ይፈጥራል። ከስፖርት ውጭ ለትልልቅ የቴክኖሎጂ አውደ-ርዕዮች፣ ለዓለም አቀፍ ጉባኤዎችና ለታላላቅ የኪነ-ጥበብ ስራዎች እንደ ዋነኛ መገናኛ ያገለግላሉ። በአጠቃላይ አሬናዎች ተመልካቹን ከሜዳው ጋር በምናባዊ እውነታ (Virtual Reality) የሚያገናኙባቸው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች እየታዩባቸው ሲሆን፣ ወደፊትም የማህበረሰቡ ዋና የባህልና የመዝናኛ ማዕከል ሆነው እንደሚቀጥሉ ይታመናል።

ፕሮፌሰር አንድሪው ጨምረው እንደሚገልፁት ዘመናዊ አሬናዎች ከስፖርት ማዘውተሪያነት ባለፈ፣ የከተሞች የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። አንድ አሬና በአንድ አካባቢ ሲገነባ፣ በዙሪያው ያሉ የንግድ ተቋማት፣ ዓለም አቀፍ ሆቴሎችና የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች በከፍተኛ ፍጥነት እንዲያድጉ ያደርጋል።


ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ በትላልቅ ከተሞች የሚገኙ አሬናዎች ለሺዎች የሚቆጠር ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ከመፍጠራቸውም በላይ፣ በውድድሮች ወቅት ለሚጎርፉ እንግዶች በሚቀርቡ አገልግሎቶች አማካኝነት በሚሊዮን የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ ለሀገራት ገቢ ያስገኛሉ። ይህም አሬናዎችን ለከተማ ልማትና ለኢኮኖሚ መነቃቃት እንደ ዋነኛ ስልታዊ መሣሪያ እንዲታዩ አድርጓቸዋል።

ከገንዘብ ጥቅሙ ባሻገር፣ አሬናዎች ማህበረሰቡን በአንድ ጥላ ስር የሚያገናኙ ጠንካራ ማህበራዊ ድልድዮች ናቸው። በተለይም በተለያዩ የባህልና የቋንቋ ዳራዎች ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ለስፖርት ፍቅር በአንድ መድረክ ላይ እንዲገናኙ በማድረግ ረገድ ወደር የላቸውም። እንደዚሁም አሬናዎች የከተሞች ‘ሳምባ’ በመሆን፣ ግለሰቦች ከቤታቸው ወጥተው ከሌሎች ጋር እንዲገናኙና ማህበራዊ ህይወታቸውን እንዲያጠናክሩ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። እንደዚሁም በቴሌቪዥንና በሶሻል ሚዲያ በሚተላለፉ ምስሎች አማካኝነት የከተማዋን ውበት ለቢሊዮኖች የሚያስተዋውቁ “ሕያው የማስታወቂያ ሰሌዳዎች” በመሆን የሀገራቸውን ስም ለዓለም ለማህብረሰብ ለማስተዋወቅ ያግዛሉ።

ከአረንጓዴው ስፍራ በተጨማሪ ዘመናዊ የስፖርት ማዘውተሪያ፣ ጂምናዚየም እና 7 አዳራሾችን ያካተተው የአረዳ ፓርክ በውስጡ የያዘው ስፖርት አሬናም ለወጣቶች የጤናማ ትውልድ መፍለቂያ አውድማዎች እንዲሆን ታስቦ የተገነባ ነው። ወጣቶችም እነዚህ ስፍራዎች ከቤትና ከስራ ውጥረት ወጥተው ስፖርታዊ እንቅስቃሴን እንደ የዕለት ተዕለት ባህል እንዲቀበሉ ከፍተኛ መነሳሳትን እንደፈጠረላቸው ይናገራሉ።

በአዲሱ የኮሪደር ልማት ማሳያ በሆነው በአራዳ ፓርክ የመሮጫ ትራክ ላይ ያገኘናቸው ወጣቶች ፊታቸው ላይ የሚታየው ብሩህ ተስፋ የለውጡን ትርጉም በግልጽ ያሳያል። “ቀደም ሲል ስፖርት ለመስራት ወይ ሜዳ መከራየት አለያም መኪና በሚበዛበት አስፋልት ዳር በጥንቃቄ እየተጋፋን መሮጥ ነበረብን” ይላል የ24 ዓመቱ ወጣት አማኑኤል እጅጉ። አክሎም፣ “አሁን ግን እንደ ልብ የምንተነፍስባቸውና ያለምንም ስጋት የምንሮጥባቸው የራሳችን መንገዶች አሉን። ይህ ለጤናችን ብቻ ሳይሆን ከጓደኞቻችን ጋር የምንገናኝበትና ቀናችንን በጥሩ መንፈስ የምንጀምርበት ቦታ ሆኖልናል” ሲል በደስታ ይገልጻል።

በአዲስ አበባ ከተማ እምብርት የተገነባው አዲሱ አራዳ ፓርክ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች አካታች በሆነ መልኩ ለጋራ ጥቅም ስለመገንባቱ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር መግለጻቸው የሚታወስ ነው፡፡


የጥበበኞቹ
ዘመን
ተሻጋሪ
መታወሻዎች